ይህንንም ፡ ቃል ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ መጥቀሴ ፡ ማንኛውም ፡ ሰው ፡ የዕለት ፡ እንጀራ ፡ ፈላጊ ፡ ሆኖ ፡ የሆነ ፡ ያልሆነውን ፡ ሲቀባጥር ፡ ነገሩ ፡ እየከረረ ፡ ከትልቅ ፡ ጠብ ፡ ላይ ፡ የሚደርሰው ፡ ሳይጣራ ፡ በመቅረቱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ቢጣራ ፡ ግን ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ የነበረው ፡ ሁናቴ ፡ ከፍሬው ፡ ገለባው ፡ ይበዛ ፡ እንደነበረ ፡ ማስረጃ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ነው ።

## ምዕራፍ ፡ ፱ ።

## ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ (የቋና) ፡ ውጊያ ።

### ፩ኛ ፤ ጉግሣ ፡ ወሌና ፡ የአንችም ፡ ውጊያ ።

ይህ ፡ ታልፎ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ እንደቆየ ፡ የበጌምድሩ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢ ፡ ቀድሞ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ባል ፡ የነበሩት ፡ እላይ ፡ ጠቅሼ፡ እንደነበረውና ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ያልተደረገውን ፡ ተደረገ ፡ በሚል ፡ በሐሰተኛ ፡ ወሬ ፡ ተመርተው ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ ትእዛዝና ፡ ሥልጣን ፡ ውጭ ፡ ሆነው ፡ ከንግሥትም ፡ ከአልጋ ፡ ወራሽም ፡ መልክት ፡ ቢላክባቸው ፡ አልሰማም ፡ ብለው ፡ ጦራቸውን ፡ አስከትተው ፡ ለመዋጋት ፡ መደራጀታቸው ፡ ተሰማ ።

በመንግሥቱም ፡ በኩል ፡ ከብዙ ፡ ጊዜ ፡ መላላክ ፡ በኋላ ፡ የማይመለሱ ፡ መሆናቸውን ፡ ስለ ፡ ተረዳ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታን ፡ አዝዞ ፤ እሺ ፡ ቢሉ ፡ በሰላም ፡ እንዲገቡ ፡ እምቢም ፡ ቢሉ ፡ በማስገደድ ፡ አስፈላጊውን ፡ እንዲፈጽሙ ፡ በ፲፱፻፳፪ ፡ ዓ ፡ ም ፡ በየካቲት ፡ ወር ፡ ላኳቸው ። የጦር ፡ ሚኒስትሩም ፡ እንደ ፡ ትእዛዙ ፡ ለመፈጸም ፡ ከሸዋ ፡ ወደ ፡ ቤጌምድር ፡ ተጉዘው ፡ በዚሁ ፡ ዓመት ፡ በመጋቢት ፡ ወር ፡ ፩ ቋና ፡ አንችም፡ ከተባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ጦር ፡ ተገናኘ ። በሰላም ፡ ለመግባት ፡ የታሰበውም ፡ ቀርቶ ፡ ተዋጉና ፡ በዚሁ ፡ ጦርነት ፡ ውስጥ ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ መጋቢት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ሰኞ ፡ በጦርነት ፡ ላይ ፡ ሞቱ ።

### ፪ኛ ፡ የንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ማረፍ ፤

ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱም ፡ የጦር ፡ ሚኒስትራቸው ፡ ድል ፡ ማድረጋቸውን ፡ ሲሰሙ ፡ የራስ ፡ ጉግሣን ፡ በጦሩ ፡ ላይ ፡ መሞት ፡ ገና ፡ ሳይሰሙ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ ከስምንት ፡ ቀን ፡ በፊት ፡ እንደ ፡ ግራብ ፡ አድርጎአሚቸው ፡ በነበረው ፡ ሕመም ፡ ምክንያት ፡ መጋቢት ፡ ፳፬ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፪ ዓ ፡ ም ፡ አረፉ ። ሥርዐተ ፡ ቀብራቸውም ፡ ለአባታቸው ፡ ለዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ መታሰቢያ ፡ ባሠሩት ፡ ቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ በምድር ፡ ቤቱ ፡ አረፈ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ግርማዊ ፡ ንጉሥ ፡ ተፈሪ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ ተብለው ፡ በዙፋኑ ፡ ተተኩ ።

---

፩ ቋና ፡ አንችም ፡ የተባለው ፡ አገር ፡ በቤጌምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ውስጥ ፡ ነው ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ።





ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ከግርማዊት ፡ እቴጌ ፡ መነንና ፡ ከልዑላን ፡ ልጆቻቸው ፡ ጋር ፡ ከግራ ፡ ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋወሰን ፡ በመካከል ፡ ልዑል ፡ መኰንን ።



ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ አስፋወሰን ፡ ከመኳንንቶች ፡ ጋር ።

ንግሥት ፡ ዘውዲቱ ፡ በሞቱ ፡ ጊዜ ፡ የተለቀሰው ፡ ልቅሶ ፡ እንደ ዚህ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ዓይነቱን ፡ ለመጻፍ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነው ። መኳንንቱ ፡ ወይዛዝሩ ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ አደባባይና ፡ ቅጽር ፡ ግቢ ፡ ካህኑ ፡ በየ ቤተ ፡ ክርስቲያኑ ፡ ድኃው ፡ በየሚኖደው ፡ በገዛ ፡ ፈቃዱ ፡ እየተሰበሰበ ፡ የውሎ ፡ ለቅሶ ፡ እያደረገ ፡ ሲያለቅሱ ፡ ከማሳዘኑም ፡ በላይ ፡ ለተመለከ ተው ፡ የሚያስደንቅና ፡ የሚያስገርም ፡ ነበር ።

ብዙ ፡ የልቅሶ ፡ ግጥሞችም ፡ እያንዳንዱ ፡ መኳንንትና ፡ ካህን ፡ ከተራ ም ፡ ሰው ፡ እየተደረሰ ፡ በተባራሪ ፡ ወረቀት ፡ እየታተሙ ፡ በየአደ ባባዩ ፡ ይበተኑ ፡ ነበር ። ከብዙ ውም ፡ ግጥም ፡ ለጊዜው ፡ ትዝ ፡ የሚለኝ ፡ ለምሳሌ ፡ ስልቱ ፡ እንዲታወቅ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ እጠቅሰዋለሁ ።

የምኒልክን ፡ ቤት ፡ መሰብሰቢያችንን ፤
ትልቁን ፡ አዳራሽ ፡ ይፍረስ ፡ ያለው ፡ ማነው ፤
አባቱ ፡ ግድግዳው ፡ ባሪያው ፡ መከንን ፡ ነው ።
ገበየሁ ፡ ማገሩ ፡ ባልቻ ፡ ገመዱ ፡ ነው ፤



ተሰማ ፡ ክዳኑ ፡ የማያፈሰዉ ፡ ነው ፤
ምኒልክ ፡ ምሰሶው ፡ የማያጋድለው ፤

እንደዚህ ፡ በኅብረት ፡ የተሠራ ፡ ሆኖ ፡ ለዘውዲቱ ፡ ደርሶአት ፤
በኀዘን ፡ በጸሎት ፡ ያጸናችው ፡ ቤት ፤
ቢገፉት ፡ ቢገፉት ፡ ቢገፉት ፡ አይፈርስም ፡ ቢነቀንቁት ።

ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፡ እዘኝ ፡ ኀዘን ፡ ይገባሻል ፤
እነሆ፡ብርሃንሽ፡ንግሥተ፡ነገሥታት፡ዘውዲቱ፡ምኒልክ፡ጠፍታለችና፤
እኔ ፡ ባሪያሽ ፡ ልጥፋ ፡
አንች ፡ ነበርሽና ፡ የነዳያን ፡ ተስፋ ።
ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፤ አልቅሽ ፡ ልቅሶ ፡ ይገባሻል ፤
አበባሽ ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ረግፋለችና ፤
እኔ ፡ ባሪያሽ ፡ ልርገፍ ፡
ሐሰት ፡ በቃልሽ ፡ አይጸፍ ፤
ኢትዮጵያ ፡ ሆይ ፤ ማቅ ፡ ልበሽ ፡ ማቅ ፡ መልበስ ፡ ይገባሻል ፤

ልምላሜሽ ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ተለይታሻለችና ፡
እኔ ፡ ልለያይ ፤
አንች ፡ ነበርሽና ፡ የነዳያን ፡ ሲሳይ ።
ኢትዮጵያ ፡ ተክዥ ፡ ትካዜ ፡ ይገባሻል ፤
ክሳትሽንና ፡ ጥቁረትሽን ፡ ላኀይሽንና ፡ ደምግባትሽን ፤
የምታይበት ፡ መስተዋትሽ ፡ ተሰብራለችና ፡
ይሰበረኝ ፡ ይሰበረኝ ፤
ሐሰት ፡ በቃልሽ ፡ አይገኝ ፤

እኔ ፡ ባሪያሽ ፡ ልሰበር ፤
አንቺ ፡ ነበርሽና ፡ የሀንካሣን ፡ እግር ፤
ወዓይን ፡ ለዕውር ።

ከጥንት ፡ ጀምሮ ፡ ከአዳም ፤
ተጽፎ ፡ አያልቅም ፡ ዓለም ፤
የኔ ፡ ወገኖች ፡ መልካካም ፤
ቀስተንቻ ፡ ብርዕ ፡ አያውቁም ፤
ያለመቃብር ፡ አይጽፉም ፤

ከፊን ፡ እንኳን ፡ የለኝ ፡ እዩልኝ ፡ ማጣቴን ፤
ሣጥን ፡ እንኳን ፡ የለኝ ፡ እዩልኝ ፡ ድህነቴን ፡
ዓለምን ፡ ዓለምን ፡ ቀበርኋት ፡ እናቴን ።
ዘሬን ፡ ዘርቼ ፡ በደን ፡
እጠብቃለሁ ፡ ዋኔን ፤

ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ የሌለባት ፡ መላ ፡
ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ የካህናት ፡ ተድላ ፤
ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ የነዳያን ፡ ሾላ ፤
ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ለወንጌል ፡ አክሊላ ፤
ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ ለቤተ ፡ ክርስቲያን ፡ ቀጸላ ፤
ፍቅርተ ፡ ሃይማኖት ፡ ጽንዕተ ፡ መሐላ ፤
ሞተች ፡ ተቀበረች ፡ እርሷም ፡ እንደሌላ ፤
አሳድጋኝ ፡ ነበር ፡ እጅግ ፡ አቀማጥላ ፡
እንደ ፡ እናት ፡ እንደ ፡ አባት ፡ እርሷው ፡ ድራ ፡ ኩላ ፤
ንብረቴን ፡ ትዳሬን ፡ በጣም ፡ አደላድላ ፤
ምናኔ ፡ ቀረብኝ ፡ እርሷ ፡ አፈር ፡ ስትበላ ።

እራሱን ፡ ላመመው ፡ ለሚያተኩሰው ፡
ጊዜዋ ፡ ነበረ ፡ የሚፈውሰው ።
ቅጠሉን ፡ ቀጥቅጦ ፡ አሽቶ ፡ ለጠጣው ፡
ጊዜዋ ፡ ነበረ ፡ የሚያስቀምጠው ።

በጉ ፡ እየተሳበ ፡ ፍሪዳው ፡ ሲነዳ ፡
ቅቤው ፡ ተሰናድቶ ፡ ማሩ ፡ እየተቀዳ ፤
እንደባላገር ፡ ልጅ ፡ እኩል ፡ አስለምዳ ፤
በምኔ ፡ ልሸኘው ፡ የሆዴን ፡ እንግዳ ።

እንግዲህ ፡ አልተክልም ፡ የጌሾ ፡ አታክልት ፡
ወይኔ ፡ ይበቃኛል ፡ ለራሴ ፡ ንብረት ።
ምንም ፡ እንባ ፡ አልወጣኝ ፡ እያዘነ ፡ ሆዴ ፡
እንዳልጽናናማ ፡ ብዙ ፡ ነው ፡ ልማዴ ።

መቀነቴ ፡ ጠፋ ፡ እራቤ ፡ በልቶታል ፡
ይህን ፡ ለግርማዊት ፡ ማን ፡ ይነግራታል ።

በዳሞት ፡ ጐዳና ፡ በሚያስፈራው ፡ ደን ፡
እንደምን ፡ አለፉት ፡ ንግሥት ፡ ብቻዎን ።

በዳሞት ፡ ጎዳና ፡ በሌለበት ፡ ዳኛ ፤
እንደምን ፡ አለፉት ፡ የሴት ፡ መንገደኛ ።

ብቻዎንም ፡ አይደል ፡ ንግሥት ፡ የሄዱት ፡
ተከትለዎታል ፡ ከኋላም ፡ ከፊት ፤
ብዙ ፡ ወይዛዝሮች ፡ ብዙ ፡ መኳንንት ።
ምንም ፡ ሰው ፡ አልቀረ ፡ ካባትዎ ፡ ሎሌ ፤
እነደጃች ፡ መርዕድ ፡ እንደጃች ፡ ገድሌ ።



እንኳን ፡ ቤተ ፡ ንጉሥ ፡ አልሠራም ፡ ሰቀላ ፡
ክብረወርቅ ፡ ስትነግረኝ ፡ ላፈርሰው ፡ ነው ፡ ብላ ።

ትልቁ ፡ ደጃዝማች ፡ በሩን ፡ ከፈተው ፡
ይተላለፍበት ፡ የተሰለፈው ፡
እሱው ፡ እንደሠራው ፡ እሱው ፡ አፈረሰው ።

ትልቁ ፡ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ሥላሴማ ፡
ባለጅ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ሁሉ ፡ ሲተማማ ፤
ጦር ፡ ሠሪ ፡ ነው ፡ አለኝ ፡ ያ ፡ መልአከ ፡ ራማ ።
ጦር ፡ ያሠራ ፡ ነበር ፡ ጥንቱንም ፡ ስንሰማ ፤
አያጣምና ፡ ሰው ፡ ኃይለማርያም ፡ ለማ ።
በንጉሥ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ በነ ፡ ራስ ፡ ተሰማ ።

ለሥዩም ፡ ሉልሰገድ ፡ ለውነተኛው ፡ ጀግና ፡
ፈረሱን ፡ አምጡለት ፡ መጣምር ፡ ጫኑና ፤
እንደርሱ ፡ ያለ ፡ ሰው ፡ በቅሎ ፡ አያውቅምና ።

የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሃብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ጠቃሚ ፡ ነበረ ፡ የሁሉንም ፡ ልብስ ፤
መርፌው ፡ አይሰበር ፡ ክሩ ፡ አይበጠስ ፤
እንግዲህ ፡ ለምኔ ፡ ጎጆ ፡ መቀለስ ፤
የራስ ፡ ሃብተ ፡ ማርያም ፡ ጠንካራው ፡ ሲፈርስ ።

እናንተ ፡ መኳንንቶች ፡ በጣም ፡ አትዘኑ ፡
እናንት ፡ ወይዛዝርቶች ፡ ከሐዘን ፡ ተጽናኑ ፤
ቢዳምን ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ገና ፡ አልመሸም ፡ ቀኑ ።

እያለ ፡ በዘመነ ፡ መንግሥታቸው ፡ የነበረውን ፡ መልካምነት ፡ ይገልጥ ፡ ነበር ።

# ምዕራፍ ፡ ፲ ።

## በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወግና ፡ ሥርዐት ፡ (ፕሮቶኮል) ።

፩ ፡ በቀድሞው ፡ ጊዜ ፡ የአስተዳደር ፡ ዘዴ ፡ በእህል ፡ በውኃ ፡ ግንኙነት ፡ በማድረግ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ከልዑላን ፡ መሳፍንትና ፡ መኳንንት ፡ አንስቶ ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ተራ ፡ ሰው ፡ ድረስ ፡ ግብር ፡ ይበላል ። መሳፍንቱና ፡ መኳንንቱ ፡ በእልፍኝና ፡ በእልፍኝ ፡ አዳራሽ ፡ እንደ ፡ ማዕረጋቸው ፡ ዘወትር ፡ ምሳ ፡ ይጋበዛሉ ፤ በየሳምንቱም ፡ እሑድ ፡ እሑድ ፡ በታላቁ ፡ አዳራሽ ፡ ሙሉ ፡ ግብር ፡ ሆኖ ፡ ሕዝቡ ፡ በሙሉ ፡ ይጋበዛል ። በግብሩ ውም ፡ ጊዜ ፡ ከሕዝቡ ፡ ብዛት ፡ የተነሳ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ለመብላት ፡ ቦታው ፡ ሳይበቃ ፡ በመቅረቱ ፡ በየተራ ፡ እንዲገባ ፡ እየተደረገ ፡ እስከ ፡ ፫ ፡ ጊዜ ፡ በሚደረገው ፡ ግብር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በአዳራሹ ፡ ይቀመጣሉ ፤ አራተኛውንና ፡ ከዚያም ፡ የሚቀጥለውን ፡ ሹማምንቱ ፡ ማለት ፡ አዛዥና ፡ አጋፋሪው ፡ ያበላሉ ።

፪ ፤ ግብሩ ፡ ከቅጥር ፡ ወደ ፡ እልፍኝ ፡ ወይም ፡ ወደ ፡ አዳራሽ ፡ በማሄድበት ፡ ጊዜ ፡ ባለወጉ ፡ በግብር ፡ ጊዜ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ አሰናድቶና ፡ ከየሥፍራው ፡ አስመጥቶ ፡ አንድ ፡ አማካይ ፡ በሆነ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ አደራጅቶ ፡ ይጠባበቃል ። የግብር ፡ መግቢያው ፡ ሰዓት ፡ ሲደርስ ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካዮች ፡ ግብር ፡ አቅርቡ ፡ ብለው ፡ ወደ ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ አንድ ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ይልካሉ ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ባለወግ ፡ የሆኑ ፡ ሹማምንቶች ፡ የቅደም ፡ ተከተል ፡ ተራቸውን ፡ ይዘው ፡ ይጠባበቁ ፡ ነበርና ፡ ተነሥተው ፡ ጉዞ ፡ ይጀምራሉ ።

፫ ፤ የጉዞው ፡ ሥርዐት ፡ በመጀመሪያ ፡ ሙሉቤት ፡ አዛዥ ፡ ከዚያ ፡ ምክትሉ ፡ ግብር ፡ አቅራቢ ፡ የሆነው ፡ ይከተላል ፤ ከዚያም ፡ በኋላ ፤

(ሀ) ፋና ፡ ወጊ ፡ የተባለው ፡ ድንብ ፡ ፋና ፡ ተብሎ ፡ የሚጠራውን ፡ በአንዳንድ ፡ ዐርብ ፡ በለሴ ፡ ጨርቅ ፡ በድንብ ፡ የተነከሩ ፡ ጧፎችና ፡ ለዚህ ፡ አገልግሎት ፡ የተዘጋጁትን ፡ የሻማ ፡ ማብሪያ ፡ በብር ፡ በተሠሩ ፡ መጋረያዎች ፡ ይዞ ፡ ባለቃው ፡ እየተመራ ፡ ይገባል ።

(ለ) ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ እስታጣቢ ፡ የሚባለው ፡ ድንብ ፡ ባለቃው ፡ እየተመራ ፡ ለንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መታጠቢያ ፡ የሚሆን ፡ ከወርቅና ፡ ከብር ፡ የተሠራ ፡ ሰንና ፡ ብርት ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንቶች ፡ (ለራሶች) ፡ የሚሆን



ውን ፡ መታጠቢያ ፡ ከብር ፡ የተሠራ ፡ ብርት ፤ ከዚያም ፡ ቀጥሎ ፡ ለደጃዝማቾችና ፡ ለፊታውራሪዎች ፡ የሚሆነውን ፡ ከነሐስ ፡ የተሠራ ፡ ብርት ፤ ውሀውንም ፡ በእርኩትና ፡ በብረት ፡ ጀበና ፡ ይዞ ፡ እንደ ፡ ደረጃው ፡ ቅደም ፡ ተከተሉን ፡ ጠብቆ ፡ ይገባል ።

(ሐ) ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ሦስተኛው ፡ ምክትል ፡ አዛዥ ፡ ቀዳሚ ፡ ሆኖ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ምግብ ፡ የያዘውን ፡ መሶብ ፡ አስከትሎ ፡ ይገባል ። ሌላውም ፡ መሶብ ፡ እንደ ፡ ደረጃው ፡ ተከታትሎ ፡ እንደዚሁም ፡ መበያ ፡ የሚሆነው ፡ ወጥ ፡ የተባለው ፡ ምግብ ፡ ማለፊያና ፡ ዶዮው ፡ ተከታትሎ ፡ ይገባል ።

(መ) ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ጠጅና ፡ ጠላ ፡ በገንቦ ፡ የተሸከሙት ፡ ተከትለው ፡ ጉዟቸውን ፡ ይቀጥላሉ ።

(ሠ) ቀጂው ፡ ብርሌና ፡ ማብረጃውን ፡ ይዞ ፡ ይከተላል ።

(ረ) ሥጋ ፡ ቤቱ ፡ ቢላዎችንና ፡ ለሥጋ ፡ መብያ ፡ አስፈላጊ ፡ የሆኑትን ፡ ይዞ ፡ ይከተላል ። በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ሥርዓትና ፡ ተራ ፡ የግብሩ ፡ አቀራረብ ፡ ጉዞ ፡ ተቀጣጥሎ ፡ ሲራመድ ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዡ ፡ ምግብ ፡ አቅራቢዎችን ፡ በመምራት ፡ እፊት ፡ እፊት ፡ ይሄዳል ።

፬ ፡ ይህ ፡ በሚደረግበት ፡ ጊዜ ፡ በአደባባዩ ፡ የሚገኘው ፡ ከተራው ፡ ሰው ፡ እስከ ፡ ራሶች ፡ የሆኑ ፡ ሁሉ ፡ የግብሩ ፡ ጉዞ ፡ በአቅራቢያቸው ፡ ሲደርስ ፡ ሁሉም ፡ ከየመቀመጫቸው ፡ ተነስተው ፡ ግብሩ ፡ እስቲያልፍ ፡ ድረስ ፡ ይቆማሉ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዡ ፡ ሎክ ፡ ብሎ ፡ በሚሰማ ፡ ድምፅ ፡ እንጀራ ፡ ይስጣችሁ ፡ ከሚል ፡ ድምፅ ፡ ጋራ ፡ እጅ ፡ እየነሳ ፡ ያልፋል ። እማቅረቢያው ፡ ሥፍራ ፡ አድርሶ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እግብር ፡ መብያው ፡ ቤት ፡ እስቲቀመጡ ፡ ይጠባበቃል ፤

፭ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ በዙፋናቸው ፡ ሲገኙ ፡ እልፍኝ ፡ አስከልካዩ ፡ ግብር ፡ ይቅረብ ፡ ብሎ ፡ ለአዛዡ ፡ ይነግራል ፤ በመጀመሪያ ፡ እጅ ፡ እስታጣቢው ፡ ሰንና ፡ ብርቱን ፡ ይዞ ፡ ሲቀድም ፡ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ ከምክትሉ ፡ ጋራ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ የማዕድ ፡ መሶብ ፡ ለሁለት ፡ ይዘው ፡ እየተንገደዱ ፡ ይቀርባሉ ፤ በዚህ ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ቆሞስነት ፡ ያለው ፡ መነኩሴ ፡ ቀርቦ ፡ በቡራኬ ፡ ያሳርግና ፡ ይመለሳል ፤ ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዥ ፡ መሶቡን ፡ ከፍቶ ፡ ሲመለስ ፡ የእንጀራ ፡ አሳላፊው ፡ ለቅልጥፍና ፡ በሚያመችው ፡ ዐይነት ፡ ልብሱን ፡ ከብብቱ ፡ በታች ፡ በወገቡ ፡ ላይ ፡ አሽርጦ ፡ ወይም ፡ ታጥቆ ፡ ይቀርብና ፡ ሥራው ፡ በቀስጠፈ ፡ ሁኔታ ፡ ይቀጥላል ። ወጡ ፡ በየመሶቡ ፡ ላይ ፡ ከመውጣቱ ፡ በፊት ፡ የቀረበው ፡ ድስት ፡ ከአሥር ፡ እስከ ፡ ፲፯ ፡ ስለሚሆን ፡ የነጭ ፡ ቤቷም ፡ ሹም ፡ አንዳንድ ፡ እንጀራ ፡ በየድስቱ ፡ ወስከንባይ ፡ ላይ ፡ ታኖራለች ፤ ወጥቤቶቹ ፡ ወስከንባ

ዩን ፡ ከፍተው ፡ እንጀራውን ፡ ሲይዙ ፡ አሳላፊው ፡ በየእንጀራው ፡ ላይ ፡ አንድ ፡ የእጅ ፡ ጭልፋ ፡ ለቅምሻ ፡ ወጥ ፡ ያወጣላቸውና ፡ ይዘው ፡ ይመለሳሉ ። ወዲያው ፡ ለልዑላን ፡ መሳፍንቶችና ፡ መኳንንቶች ፡ የሚቀርበው ፡ መሶብ ፡ በአዛዦች ፡ እየቀረበ ፡ እንጀራ ፡ አሳላፊዎቹ ፡ በቀለጠፈ ፡ ሁናቴ ፡ በየደረጃው ፡ ይደረድራሉ ።

፺ ፡ ይህ ፡ መሰናዶ ፡ እንደተደራጀ ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካዩ ፡ እንደየማዕረጉ ፡ መሳፍንቶችንና ፡ መኳንንቶችን ፡ ወይዛዝሮችንም ፡ እየጠራ ፡ ያስቀምጣል ፡ እንደተቀመጡም ፡ አዛዦች ፡ መሶቡን ፡ እየከፈቱ ፡ ይመለሳሉ ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ቀጂው ፡ በየብርሌዎች ፡ ከሞላ ፡ በኋላ ፡ ለከፍተኛ ፡ ባለወንች ፡ ስለ ፡ ክብራቸው ፡ በአፈ ፡ ድስት ፡ ብርሌ ፡ ልዩ ፡ ዐይነት ፡ በሆነ ፡ ከፈይ ፡ ጨርቅ ፡ ተሸፍኖ ፡ የሚሰጣቸውን ፡ በአፈ ፡ ድስት ፡ ብርሌ ፡ ሆኖ ፡ ሳይሸፈን ፡ የሚሰጣቸውንና ፡ በሹርቢ ፡ ብርሌ ፡ የሚጠጡትን ፡ ለየብቻቸው ፡ ሞልቶ ፡ ያቀርባል ። የጠጁም ፡ ዐይነት ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ የራሶች ፡ ብልጫ ፡ ያለው ፡ ነው ። የሹሞችም ፡ ጥሩ ፡ ዐይነት ፡ ነው ።

ቀጥሎም ፡ የሚቀርበው ፡ እርጥብ ፡ ሥጋ ፡ ሲሆን ፡ ወዲያው ፡ ቀጥሎ ፡ እንደ ፡ ፍላንቱ ፡ መመገብ ፡ እንዲችል ፡ ጥብሱን ፡ እያዘጋጁ ፡ ያቀርባሉ ፤ ቢላዎንም ፡ ካራ ፡ አሳላፊ ፡ በመባል ፡ የሚጠራው ፡ የዚህ ፡ ክፍል ፡ ሠራተኛ ፡ ሥጋ ፡ ቤቱን ፡ በመከተል ፡ ቢላዎቹን ፡ ያድላል ፤ እንጀራ ፡ አሳላፊዎች ፡ የሥጋ ፡ መብያ ፡ አዋዜና ፡ ድቁሱን ፡ በፊት ፡ በፊቱ ፡ ወይም ፡ በመሶቡ ፡ መካከል ፡ ያደርጋሉ ። በቀድሞው ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ ወግና ፡ ሥርዐት ፡ የግብር ፡ መሰናዶ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሲከናወን ፡ የማስተናበሩ ፡ ሥነ ፡ ሥርዐት ፡ ደግሞ ፡ እንደሚቀጥለው ፡ ነው ።


## የግብር ፡ ማስተናበር ።

በእልፍኝ ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ በእልፍኝ ፡ አዳራሽ ፡ ግብር ፡ ወይም ፡ በታላቁ ፡ የአዳራሽ ፡ ግብር ፡ ላይ ፡ ያቀማመጡ ፡ ደረጃ ፡ እንደ ፡ ሰውዬው ፡ ማዕረግ ፡ ነው ። የመሳፍንትና ፡ የመኳንንት ፡ መቀመጫ ፡ በከፍተኛው ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሆኖ ፡ ከመጋረጃ ፡ ግቢ ፡ ነው ። እነርሱ ፡ ደግሞ ፡ በመካከላቸው ፡ የቅድም ፡ ተከተል ፡ ተራ ፡ አላቸው ። ከዚህም ፡ ቀጥሎ ፡ በመካከለኛው ፡ ደረጃ ፡ ላይ ፡ ሹማምንት ፡ በየማዕረጋቸው ፡ ይቀመጣሉ ። ሌላውም ፡ እንደዚሁ ፡ በየደረጃው ፡ ይቀጥላል ።


የማዕረግ ፡ ዕድገት ፡ ለማግኘትና ፡ ከከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ ለመድረስ ፡ የሚቻለው ፡ ለመንግሥቱ ፡ ታማኝ ፡ ሆኖ ፡ አገልግሎቱን ፡ በሰላም ፡



በ መጀመሪያ ፡ በመጋረጃ ፡ ግቢ ፡ የሚደረገው ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ሥርዓት ፡



በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የተጋበዙት ፡ መጋረጃ ፡ ከተገለጠ ፡ በኋላ ፡ የመኳንንቱ ፡ አቀማመጥ ፡




በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ በመንግሥት ፡ ጀምሮ ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ በዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፫ ፡ ዓ ፡ ም ፡ እልፍኝ ፡ ውስጥ ፡ በመጀመሪያ ፡ ደረጃ ፡ ከሚበሉት ፡ ሌላ ፡ መጋረጃ ፡ ከተገለጠ ፡ በኋላ ፡ የሚበሉ ፡ መኳንንቶች ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ሁኔታ ፡ ቀጥሎ ፡ እንደተመለከተው ፡ ነው ።

መጋረጃ ፡ ከተገለጠ ፡ በኋላ ፡ የሚቀመጡት ፡ በመሶብ ፡ ሳይሆን ፡ በሰደቃ ፡ ማለት ፡ በገበታ ፡ ነው ፡ ገበታውም ፡ የሚዘረጋው ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማዕድ ፡ በሚቀርብበት ፡ ጊዜ ፡ የሚቀርበው ፡ ድንኳን ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ ከመጋረጃው ፡ ግቢ ፡ የሚጋበዙበት ፡ ድስቱ ፡ ከተነሣ ፡ በኋላ ፡ ነው ። በመኳንንቱም ፡ ፊት ፡ የተረበው ፡ መሶብ ፡ በሙሉ ፡ ይነሣና ፡ መኳንንቱ ፡ የነብ ፡ አቀማመጣቸውን ፡ ለውጠ ፡ በተራ ፡ አቀማመጥ ፡ ይቀመጣና ፡ መጋረጃ ፡ ይገለጣል ። በ ዚህ ፡ ጊዜ ፡ መጋረጃው ፡ ከተገለጠ ፡ በኋላ ፡ የሚጋበዙት ፡ ገበታው ፡ ቀድሞ ፡ ድስት ፡ ወደነበረበት ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ማንበር ፡ ቀርበ ፡ ይዘረጋል ፡ ወጡ ፡ በደጆችቱ ፡ ከተበጋጀበት ፡ በኋላ ፡ ስማቸው ፡ በገጽ ፡ ፻፲፬ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ የተጠቀሰት ፡ ሰዎች ፡ እንደማዕረጋቸው ፡ ይቀመጣሉ ።

የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሶብ ፡ ይነሳና ፡ በመሶብ ፡ የሚገኘው ፡ ተመልሶ ፡ ምግብ ፡ እንዳለ ፡ በአንድ ፡ ለዚሁ ፡ ተብሎ ፡ በተዘጋጀ ፡ የቀዳ ፡ አጥሩ ፡ ይገለበጥና ፡ ለአዳዎን ፡ በአንድ ፡ መኳንንት ፡ አማካይነት ፡ ይሰጣል ። የንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ መሶብ ፡ ሲነሳ ፡ አሲታዎቢ ፡ ጠሐውን ፡ በሰንንግ ፡ በብርት ፡ ይዞ ፡ ሲቀርብ ፡ የዞፋን ፡ ቤቱ ፡ ፎጣውን ፡ ይዞ ፡ ይቀርባል ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እጃቸውን ፡ በሚታጠቡበት ፡ ጊዜ ፡ እዚያ ፡ የተቀመጠው ፡ መኳንንቱም ፡ መሳፍንቱም ፡ ይቆማል ። ቆማሽም ፡ ልብሱን ፡ ገልጾ ፡ ነው ፡ የሚቆመው ።

## ባጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ፡




ግርማዊ ፡ አጼ ፡ ምኒልክ ፡ እቴጌ ፡ ጣይቱ ፡

፩

ወይዘሮ ፡ ዘውዲቱ ፡ ምኒልክ ፡
ወይዘሮ ፡ ትሰሜ ፡ ዳርጌ ፡
ወይዘሮ ፡ ዘርፈሸዋል ፡ ሰይፉ ፡
ወይዘሮ ፡ አሰለፈች ፡ ወንዴ ፡
ወይዘሮ ፡ የሺ ፡ እመቤት ፡

፪

ደጃዝማች ፡ ወሰን ፡ ሰገድ ፡ ምኒልክ ፡

፫

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡
ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡
ልጅ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
ልጅ፡ ደስታ ፡ ብሩ ፡

ልጅ፡ አምቻው ፡ ገሥሡ ፡
ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡

፬

ራስ ፡ ወሌ ፡

፭

ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ አበ ሰይጣን ፡

፮

ወህኒ ፡ አዛዥ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡ የአን ኮበሩ ፡

1

ራስ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ራስ ፡ መኰንን ፡
ራስ ፡ ተሰማ ፡

2

ራስ ፡ ሚካኤል ፡
ራስ ፡ መንገሻ ፡ አቲከም ፡

3

ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡
ደጃዝማች ፡ ውቤ ፡
ደጃዝማች ፡ ተሰማ ፡ ዳርጌ ፡
ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡
ደጃዝማች ፡ ገሥሡ ፡
ራስ ፡ በዛብህ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡

4

ሊቀመኳስ ፡ አባተ ፡



## ባጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ፡

፯

ራስ ፡ ሙሉ ፡ ጌታ ፡
በጅሮንድ ፡ ዘለቀ ፡ መታፈሪያ ፡
ቀኛዝማች ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አማላፊ ፡ መሸሻ ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡

፰

ባላምባራስ ፡ ብሩ ፡ መሸሻ ፡
ልጅ ፡ ደበበ ፡ አንዳርጋቸው ፡
ልጅ ፡ አበበ ፡ ብርቄ ፡
ልጅ ፡ እረኛው ፡ ገዝሙ ፡
ባላምባራስ ፡ ዛሌቻ ፡ ገዝሙ ፡
ልጅ ፡ አበበ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡
ልጅ ፡ መንገሻ ፡ ወሰኔ ፡
(ሊቀ ፡ መኳስ) ፡ ልጅ ፡ መኰንን፡ ዋሌ፡ቱ፡
ልጅ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ መገና ፡

፱

ልጅ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡
ልጅ ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡
ልጅ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡
ልጅ ፡ አሉላ ፡ ጃሌ ፡
ልጅ ፡ በየነ ፡ መርድ ፡
ልጅ ፡ ወርቁ ፡ ጃሌ ፡
ልጅ ፡ ተፈሪ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
ልጅ ፡ ገብሬ ፡ አድነው ፡
ልጅ ፡ ፍቅሬ ፡ ሥላሴ ፡ ከተማ ፡
ገብረ ፡ ማርቆስ ፡

፲

ደጃዝማች ፡ አድማሱ ፡
ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡
ደጃዝማች ፡ ዘሴቱ ፡
ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ አዛለች ፡
ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወልዴ ፡

፲፩

አማላፊ ፡ ድልነሴ ፡
ልጅ ፡ ዘውዴ ፡ ጐበና ፡
አቶ ፡ ደስታ ፡ ገብረየስ ፡
ልጅ ፡ ሸዋዬ ፡
ባልደራስ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡
ልጅ ፡ ይማም ፡ ቴዎድሮስ ፡ (ቀኛዝማች)
አቶ ፡ ሀብቴ ፡ ማርያም ፡

በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ እልፍኝ ፡ አዳራሽና ፡ ሽክላ ፡ ቤት ፡ የሚጋበዙ ፡ ዋና ፡ ዋናዎቹ ።

አፈንጉሥ ፡ ነሲቡ ፡
ፊታውራሪ ፡ ሀብቴ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ራስ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡
ዋግ ፡ ሥዩም ፡ ከበደ ፡

ራስ ፡ ስብሐት ፡
ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ብሩ ፡
ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
ደጃዝማች ፡ ጉግሣ ፡ አርአያ ፡ /ራስ/
ራስ ፡ ወልዴ ፡
ፊታውራሪ ፡ አባይሬ ፡

5

ደጃዝማች ፡ ናደው ፡
ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ መንገሻ ፡
ደጃዝማች ፡ ይልማ ፡
ደጃዝማች ፡ አስፋው ፡ ዳርጌ ፡
ደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
ደጃዝማች ፡ አሊ ፡ ሚካኤል ፡
ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡
ደጃዝማች ፡ በለው ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ሊቀ ፡ መኳስ ፡ አድነው ፡
ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ ሚካኤል ፡
ደጃዝማች ፡ መርድ ፡ መንገሻ ፡
ደጃዝማች ፡ ታዬ ፡ ጉልላቴ ፡

6

ሙሴ ፡ ሊሊክ ፡

7

ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወርቄ ፡

10

ነጋድራስ ፡ ዘውጌ ፡
አቶ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ሰርቢዮን ፡
አቶ ፡ ወ/ገብርኤል ፡ ከተሬ ፡ (ፈታ) ፡

11

በጅሮንድ ፡ ዮሴፍ ፡ (ያባታችን) ፡ ያቡን ፡
ማቴዎስ ፡ አስተርጓሚ ፡

12

አማላፊ ፡ ሠንደቁ ፡
አቶ ፡ ወርቁ ፡
ቀኛዝማች ፡ የሺነህ ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
ባላምባራስ ፡ አስፋው ፡ ባንቴ ፡
አማላፊ ፡ ሀብቴ ፡ ሚካኤል ፡
አማላፊ ፡ ገብረየስ ፡

13

አሳላፊ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡
አብዋ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
አዛዥ ፡ ተክሉ ፡
አቶ ፡ የሀሉ ፡ መብራት ፡

አቶ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ የሸዋምልቶ ፡
አቶ ፡ ዘውዴ ፡ እርገጤ ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ አባጮምር ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ደፋር ፡

14

አፈንጉሥ ፡ እስጢፋኖስ ፡
ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
ፊታውራሪ ፡ ኢብሳ ፡
ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡
ደጃዝማች ፡ ሀብቴ ፡ ሚካኤል ፡
ልጅ ፡ በድሉ ፡ አጥናፌ ፡
አዛዥ ፡ አየለ ፡
ባላምባራስ ፡ ባንቴ ፡
አቶ ፡ ብሩ ፡ (ማንደበል) ፡
ልጅ ፡ እንተሉ ፡
አቶ ፡ ወልደሃና ፡ የሠራተኞች ፡ አለቃ ፡
ልጅ ፡ ማዘው ፡ ብዙነህ ፡
አቶ ፡ ሀብቴ ፡ ወልዴ ፡
አዛዥ ፡ በዛብህ ፡
ደጃዝማች ፡ ማዘው ፡ ጅማ ፡
ደጃዝማች ፡ አምዴ ፡
ደጃዝማች ፡ መታፈሪያ ፡
ደጃዝማች ፡ ክፈተው ፡
ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አፈወርቅ ፡
ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡
ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ ይመር ፡
አዛዥ ፡ አባተምሳሥ ፡
ግራዝማች ፡ ገበየሁ ፡
ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባጀበል ፡
ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡
ባላምባራስ ፡ ማዛው ፡ ደስታ ፡
ቀኛዝማች ፡ ትእዛዙ ፡
ቀኛዝማች ፡ ንብለ ፡ ድንግል ፡
አቶ ፡ አወቀ ፡ ጣሰው ፡ (የዋንጫ ፡ ሰራ ዎች ፡ ሹም) ፡

ሀ

መምህር ፡ ዜና ፡
መምህር ፡ ፈቃዱ ፡
መምህር ፡ አካለ ፡ ወልድ ፡


ለ

አባ ፡ እንግዳ ፡
አባ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
መላከ ፡ ፀሐይ ፡ ደስታ ፡

መ

አባ ፡ መልኬ ፡
አባ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡

## በንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ።




በእልፍኝ ፡ ግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ፡ (በ፲፱፻፲ ፡ ዓ ፡ ም) ፡ ከንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ጋር ፡ በዙፋን ፡ መሰብ ።

ወይዘሮ ፡ ትሰሜ ፡ ዳርጌ ፡
ወይዘሮ ፡ ዘርፈሽዋል ፡ ወይፉ ፡
ወይዘሮ ፡ ፀሐይ ፡ ወርቅ ፡ ዳርጌ ፡
ወይዘሮ ፡ አሥለፈች ፡ ወንዴ ፡
ወይዘሮ ፡ ወለተ ፡ ዮሐንስ ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ።
ወይዘሮ ፡ ከፈይ ፡ ወሌ ፡
ወይዘሮ ፡ ሥሂን ፡ ሚካኤል ፡

፳

ከንግሥት ፡ ዙፋን ፡ በስተቀኝ ።

ወይዘሮ ፡ አጸደ ፡ አስፋው ፡
ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ወይዘሮ ፡ ንግሥት ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ወይዘሮ ፡ አማረች ፡ ዋለሉ ፡
ወይዘሮ ፡ የሻሽ ፡ ወርቅ ፡ ይልማ ፡
ወይዘሮ ፡ አልማዝ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፡
ወይዘሮ ፡ በላይነሽዋ ፡ አባጂቢር ፡
ወይዘሮ ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡ መንገሻ ፡
ወይዘሮ ፡ ትደንቂያለሽ ፡ ወልደጊዮርጊስ ፡

ወይዘሮ ፡ አስቴር ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፡
ወይዘሮ ፡ አልማዝ ፡
ወይዘሮ ፡ ገሠሠች ፡

፲፱

ወይዘሮ ፡ የአቦነሽ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
ወይዘሮ ፡ ጌጤነሽ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
ወይዘሮ ፡ አጸደ ፡ ኃይሉ ፡
ወይዘሮ ፡ አጸደ ፡ ገንሜ ፡
ወይዘሮ ፡ ጥሩ ፡ ወርቅ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
ወይዘሮ ፡ የሽዋ ፡ ጣይ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
ወይዘሮ ፡ አጸደ ፡ ተክለ ፡ ማርያም ፡
ወይዘሮ ፡ ልክምየለሽ ፡ በሻህ ፡
ወይዘሮ ፡ ጾጊ ፡ ዋለሉ ፡

፰

ወይዘሮ ፡ ብርሃኔ ፡ መንገሻ ፡ ዮሐንስ ፡
ወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ብርቅነሽ ፡ አደሀሉሽም ፡
ወይዘሮ ፡ ንግሥት ፡ ወለተገና ፡
ወይዘሮ ፡ ጉፉ ፡ ጌጿ ፡ አቅሌስ ፡
ወይዘሮ ፡ አስገደች ፡ ከበደ ፡

1

ከንግሥት ፡ ዙፋን ፡ በስተ ፡ ግራ ።
ከልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ጋር ።

ከቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ጥቅምዮም ፡ ከበደ ፡
ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡
ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡
ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፡
ራስ ፡ ጉግሣ ፡ አርአያ ፡
ራስ ፡ አባተ ፡ ቧ ፡ ያለው ፡
ደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡
ደጃዝማች ፡ ታዬ ፡ ጉልላቴ ፡

2

ከንግሥት ፡ ዙፋን ፡ በስተግራ ፡
ከልጋ ፡ ወራሽ ፡ ዙፋን ፡ ቀኝ ፡

ደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
ደጃዝማች ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡



## በንግሥት ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ የግብር ፡ አቀማመጥ ፡ ተራ ።

3

ከልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ በስተግራ ፡
ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻ ፡
ራስ ፡ ናደው ፡
ራስ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡
ደጃዝማች ፡ ተድላ ፡ አባ ፡ ጉበን ፡
ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡
ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡

፲፪

ወይዘሮ ፡ አጥረሽዋል ፡ ደምሰው ፡
ወይዘሮ ፡ ላቀች ፡ ደምሰው ፡
ወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ገበየሁ ፡
ወይዘሮ ፡ ዳርምየለሽ ፡ እንዳርጋቸው ፡
ወይዘሮ ፡ መነን ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡
ወይዘሮ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ ቡስሬ ፡
ወይዘሮ ፡ አስካለ ፡ ዋለሉ ፡
ወይዘሮ ፡ አስለፈች ፡ ሺበሺ ፡
ወይዘሮ ፡ መነን ፡ በሰሬ ፡

4

ንቡረዕድ ፡ አድማሱ ፡
አፈንጉሥ ፡ እስጢፋኖስ ፡

5

ደጃዝማች ፡ ከተማ ፡
ደጃዝማች ፡ ከፈተው ፡
ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡
ደጃዝማች ፡ ወሰኔ ፡ ትርፌ ፡
ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ለማ ፡
ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡
ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡
ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴ ፡
ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
ደጃዝማች ፡ መርዕድ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡
ደጃዝማች ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ናደው ፡
ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ደጃዝማች ፡ መታፈሪያ ፡
ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ አባጆበል ፡
ደጃዝማች ፡ ገድሌ ፡
ደጃዝማች ፡ ዙሰሬ ፡
አዛዥ ፡ ማዘው ፡

6

ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ ብሩ ፡
ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ይናዱ ፡
ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ወንድምአገኘሁ ፡ (ሊጋባ) ፡
ደጃዝማች ፡ ሺበሺ ፡ በያን ፡
ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ ወሰኔ ፡
ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፡
ደጃዝማች ፡ አስፋ ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡
ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ወሰን ፡ የለሽ ፡
ደጃዝማች ፡ ኀይለማርያም ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ደጃዝማች ፡ አበቸው ፡ ገሠሠ ፡
ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ተወንድ ፡ በላይ ፡
ደጃዝማች ፡ ደበበ ፡ እንዳርጋቸው ፡
ደጃዝማች ፡ ሥዩም ፡ ልዑል ፡ ሰገድ ፡
ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ውቤ ፡
ደጃዝማች ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡
ደጃዝማች ፡ አድማሱ ፡ ብሩ ፡
ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡

7

ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ ወልደ ፡ መስቀል ፡
ደጃዝማች ፡ እምሩ ፡ ሚካኤል ፡ ሀብተ ፡ ሥላሴ ፡
ደጃዝማች ፡ ተሰፉ ፡ ቅኑ ፡
ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ብሩ ፡
ጸሐፊ ፡ ትእዛዝ ፡ አፈወርቅ ፡

ሊቀ ፡ መኳስ ፡ መኰንን ፡ ዋልተንጉስ ፡
ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፡
በጅሮንድ ፡ ዘለቀ ፡ መታፈሪያ ፡
ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ተድላ ፡
አዛዥ ፡ ዛማኔል ፡
ፊታውራሪ ፡ ዘለቀ ፡ ተሰማ ፡
ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ ይመር ፡
በጅሮንድ ፡ ዘለቀ ፡ አግደው ፡
ደጃዝማች ፡ ግዛው ፡ ጀማ ፡
ደጃዝማች ፡ አቻምየለህ ፡
ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ወሰኔ ፡
በጅሮንድ ፡ ውብ ፡ እሸት ፡ ኃይሉ ፡

8

ከመጋረጃ ፡ ውጭ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጊዜ ፡ የሚጋበዙ ።
ፊታውራሪ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ ከተራ ፡

9

ፊታውራሪ ፡ ገብሬ ፡
ፊታውራሪ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡
ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ አባለች ፡
ቀኛዝማች ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ቀኛዝማች ፡ ኑጋሽ ፡ ጠንቁ ፡
ከንቲባ ፡ ወሰኔ ፡ ዛማኑኤል ፡
ቀኛዝማች ፡ ግዛው ፡ ደስታ ፡
ፊታውራሪ ፡ ይፍሩ ፡ በንት ፡ ይዳኝ ፡
ባላባራስ ፡ ብሩ ፡ መሸሻ ፡
ቀኛዝማች ፡ ደጀኑ ፡
ባላምባራስ ፡ በላይነህ ፡ ደባልቀው ፡
አዛዥ ፡ ዬዱ ፡
ቀኛዝማች ፡ ደስታ ፡ ወሰኔ ፡
ፊታውራሪ ፡ ኑጋ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡
መልአከ ፡ ገነት ፡ ወልደሃና ፡
ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ ሀብተ ፡ ማርያም ፡
ቀኛዝማች ፡ ሀምሩ ፡ ገብረ ፡ ሥላሴ ፡

10

አዛዥ ፡ ተሰማ ፡
ቀኛዝማች ፡ እሥራት ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (ፊታውራሪ) ፡
አዛዥ ፡ ወሰኔ ፡

11

ፊታውራሪ ፡ አበበ ፡ አስፋው ፡
ፊታውራሪ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡ ወ/ጊዮርጊስ ፡
ፊታውራሪ ፡ ካሣ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
ቀኛዝማች ፡ ዘመድ ፡ አገኘሁ ፡
ግራዝማች ፡ ገብረ ፡ ወልዴ ፡
አዛዥ ፡ ደሜ ፡
ግራዝማች ፡ አንደሼ ፡
ልጅ ፡ ሥዩም ፡ ደምሰው ፡
ባላምባራስ ፡ ደምስ ፡ አስፋው ፡
ግራዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ድል ፡ ነሣሁ ፡
ግራዝማች ፡ አየለ ፡ አስፋው ፡
ቀኛዝማች ፡ ኤሉስ ፡ ትኩ ፡
ቀኛዝማች ፡ አርኪ ፡ ጻድቅ ፡
ልጅ ፡ ግዛሉ ፡ ዋለሉ ፡
ልጅ ፡ ሥዩም ፡ ዋለሉ ፡

12

መጋረጃ ፡ ከተነሰነ ፡ በኋላ ።

ቀኛዝማች ፡ የሺነህ ፡
ልጅ ፡ በክሩ ፡ ሰበጋዲስ ፡
ቀኛዝማች ፡ ግዱ ፡ ወሰን ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ የኔዳው ፡
አቶ ፡ ሀብተ ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ አማኑ ፡
ልጅ ፡ እንግዳዊር ፡ ወልደየስ ፡
ልጅ ፡ አወላቸው ፡

ልጅ ፡ አሻግሬ ፡
ልጅ ፡ መንገሻ ፡ ባልቻ ፡
ልጅ ፡ ወርቁ ፡ ደስታ ፡
ልጅ ፡ ደምሴ ፡ ብሩ ፡ (ፊታውራሪ) ፡
ልጅ ፡ ገሠሠ ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ማርያ ፡ እንግዳው ፡
ልጅ ፡ ሥዩም ፡ ደምሰው ፡
ልጅ ፡ ክፈተው ፡ ደምሰው ፡
ልጅ ፡ ሙሉጌታ ፡ በንቲዋሉ ፡
ልጅ ፡ እስጢፋኖስ ፡ ብሩ ፡
ቀኛዝማች ፡ ሙላት ፡ ጎጋቱ ፡ አባ ፡ ሸኘው ፡
ባላምባራስ ፡ ብሩ ፡ የውኅቴ ፡
ልጅ ፡ ግዛለ ፡ ማርያም ፡ ተሰማ ፡
ልጅ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ይብሶ ፡
ልጅ ፡ ተሰማ ፡ አያኔ ፡
ልጅ ፡ ሙሴ ፡ ባልቻ ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ ገብረየስ ፡

13

አሳላፊ ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡
አሳላፊ ፡ ካሣዬ ፡ ግራዝማች ፡
ቀኛዝማች ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡

14

በጅሮንድ ፡ አጥናፉ ፡
በጅሮንድ ፡ አስፋው ፡
አቶ ፡ ተሰማ ፡ ወልዴ ፡
አቶ ፡ መታፈሪያ ፡ ደስታ ፡
አቶ ፡ ደበሙ ፡
አቶ ፡ የምድር ፡ ገነት ፡
ባሻ ፡ ከለች ፡
ባል ፡ ደራስ ፡ ገዛኸኝ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ፡
አቶ ፡ ኃይሌ ፡ ገሜ ፡ ሰረው ፡
ልጅ ፡ ደስታ ፡ አለሜ ፡
አቶ ፡ አደም ፡
አቶ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ጸሐፊ ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ሐዋርያት ፡ እንጀራ ፡ አሳላፊ ፡

15

አሳላፊ ፡ ኃይለ ፡ ኢየሱስ ፡
አቶ ፡ ወልደ ፡ ጻድቅ ፡
አቶ ፡ በየነ ፡
ኃይለ ፡ ማርያም ፡ አውግቸው ፡
አቶ ፡ አብቴ ፡ አውግቸው ፡

ሀ

መምሕር ፡ ደስታ ፡ አቡነአብርሃም ፡
መምሕር ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ ዜና ፡ ማርቆስ ፡
መላከ ፡ ፀሐይ ፡ ደስታ ፡

ለ

መሶብ ፡ በንግሥት ፡ ዘ ፡ ወ ፡ ጓዳ ፡ ውስጥ ፡

ልጅ ፡ ፍቅሬ ፡ ሥላሴ ፡ ከተማ ፡ (በጅሮንድ) ፡
ልጅ ፡ በየነ ፡ መርዕድ ፡ (ደጃዝማች) ፡
ልጅ ፡ ወርቁ ፡ ጃሌ ፡ ቀኛዝማች ፡
ልጅ ፡ ሥዩም ፡ ተሰማ ፡ (ግራዝማች) ፡
ልጅ ፡ ግዛው ፡ ጣይቱ ፡ ኑጓ ፡ ድራስ ፡
ልጅ ፡ ከበደ ፡ አድነው ፡

መ

መምሕር ፡ ጸሐይ ፡ የዝቋላው ፡
አለቃ ፡ ወልደ ፡ ተክሌ ፡
መምሕር ፡ ይርዳው ፡

ሰ

አባ ፡ አለሙ ፡
አባ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡

ጊዜም ፡ ሆነ ፡ በጦር ፡ ጊዜ ፡ ሳገልግሎቱ ፡ የልግም ፡ ጓዳ ፡ ሳያበጅለት ፡ በንጹሕ ፡ ሕሊና ፡ በቅንነት ፡ ያገለገለ ፡ ሲሆን ፡ ነው ። የክብር ፡ አቀማ መጥ ፡ የሚፈቀደውም ፡ ከሹመት ፡ ደረጃ ፡ ጋራ ፡ ነው ።

የፊታድም ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ እንደሚከተለው ፡ ነው ። ለምሳሌ ፡ ፊታውራሪ ፡ የነበረ ፡ አንድ ፡ ሰው ፡ ደጃዝማች ፡ ሲባል ፤ እንደዚሁም ፡ ደጃዝማች ፡ የነበረው ፡ ቢትወደድ ፡ ወይም ፡ ራስ ፡ ሲባልና ፡ ከቀድሞው ፡ ይሆታ ፡ ከፍ ፡ ሳለው ፡ አገር ፡ ሳስተዳዳሪነትና ፡ ለማዕርግ ፡ ተመርጦ ፡ ሲሾም ፡ ተሿሚው ፡ ሹመቱ ፡ በግልጥ ፡ ወደ ፡ ሚነገርበት ፡ ቦታ ፤ በነ ጋሪትም ፡ እንደ ፡ ሆነ ፡ ነጋሪት ፡ ወደ ፡ ሚመታበት ፡ አደባባይ ፡ ከመ ሄዱ ፡ በፊት ፡ በውስጥ ፡ ሳለ ፡ ይነገረዋል ።

ተሿሚው ፡ ሰው ፡ መጀመሪያ ፡ ይጠራና ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ሄዶ ፡ የሹ መት ፡ ማዕርግ ፡ ልብሱን ፡ በደንብ ፡ ለብሶ ፡ ይመጣል ፤ ከዚያም ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፡ ሊጋባውና ፡ ከመኳንንት ፡ አንድ ፡ ለዚህ ፡ ሥራ ፡ የተመደበ ፡ ሰው ፡ ሆነው ፡ እቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ለሹመት ፡ መንገሪያ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጀው ፡ ቦታ ፡ ወስደው ፡ ይነግሩታል ። ከዚያም ፡ በኋላ ፡ ነጋሪት ፡ ወደሚመታበት ፡ ቦታ ፡ ሄዶ ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ ተመልሶ ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ እጅ ፡ ለመንሳት ፡ ሲገባ ፡ የመቀመጫውን ፡ ደረጃ ፡ እልፍኝ ፡ አስከልካዩ ፡ አሳስቦ ፡ የክብሩ ፡ መጠበቅ ፡ በዚሁ ፡ ቀን ፡ ይጀመራል ፡ እንደዚሁም ፡ በማግሥቱ ፡ ሲመጣ ፡ የመሶብ ፡ ጓደኞቹን ፡ የሚቀላቀል በትና ፡ የፕሮቶኮሉ ፡ መግለጫ ፡ ቀን ፡ ይሆናል ።

የዚህን ፡ ፕሮቶኮል ፡ ማለት ፡ ያቀማመጡን ፡ ሥነ ፡ ሥርዓት ፡ የሚ ጠብቀው ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ ነው ። ሹመት ፡ በሚሰጥበት ፡ ጊዜ ፡ ግን ፡ የተሿሚዎችንም ፡ ሊስት ፡ ከጽሕፈት ፡ ሚኒስቴር ፡ ተቀብሎ ፡ የትዶም ፡ ተከተሉን ፡ ተራ ፡ በሊስቱ ፡ መሠረት ፡ ጠብቆ ፡ በአጋፋሪው ፡ አቅራቢነት ፡ እየተረዳ ፤ ተሿሚውን ፡ የሚጠራውና ፡ ሹመቱን ፡ ሊነግሩ ፡ ወደ ፡ ተዘጋጁትም ፡ ባለሥልጣኖች ፡ የሚያስገባው ፡ ሊጋባው ፡ ነው ። ሹመቱንም ፡ የሚነግሩት ፡ አንድ ፡ በማዕርግ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱ የቅርብ ፡ አማካሪ ፡ የሆነ ፡ መኳንንት ፡ ወይም ፡ ሚኒስትርና ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፡ ናቸው ። እነርሱም ፡ ከሊጋባው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ለተሿሚው ፡ ይነግሩታል ። የሹመቱንም ፡ ቃል ፡ የሚነግረው ፡ በንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ስም ፡ ሆኖ ፡ በተለይ ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፡ ነው ። ተሿሚውም ፡ ቃሉን ፡ ከሰማ ፡ በኋላ ፡ በትህትና ፡ ለጥ ፡ ብሎ ፡ መሬት ፡ ይስምና ፡ ሹመቱን ፡ ተቀብሎ ፡ ይቆያል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከሕዝብ ፡ ለማስተዋወቅ ፡ ነጋሪት ፡ ወደ ፡ ሚመታበት ፡ አደባባይ ፡ በመጀመሪያ ፡ አጋፋሪው ፡ ከዚያ ፡ ቀጥሎ ፡ ሊጋባና ፡ ጸሐፊ ፡ ትእዛዙ ፤ ከነሱም ፡ ቀጥሎ ፡ ተሿሚው ፡ ሆነው ፡ ይሄ



ዱና ፡ ከዚያ ፡ ሲደርሱ ፡ አዋጆችንና ፡ ሹመቶችን ፡ የመናገር ፡ መብት ፡ የተሰጠው ፡ የነጋሪት ፡ መችዎች ፡ አለቃ ፡ ከጽሕፈት ፡ ሚኒስትሩ ፡ እየተ ነገረው ፡ ለዘማ ፡ ባለ ፡ ድምፅ ፡ ለሕዝቡ ፡ ይነግራል ፤ ይህ ፡ ቃል ፡ የሚነገ ርበት ፡ ቦታ ፡ ከአደባባዩ ፡ በጣም ፡ ከፍ ፡ ባለ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከአሥር ፡ ሺህ ፡ የማያንስ ፡ ሕዝብ ፡ ተነግሮት ፡ አዋጁን ፡ ሰምቶ ፡ ይመለሳል ። ድምፅ ፡ ማጉያ ፡ ራዲዮ ፡ በብዙ ፡ ወሬ ፡ ማዳረሻ ፡ የዕለት ፡ ጋዜጣ ፡ በሌለ በት ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ አዋጁም ፡ ሆነ ፡ ሹመቱ ፡ ዕለቱን ፡ በከተማውም ፡ ሆነ ፡ በውጭ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ ተሰምቶ ፡ ያድራል ፤

እንደምን ፡ ተሰምቶ ፡ ያድራል ? የሚል ፡ ጠያቂ ፡ ቢኖር ፡ የሚሰማ በትን ፡ ምክንያት ፡ እንገልጻለን ። በከተማ ፡ ያለው ፡ ነጋሪት ፡ ሲመታ ፡ እስከ ፡ ሁለት ፡ ሦስት ፡ ሰዓት ፡ ስለሚቆይ ፡ ነጋሪት ፡ ወጥቷል ፡ ሲል ፡ ሕዝቡ ፡ ከያለበት ፡ ተጠራቅሞ ፡ አደባባዩን ፡ ይሞላዋል ። አዋጁን ፡ ከሰማ ፡ በኋላም ፡ በየሠፈሩ ፡ ስለሚሠራጭ ፡ ወዲያው ፡ ወሬው ፡ ይዳረ ሳል ፤ እንደዚሁም ፡ በየዳር ፡ አገሩና ፡ በየጠቅላይ ፡ ግዛቶች ፡ የመንግ ሥቱ ፡ ደንበኛ ፡ ስልከኛ ፡ ስላለ ፡ ከአዋጁ ፡ በኋላ ፡ ወዲያውኑ ፡ በስልክ ፡ ያስተላልፈዋልና ፡ ዕለቱን ፡ ተሰምቶ ፡ ያድራል ። የተባለው ፡ ስለዚህ ፡ ነው ። በዚያ ፡ ጊዜ ፡ ስልክ ፡ ያልገባለት ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ አልነበረም ።


## የማዕርግ ፡ ልብስና ፡ ሽልማት ፤

ከዳግማዊ ፡ ምኒልክ ፡ ሲያያዝ ፡ መጥቶ ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ከዚያም ፡ በቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ዘመነ መንግሥት ፡ እስከ ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የነበረው ፡ የሹመትና ፡ የሽልማት ፡ ልብስ ፡ ከታች ፡ ወደ ፡ ላይ ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተውን ፡ ማዕረግ ፡ እየተከተለ ፡ ያድጋል ።

ለአቀራረብ ፡ እንዲመች ፡ ይህ ፡ የማዕረግ ፡ ሥርዓት ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሽልማትና ፡ በወታደር ፡ ሹመት ፡ ሆኖ ፡ በሁለት ፡ ሊከፈል ፡ ይችላል ። በመሠረቱ ፡ ግን ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ተሸላሚ ፡ ከቤተ ፡ መን ግሥት ፡ ወደ ፡ ወታደር ፡ ሹመት ፡ መተላለፉ ፡ የታወቀና ፡ የተለመደ ፡ ነገር ፡ ነው ።

## የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሽልማት ፤

፩ኛ ፤ ሀ ፤ የጨዋ ፡ ልጅ ፡ ሆኖ ፡ በባለሟልነትና ፡ በእልፍኝ ፡ አሽከርነት ፡ ሲያገለግል ፡ በአገልግሎቱ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ሽልማት ፡ በሚያገ ኝበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ነጭ ፡ መርዶፋ ፡ ሱሪ ፡ ኩታ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ቀሚስ ፡ ነው ።



የቀድሞውን ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ ለብሰው ፡ ከግራ ፡ ወደ ፡ ቀኝ ፡ ደጃዝማች ፡ ተፈሪ ፡ መኰንን ፡ ዛሬ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፤ አቤቶ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱ ፤ ደጃዝማች ፡ ብሩ ፡ ወልደ ገብርኤል ፡ (ራስ) ፡ ናቸው ።





ይህ ፡ ሥዕል ፡ የሚያሳየው ፡ በአዲሱ ፡ ዘመን ፡ ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ በጃንሆይ ፡ የድል ፡ በዓል ፡ ቀን ፡ በተሻሻለው ፡ በአዲስ ፡ የጦር ፡ ልብስ ፡ የተነሡት ፡ ሲሆን ፡ ከቀኝ ፡ ልዑል ፡ የኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ አልጋወራሽ ፡ መርዕድ ፡ አዝማች ፡ አስፋወሰን ፡ ብግራ ፡ የመከላከያ ፡ ሚኒስትሩ ፡ ሌ/ጄኔራል ፡ መርዕድ ፡ መንገሻ ፡ ናቸው ።

ለ ፤ አገልግሎቱን ፡ ሳያሳድፍ ፡ ከፍ ፡ ሲል ፡ መብሩቅ ፡ ስሪ ፡ ቀጭን ፡ ኩታ ፡ ሐር ፡ ቀሚስ ፡ በወርቅ ፡ ገመድ ፡ እጅጌውና ፡ አንገቱ ፡ የተሰፋበት ፡ ሆኖ ፡ ይሸለማል ።

ሐ ፡ ባገልግሎቱ ፡ ደስ ፡ አሰኝቶ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ የሹመት ፡ ደረጃ ፡ ሳያገኝ ፡ በባለሟልነቱ ፡ የሚሸለም ፡ ሲሆን ፡ ማለፊያ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ቀሚስ ፡ በወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ አንገቱና ፡ እጅጌው ፡ የተሰፋ ፡ ሆኖ ፡ ሐር ፡ ጃኖ ፡ ጭምር ፡ ይሸለማል ።

መ ፤ ከዚህ፡ በላይ ፡ የተጻፈውን ፡ የማዕረግ ፡ ዕድገት ፡ ካገኘ ፡ በኋላ ፡ ያለው ፡ ሽልማት ፡ እንደሌላው ፡ ሁሉ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ልዩነት ፡ አይኖረውም ።

## የወታደር ፡ ሹመት ፤

፸፫ ፤ ሀ ፡ የወታደር ፡ አገልግሎት ፡ በ፶ ፡ አለቃ ፡ ይጀምራል ፤ የልብሱም ፡ ዓይነት ፡ መደቡ ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ቀለሙ ፡ ወደ ፡ ብጫነት ፡ የሚያደላ ፡ አብደላ ፡ ካኔ ፡ ከተባለው ፡ የጨርቅ ፡ ዓይነት ፡ ነው ። በሚሸለምበት ፡ ወይም ፡ በሚሾምበት ፡ ጊዜ ፡ የሚሰጠው ፡ ነጭ ፡ መርዶፋ ፡ ስሪ ፡ ኩታ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ። መደረቢያ ፡ የለውም ።

ለ ፤ ወታደር ፡ የመቶ ፡ አለቃ ፡ ሲሆን ፡ መደቡ ፡ ቀጭን ፡ የሆነ ፡ ከሃምሳ ፡ አለቃው ፡ ቀሚስ ፡ ልዩነት ፡ ያለው ፡ ሆኖ ፡ አብደላ ፡ ካኒ ፡ ቀሚስ ፡ ነው ። ባለሐር ፡ ጥልፍ ፡ ለምድ ፡ መደረቢያ ፡ አለው ።

ሐ ፤ ሻምበል ፡ መደቡ ፡ ከመቶ ፡ አለቃው ፡ ጥቂት ፡ ሰፋ ፡ ያለ ፡ ሆኖ ፡ አብደላ ፡ ካኒ ፡ ቀሚስ ፡ በቀጭን ፡ ወርቅ ፡ ገመድ ፡ እጅጌውና ፡ አንገቱ ፡ ላይ ፡ የተሰፋበት ፡ ሆኖ ፡ አጥላስ ፡ ካባ ፡ እንደ ፡ ቀሚሱ ፡ በቀጭን ፡ ወርቅ ፡ ገመድ ፡ የተሰፋበት ፡ ሆኖ ፡ ወይም ፡ ሐር ፡ ጥልፍ ፡ ሆኖ ፡ ባለ ፡ ጉባጉብ ፡ ለምድ ፡ ይሸለማል ፤ ባለሙጣ ፡ ጐራዴ ፤ ጣፋ ፡ ጋሻም ፡ ይሰጠዋል ።

መ ፤ ሻምበል ፡ በሻምበልነቱ ፡ እንዳለ ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ የሚሰጠው ፡ ሲሆን ፡ ባላምባራስ ፡ የሆነ ፡ እንደሆነ ፡ ልብሱ ፡ አይለወጥም ፡ ግራዝማች ፡ የተባለ ፡ እንደሆነ ፡ የወርቅ ፡ ገመድ ፡ የነበረው ፡ በካባና ፡ በቀሚስ ፡ ላይ ፡ የወርቅ ፡ ጥብብ ፡ ይሰፋበታል ። የቀረው ፡ እንዳለ ፡ ነው ።



ሠ ፤ ሻለቃ ፡ ሆነው ፡ ቀኛዝማች ፡ ግራዝማችም ፡ የሚባሉ ፡ ስለ ፡ ሚኖሩ ፡ ሻለቃ ፡ ለመሆናቸው ፡ በቀሚሱና ፡ በካባው ፡ ላይ ፡ ከወደውስጥ ፡ የወርቅ ፡ ገመድ ፡ ተሰፍቶ ፡ ከወደፊቱ ፡ የወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ ይሰፋበታል ። ጐራዴ ፡ ከነሙጣው ፤ ጣፋ ፡ ጋሻ ፡ ይሸለማል ፤ የጋሻውም ፡ የጐራዴውም ፡ ጌጥ ፡ ከሻምበሉ ፡ ልዩነት ፡ አለው ።

ረ ፤ ፊታውራሪ ፡ ሲባል ፡ ከውስጥ ፡ የሐር ፡ ጥልፍ ፡ ሰገጥ ፡ ከግንባሩ ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ በቀሚሱና ፡ በካባው ፡ ላይ ፡ ይሰፋበታል ። ከላይና ፡ ከታች ፡ ዳር ፡ ዳሩን ፡ ጥበብ ፡ የተሠራበት ፡ ሐር ፡ ጃኖ ፤ ጐራዴ ፡ ከነሙጣው ፤ ጣፋ ፡ ጋሻ ፡ ይሸለማል ።

ተሸላሚው ፡ የረጅም ፡ ጊዜ ፡ አገልግሎት ፡ ያለው ፡ ሲሆን ፡ በሐር ፡ ጃኖው ፡ ቦታ ፡ ድርብ ፡ ይሆናል ፡ ባለ ፡ ወርቅ ፡ ጥልፍ ፡ ለምድ ፡ ጎፈርም ፡ ሊሸለም ፡ ይችላል ። አሠራሩ ፡ ግን ፡ የካባውን ፡ ሁኔታ ፡ የተከተለ ፡ ነው ። ጐራዴ ፡ ሲሸለም ፡ ደበላ ፡ ድግ ፡ አብሮ ፡ ይሰጣል ፤ ባለሐር ፡ ጥልፍ ፡ የበቅሎ ፡ ዕቃ ፡ በቅሎ ፡ ከነሥርዓቱ ፡ የብር ፡ አልቦ ፡ ፈረስ ፡ ከነመጣብሩ ።

ሰ ፤ የሊቀመኳስ ፡ ሽልማት ፡ ካባና ፡ ቀሚሱ ፡ ሌላውም ፡ ሽልማት ፡ በሙሉ ፡ በደጃዝማቾች ፡ ዐይነት ፡ ሲሆን ፡ በላንቃው ፡ ልዩነት ፡ አለው ፡ ይኸውም ፡ በውስጥ ፡ በካባ ፡ ዐይነት ፡ የተሰፋ ፡ ወርቅ ፡ ዘቦ ፡ ለብሶ ፡ በዚያ ፡ ላይ ፡ ላንቃ ፡ ይደረባል ፤ በራሱም ፡ ላይ ፡ አረንጓዴ ፡ ማሰሪያ ፡ ያስራል ፡ ስሪውም ፡ ወይን ፡ ጠጅ ፡ ከፋይ ፡ ይሆናል ።

ሸ ፡ ደጃዝማች ፡ ሲባል ፡ ቀሚሱ ፡ በብርና ፡ በወርቅ ፡ ሰገጥ ፡ ይጠለፍና ፡ መከፈፈያው ፡ ሁለት ፡ የወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ ይሰፋበታል ፤ መብሩቅ ፡ ስሪ ፤ ፩ ፡ ጣቃ ፡ ሻሽ ፡ ለድግ ፤ ዝናር ፡ ጐራዴ ፤ ድርብ ፡ ካባ ፤ ላንቃ ፤ ማለፊያ ፡ ጠመንጃ ፤ ጣፋ ፡ ጋሻ ፤ በማግሥቱ ፡ የሚለበስ ፡ በቀሚስ ፡ ዓይነት ፡ የተጠለፈ ፡ አንድ ፡ ካባ ፤ በቅሎ ፡ ከነሥርዓቱ ፤ የሐር ፡ ጥልፍ ፡ መረሻት ፤ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ቅልቅል ፡ የሆነ ፡ አልቦ ፡ ባለብር ፡ መጣብር ፡ ፈረስ ፡ ፩ ፡ ጦር ፡ ነጭ ፡ ጥላ ፡ ይሰጣል ።

ቀ ፤ የሻለቃ ፡ ደጃዝማች ፡ በብርና ፡ በሐር ፡ ጥልፍ ፡ የተለጠፈ ፡ ላንቃ ፡ ካባው ፡ እንደዚሁ ፡ በሐርና ፡ በብር ፡ የተጠለፈ ፡ ሆኖ ፡ ደረጃው ፡ ከመንግሥቱ ፡ ደጃዝማች ፡ ለየት ፡ ያለ ፡ ነው ። የሻለቃ ፡ ደጃዝማች ፡ የሚባለውም ፡ ከንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ መንግሥት ፡ የሚሾም ፡ ሳይሆን ፡ ንጉሥ ፡ ተብሎ ፡ የሚሾመውና ፡ ራስ ፡ ተብሎ ፡ የሚሾመው ፡ ደጃዝማች ፡ የሚያሰኘውን ፡ ሹመት ፡ እንዲሾም ፡ የተፈቀደ ፡ ስለሆነ ፡ እነሱ ፡ የሚሾሙት ፡ ነው ።

## ከፍተኛ ፡ ሽልማትና ፡ ማዕረግ ፤

፫ ፤ ሀ/ ቢትወደድ ፡ ሲባል ፡ ልብሱ ፡ በሙሉ ፡ እንደራሶች ፡ ሆኖ ፡ የራስ ፡ ወርቅ ፡ ብቻ ፡ አይሸለምም ፤

ለ/ ራስ ፡ ሲባል ፡ በወርቅ ፡ ሰገጥ ፡ የተጠለፈ ፡ በጥንድ ፡ ወርቅ ፡ ጥብጣብ ፡ የተከፈፈ ፡ ቀሚስ ፤ ሐር ፡ ድግ ፤ ዝናር ፤ ባለወርቅ ፡ ሙጣ ፡ ጐራዴ ፤ በትከሻው ፡ ላይ ፡ መደረቢያ ፡ ያለበት ፡ የወርቅ ፡ ላንቃ ፤ በራሱ ፡ ላይ ፡ አረንጓዴ ፡ ማሰሪያ ፡ አስሮ ፡ ራስ ፡ ወርቅ ፡ ያደረጋል ። ማለፊያ ፡ ጠመንጃ ፤ ወርቅ ፡ ጣፋ ፡ ጋሻ ፤ በቀሚሱ ፡ ዓይነት ፡ የተሰፋ ፡ በማግሥቱ ፡ የሚለበስ ፡ ክብ ፡ ወይም ፡ ባለኳስ ፡ ካባ ፤ ባለብርና ፡ ወርቅ ፡ ጥልፍ ፡ የወርቅ ፡ አልቦ ፤ ባለብር ፡ ጉብጉብ ፡ ሐር ፡ ጥልፍ ፡ መረሻት ፡ የተሚነ ፡ በቅሎ ፤ ባለወርቅ ፡ መጣብር ፡ የተሚነ ፡ ፈረስ ፤ ጥንድ ፡ ጦር ፤ አረንጓዴ ፡ ጥላ ፡ ይሸለማል ።

ሐ/ ሴት ፡ ወይዘሮዎችም ፡ የወርቅና ፡ የሐሩ ፡ ጥልፍ ፡ በቀሚሱ ፡ ላይ ፡ የሚጠለፈው ፡ በባላቸው ፡ ማዕረግ ፡ ዐይነት ፡ ወይም ፡ በትውልዳቸው ፡ ከፍተኛነት ፡ የወንድ ፡ መኰንኖች ፡ በሚሸለሙበት ፡ ከጐራዴ ፤ ከጋሻው ፤ ከጠመንጃው ፡ በስተቀር ፡ በልብሱ ፡ በኩል ፡ ልዩነት ፡ የሌለው ፡ ነው ። በቀሚሱ ፡ ጨርቅ ፡ ዐይነት ፡ ግን ፡ የወንዱ ፡ አብደላ ፡ ካኔ ፡ ሲሆን ፡ የሴቲቱ ፡ ነጭ ፡ ሐር ፡ ሆኖ ፡ ለከፍተኞችና ፡ ለዝቅተኞች ፡ የሐሩ ፡ ጥራት ፡ ልዩነት ፡ ይኖረዋል ።

መ/ የአንበሳ ፡ ጎፈር ፤ አንፋሮ ፤ አቁዳማድሪ ፤ ቢተዋ ፡ በተጨማሪ ፡ እንደጀግንነቱ ፡ ጌጡ ፡ ማዕረጉን ፡ ሳይለቅ ፡ የሚሸለም ፡ ነው ።

በቤተ ፡ መንግሥት ፡ ዕድገት ፡ ያገኘ ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ለወታደር ፡ ሹመት ፡ ተመርጦ ፡ በከፍተኛ ፡ ደረጃ ፡ የጦር ፡ አዛዥ ፡ ሊሆን ፡ መቻሉ ፡ ከላይ ፡ ተገልጿል ።

# ምዕራፍ ፡ ፲፩ ።

## ኢትዮጵያ ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ የማይጨው ፡ ጦርነት ።

ጠላታችን ፡ ኢጣልያ ፡ ፋሽስት ፡ ሀገራችንን ፡ ኢትዮጵያን ፡ በግልጥ ፡ በግፍ ፡ መውረር ፡ የጀመረችው ፡ በ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ መስከረም ፡ ፳፫ ፡ ቀን ፡ ነው ። ኢትዮጵያን ፡ ጠላት ፡ ኢጣልያ ፡ ለመውረርና ፡ የጊዜውንም ፡ ድል ፡ ልታገኝ ፡ የቻለችው ፡ በዚህ ፡ በተጠቀሰው ፡ ዘመን ፡ በተነሳው ፡ የጦርነት ፡ ኃይል ፡ ብቻ ፡ ሳይሆን ፡ ቀደም ፡ ብላ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ውስጥ ፡ ባቋቋመቻቸው ፡ የዲፕሎማቲክ ፡ ሠራተኞችና ፡ሚሲዮናዊያኖች ፡ አማካይነት ፡ የሀገሪቱን ፡ ታላላቅ ፡ ሰዎች ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ በማጋጨትና ፡ በማጣላት ፡ ኃይል ፡ እንዲቀነስ ፡ ታደርግ ፡ በነበረው ፡ የተንኰል ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ይህ ፡ የታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ የተጀመረው ፡ ለወደፊት ፡ መታረሚያ ፡ ለማድረግ ፡ ይጠቅም ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ስለሆነ ፡ ደራሲው ፡ ይሉኝታ ፡ ከፊቱ ፡ እንዲጠፋለት ፡ እየጸለየ ፡ የተሰማውን ፡ ፍሬ ፡ ነገር ፡ ብቻ ፡ ሲገልጽ ፡ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በስህተትና ፡ በተንኰል ፡ የተፈጸሙትን ፡ አንዳንድ ፡ ነገሮች ፡ እንዲገልጽ ፡ ይገደዳል ።

ሀ/ እያለፍናቸው ፡ በመጣነው ፡ ጽሑፎች ፡ ውስጥ ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ባለመግባባት ፡ ይሠራ ፡ የነበረውን ፡ እያስረዳን ፡ መጥተናል ፤ ለምሳሌ ፡ ያህል ፡ በቢገምድር ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ባላባትና ፡ ገዢ ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ በጠላት ፡ ስብከትና ፡ ተንኰል ፡ ተታለው ፡ በመንግሥታቸው ፡ ላይ ፡ አምጸው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ጦር ፡ ታዝዞ ፡ ተዋግተው ፡ በገዛ ፡ ጥፋታቸው ፡ በጦሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ስለሞቱ ፡ የቢጌምድርና ፡ የየጁ ፡ ባላባቶች ፡ ባላባታችን ፡ ሞቱብን ፡ በሚል ፡ ምክንያት ፡ ለመንግሥት ፡ የልብ ፡ ወዳጅና ፡ ታማኝ ፡ ሆነው ፡ ስላልተገኙ ፡ በመጀመሪያው ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ የታወቀውን ፡ የጥንት ፡ ጀግንነታቸውን ፡ እንዳልሠሩበት ፡ ታውቋል ፤ በኋላ ፡ ግን ፡ በአርበኝነት ፡ ነገሩ ፡ ከገባቸው ፡ በኋላ ፡ ጠላትን ፡ እንዳሰቃዩት ፡ እርግጠኛ ፡ ነው ።

ለ/ ጐጃምም ፡ እንደዚሁ ፡ ጠቅላይ ፡ ገዢና ፡ ባላባቱ ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ እንዲያመልጡ ፡ በማድረግ ፡ ረድተዋል ፡ ተብለው ፡ ተከሰው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ነገሩ ፡ እውነት ፡ ሆኖ ፡ በመገኘቱ ፡ በጥፋታቸው ፡ ተፈርዶባቸው ፡ የነበረው ፡ የሞት ፡ ፍርድ ፡ በእሥራትና ፡ ሀብትን ፡ በመውረስ ፡ እንዲቀጡ ፡

ተለውጠላቸው ፡ በእስር ፡ ቤት ፡ ተቀምጠው ፡ ነበር ፡ ስለ ፡ ዚህና ፡ ሌሎችም ፡ እነ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ በለው ፡ እነ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታምራት ፡ የሚባሉት ፡ ለጠላት ፡ ተንኰል ፡ መሣሪያ ፡ የሆኑ ፡ ሰዎች ፡ በተሜኑት ፡ ተንኰል ፡ መርተወት ፡ በራስ ፡ እምሩ ፡ መሪነት ፡ ዘምቶ ፡ የነበረው ፡ የጐጃም ፡ ጦር ፡ ከልቡ ፡ አስቦ ፡ ጠላትን ፡ ሊወጋ ፡ ያልፈለገ ፡ ነበርና ፡ ለጊዜው ፡ የዘመተ ፡ መስሎ ፡ ከተጓዘ ፡ በኋላ ፡ ከጦሩ ፡ ግምባር ፡ ላይ ፡ በመክዳት ፡ የተመለሰ ፡ ነው ።

በልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለ ፡ ሃይማኖት ፡ ላይ ፡ የተሰጠው ፡ ፍርድ ፡ ከተነሳ ፡ ዘንድ ፡ የፍርዱን ፡ አፈጻጸምና ፡ በጊዜውም ፡ የደረሰውን ፡ ሁኔታ ፡ ከዚህ ፡ በሚከተለው ፡ መሥመር ፡ ገልጫዋለሁ ።

ልጅ ፡ ኢያሱ ፡ በመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ የታሠሩት ፡ ኰረማሽ ፡ መሆኑ ፡ በምዕራፍ ፡ ፫ ፡ እንደተገለጸው ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ወደፍቼ ፡ ተዛውረው ፡ በልዑል ፡ ራስ ፡ካሣ ፡ ኃይሉ ፡ ጠባቂነት ፡ እንዲታሠሩ ፡ ተደርጎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ልጅ ፡ ኢያሱን ፡ ከታሰሩበት ፡ ከፍቼ ፡ እንዲወጡ ፡ በተደረገው ፡ ሽንጎ ፡ ውስጥ ፡ በመገኘታቸው ፡ መታሠራቸውንና ፡ እፍርድ ፡ ችሎት ፡ ቀርበው ፡ ሞት ፡ ከተፈረደባቸው ፡ በኋላ ፡ የሞቱ ፡ ፍርድ ፡ በእሥራትና ፡ ሀብት ፡ በመወረስ ፡ ተለውጦ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ የፍርዱን ፡ መሻሻል ፡ ለልጃቸው ፡ ለወይዘሮ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ ኃይሉ ፡ እንድነግር ፡ ተልኬ ፡ የነገርኋቸው ፡ እኔ ፡ ነኝ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ወይዘሮ ፡ ሰብለ ፡ ወንጌል ፡ የነበሩት ፡ አጎታቸው ፡ ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻ ፡ ቤት ፡ ነበር ። መልክቱንም ፡ በነገርኋቸው ፡ ጊዜ ፡ ሞቱ ፡ በዕሥራት ፡ ስለመለወጡ ፡ በጣም ፡ ደስ ፡ ብሏቸው ፡ እሳቸው ፡ ካሉበት ፡ ከልፍኝ ፡ እልልታው ፡ ተጀመረና ፡ በፎቁ ፡ በረንዳ ፡ ብቅ ፡ ሲሉ ፡ በውጭ ፡ በትጥር ፡ ያለው ፡ ሥራ ፡ ቤት ፡ ሁሉ ፡ እልልታውን ፡ አቀለጠው ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እመቤት ፡ ሆይ ፡ ዓለም ፡ ፀሐይ ፡ እያሱ ፡ ገና ፡ ባል ፡ ያላገቡ ፡ ልጅ ፡ አገረድ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ እዚያው ፡ ከናታቸው ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ የደስታው ፡ ተካፋይ ፡ ሆነዋል ።

ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ ቤቱን ፡ እንደራሴ ፡ አሽከሮቻቸው ፡ ቀኛዝማች ፡ መርሻና ፡ ቀኛዝማች ፡ ይመር ፡ እንዲጠብቁ ፡ ነግሬ ፡ ልጅ ፡ ዮሐንስ ፡ ኃይሉን ፡ ይዤ ፡ እንድመጣ ፡ ተላክሁ ፡ እቤታቸው ም ፡ እንደደረስሁ ፡ ሁሉቱን ፡ ሹሞቻቸውን ፡ አገኘሁና ፡ ለነሱ ፡ ስለ ፡ ጥበቃው ፡ መልክቱን ፡ ነግሬ ፡ ልጅ ፡ ዮሐንስ ፡ ኃይሉ ፡ ያለበትን ፡ ጠይቄ ፡ ወዳለበት ፡ ክፍል ፡ አደረሱኝና ፡ ወደ ፡ ግቢ ፡ መጠራቱን ፡ ነግሬ ፡ ይዤ ፡ ስሄድ ፡ ከልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ ነበሩና ፡ እሱን ፡ እንዳመጣ ፡ አልታዘዝኩም ፡ ነበርና ፡ ትቼው ፡ ሄድኩ ። ልጅ ፡ ዮሐንስም ፡ ከግቢ ፡ ሲደርስ ፡ ለጊዜው ፡



የሚያርፍበት ፡ ቦታ ፡ ተደረገለትና ፡ ቆይቶ ፡ ወዲያው ፡ በገሙ ፡ ጎፋ ፡ ግዛት ፡ አገር ፡ ተሰጠውና ፡ እንዲሄድ ፡ ተደረገ ። ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ ግን ፡ ምንም ፡ ሳያገኘው ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥትም ፡ እየመጣ ፡ አደባባይ ፡ እየዋለ ፡ ይመለስ ፡ ነበር ። ከዕለታት ፡ ባንደኛው ፡ ቀን ፡ ዕታላቁ ፡ አዳራሽ ፡ ግብር ፡ ሆኖ ፡ ልጅ ፡ ማሞ ፡ ኃይለ ፡ ሚካኤል ፡ በግብሩ ፡ ጊዜ ፡ በራስጌ ፡ በኩል ፡ ገብቶ ፡ ምሳውን ፡ ተጋብዞ ፡ ነበር ። ምሳውን ፡ በልቶ ፡ ካበቃ ፡ በኋላ ፡ መጋረጃ ፡ ተገልጦ ፡ በግንባር ፡ የሚገባው ፡ አዛውንት ፡ በሚጋበዝበት ፡ ጊዜ ፡ በዙፋኑ ፡ በስተቀኝ ፡ በራስጌ ፡ በኩል ፡ በግንባር ፡ ወደ ፡ ግብገዮው ፡ የሚገባውን ፡ አዛውንት ፡ በምንመለከትበት ፡ ጊዜ ፡ አብረን ፡ ቆመን ፡ ሳለ ፡ አንድ ፡ ጥያቄ ፡ ጠየቀኝ ፡ ጥያቄውም ፡ እንደዚህ ፡ የሚል ፡ ነበር ፤ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በተያዙ ፡ ጊዜ ፡ እኛ ፡ ቤት ፡ መጥተው ፡ ልጅ ፡ ዮሐንስን ፡ ይዘው ፡ ሲሄዱ ፡ እኔን ፡ ጥለውኝ ፡ የሄዱት ፡ ለምንድነው ፡ ብሎ ፡ ጠየቀኝ ፡ እኔም ፡ ባንተ ፡ ላይ ፡ እምነት ፡ ስለ ፡ ተጣለብህ ፡ እንድጠራህ ፡ ባለመታዘዜ ፡ ነው ፡ አልኩት ፤ እሱም ፡ አይደለም ፡ ነገሩ ፡ ገብቶኛል ፡ በመናቁ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ።

ከዚህ ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ታስረው ፡ ሊቀመጡ ፡ የተወሰነው ፡ አሩሲ ፡ በደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ግዛት ፡ ስለሆነ ፡ ከደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ጋራ ፡ ወደ ፡ አሩሲ ፡ ሲሄዱ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ የሚገኘው ፡ ቤታቸውና ፡ በቤታቸው ፡ የሚገኘው ፡ ሀብታቸው ፡ እንደራሴ ፡ የነበሩት ፡ ቀኛዝማች ፡ መርሻና ፡ የንብረቱ ፡ ሃላፊ ፡ የነበሩት ፡ ቀኛዝማች ፡ ይመር ፡ እንዳሉ ፡ በውስጥ ፡ እንዲሠሩ ፡ ተደርጎ ፡ በበላይ ፡ ሆነው ፡ ሀብቱን ፡ እንዲመዘግቡና ፡ እንዲጠብቁ ፡ ልጅ ፡ መስፍን ፡ ቀለመወርቅና ፡ ባላምባራስ ፡ እማኙ ፡ ይመር ፡ ታዘው ፡ እንዲጠብቁ ፡ ሲደረግ ፡ የጐጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ አስተዳደር ፡ ለልዑል ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ተሰጠ ።

ልዑል ፡ ራስ ፡ እምሩም ፡ ወደ ፡ ተሾሙበት ፡ ጎጃም ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ከመሄዳቸው ፡ በፊት ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ ደርሰው ፡ ለመምጣት ፡ ስለሄዱ ፡ ለጊዜው ፡ ያስተዳደሩን ፡ ሥራ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቢ ፡ ደረሰ ፡ በጥብቅነት ፡ እየሠሩ ፡ እንዲቆዩ ፡ ለሀብቱና ፡ ለንብረቱ ፡ እየመዘገቡ ፡ እንዲጠብቁ ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ያየህ ፡ ይራድ ፡ ከብዙ ፡ የሥራ ፡ ልምድ ፡ ካላቸው ፡ ሰዎች ፡ ጋራ ፡ ታዘው ፡ ሄደው ፡ ሥራ ፡ በጀመሩበት ፡ ጊዜ ፡ እኔም ፡ በዚያ ፡ ጊዜ ፡ የግምጃ ፡ ቤት ፡ የጌጥና ፡ የሽልማት ፡ ዲሬክተር ፡ ስለ ፡ ነበርኩ ፡ የዕቃውን ፡ ሁኔታ ፡ እንድመለከት ፡ ከግርማዊነታቸው ፡ ታዝዤ ፡ ሚሽካ ፡ ባብቼፍ ፡ በአውሮፕላን ፡ እንዲወስደኝ ፡ ታዞ ፡ በአየር ፡ መንገድ ፡ ሄጄ ፡ ነበርና ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ግምጃ ፡ ቤቱንና ፡ በውስጡ ፡ ያለውን ፡ ዕቃ ፡ አንድ ፡ ባንድ ፡ ጐበኘቻለሁ ።



ልዑል ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

ስለ ፡ ዕቃና ፡ ስለ ፡ ገንዘብ ፡ አቀማመጥ ፡ ስመለከት ፡ በጣም ፡ ይገርመኝ ፡ ነበር ። ይገርመኝ ፡ ነበር ፡ ያልኩትም ፡ ምክንያት ፡ የዕቃው ፡ አቀማመጥ ፡ መልክ ፡ ያልያዘ ፡ አንዱ ፡ ባንዱ ፡ ላይ ፡ የተነባበረ ፡ ማረሻና ፡ ብር ፡ ወርቅና ፡ ሽንኩርት ፡ ዝንጅብል ፡ ሳይለያዩ ፡ በያንዳንዱ ፡ ዕቃ ፡ ላይ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ ይታይ ፡ ስለነበረ ፡ ነው ። በዚህም ፡ ጊዜ ፡ የግምጃ ፡ ቤቱን ፡ ኃላፊ ፡ አታፍርም ፡ ወይ ፡ የዚህን ፡ ዓይነት ፡ የዕቃ ፡ አቀማመጥ ፡ ምን ፡ ሥራ ፡ ነው ፡ ብለህ ፡ ይዘኸዋል ፡ ብዬ ፡ በቅርብ ፡ ጠቅሼ ፡ ዕቃውን ፡ እያሳየሁ ፡ የጠየቅሁት ፡ በየቁና ፡ ላይ ፡ ወርቅና ፡ ሽንኩርት ፡ እንደዚሁም ፡ ዝንጅብል ፡ እየተቀላቀሉ ፡ የተቀመጡበትን ፡ በማሳየት ፡ ነበር ። እሱም ፡ እንዲህ ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ፡ በደንብ ፡ መልክ ፡ ሰጥቶ ፡ ማስቀመጡ ፡ ሳያቅተን ፡ ልዑል ፡ በገቡበት ፡ ጊዜ ፡ ያስቀመጡት ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ለምልክት ፡ አስቀምጠውት ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ እንዳስቀመጡት ፡ እንዲያገኙት ፡ ብለን ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ መለሰልኝ ። የዕቃው ፡ ዐይነት ፡ ግን ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ኤውሮፓ ፡ በሄዱ ፡ ጊዜ ፡ ገዝተው ፡ ያመጡት ፡ መጠን ፡ የሌለው ፡ ሰዓት ፡ ሽቶ ፡ የገላ ፡ ሳሙና ፡ ሌላም ፡ ይህን ፡ የመሳሰለው ፡ ሁሉ ፡ በሻንጣ ፡ እንደ ፡ ተቆለፈ ፡ ሻንጣው ፡



በሻንጣ ፡ ላይ ፡ እየተደራረበ ፡ ከዚህ ፡ ጋራ ፡ ያሞሉ ፡ ጨው ፡ በብዙ ፡ የማረሻ ፡ ብረት ፡ ማለት ፡ የገበሬ ፡ ዕቃ ፡ በያይነቱ ፡ በብዛት ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ የጠገራ ፡ ብር ፡ በስልቻና ፡ በከረጢት ፡ እየሆነ ፡ ተቆልሎ ፡ ነው ፡ የሚታየው ፡ ለምዝገባ ፡ የሄዱትም ፡ ከላይ ፡ ከላዩ ፡ ያገኙትን ፡ ያነሳሱለት ፡ ይመስላል ፡ እንጂ ፡ በፍጹም ፡ የምዝገባው ፡ ሥራ ፡ አልተጀመረም ፡ ነበር ። አይቶ ፡ ሐሳብ ፡ ለማቅረብ ፡ እንዳልችል ፡ ውሎ ፡ ገባ ፡ ለመመለስ ፡ ነበርና ፡ የሄድኩት ፡ ዕቃውን ፡ በሙሉ ፡ ለማየት ፡ ባቀማመጡም ፡ ምንክያት ፡ የማይቻል ፡ ስለሆነ ፡ በደምብ ፡ መልክ ፡ እየሰጡ ፡ እንዲያዘጋጁት ፡ ነግሬ ፡ በሄድኩበት ፡ አውሮፕላን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለስኩ ።

የዕቃው ፡ ሁኔታ ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ እንዳለ ፡ በአስተዳደር ፡ በኩል ፡ ደግሞ ፡ የተላኩት ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ በኋላ ፡ (ደጃዝማች) ፡ ሥራቸውን ፡ ቀጥለው ፡ ሳለ ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ ልጅ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ኃይሉ ፡ ተከሶ ፡ ቀርቦ ፡ በሳቸው ፡ ችሎት ፡ ላይ ፡ በሚነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ የሥልጣን ፡ መልክ ፡ ለማሳየት ፡ ቆጣ ፡ እያሉ ፡ አንዳንድ ፡ ጥያቄዎች ፡ አቅርበውለት ፡ ኖሮ ፡ ቀድሞ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ በቁባትነት ፡ አስቀምጧት ፡ የነበረች ፡ ሴት ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ በቁባትነት ፡ ወስደው ፡ ያስቀመጧት ፡ መሆኑን ፡ በማወቁ ፡ በችሎቱ ፡ ላይ ፡ ቆጣ ፡ የቀረበው ፡ በዚያ ፡ ምክንያት ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ከችሎቱ ፡ ሲመለስ ፡ አንዳንድ ፡ የአባቱ ፡ አሽከሮች ፡ እየነገሩ ፡ ስላነሳሱት ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ የሚቀመጡት ፡ እዚያው ፡ ግቢ ፡ ውስጥ ፡ ስለነበረ ፡ በማግሥቱ ፡ በማለዳ ፡ ተነስቶ ፡ እከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ቁባቱን ፡ ሊወስድ ፡ በማርቆስ ፡ በኩል ፡ ገብቶ ፡ ተኩስ ፡ ከፈተ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በግቢው ፡ ውስጥ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ብቻ ፡ ሳይሆኑ ፡ የራስ ፡ እምሩ ፡ ሰዎች ፡ እንደራሴ ፡ የነበሩት ፡ ግራዝማች ፡ ወልደኢየሱስ ፡ የሚባሉት ፡ ጭምር ፡ እዚያው ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ አደጋውን ፡ ተከላከለው ፡ ነፍስ ፡ ሳይወድቅ ፡ ግቢውን ፡ ለቀው ፡ ወደ ፡ አብማ ፡ ወጡ ። በዚያች ፡ ሰዓት ፡ ተኩሱን ፡ የሰማ ፡ በአካባቢው ፡ የሚገኝ ፡ ባላገር ፡ እንደዚሁ ፡ መኳንንቱና ፡ የመኳንንቱም ፡ ልጅ ፡ እየሮጠ ፡ ወደግቢው ፡ ገባና ፡ ምክንያቱን ፡ ሲረዳ ፡ ግማሹ ፡ አጥቅተውታልና ፡ ደግ ፡ አደረገ ፡ እያለ ፡ የሐሳቡ ፡ ተካፋይ ፡ ሲሆን ፡ ግማሾቹ ፡ እሳቸውን ፡ አደል ፡ ማየት ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ መንካቱን ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ለመገላገል ፡ አስበው ፡ ሳለ ፡ ዕቃው ፡ እንደምንም ፡ የተቀመጠበት ፡ ግምጃ ፡ ቤት ፡ ያለው ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ውስጥ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ከውጭ ፡ ለሚመጣው ፡ ሰው ፡ ወዲያው ፡ ጉቢጥ ፡ የሚባለውን ፡ አረቄና ፡ ኮኛክ ፡ ከግምጃ ፡ ቤቱ ፡ እያወጣና ፡ እየከፈተ ፡ ሲያድለው ፡ ጊዜ ፡ ከነጠርሙሱ ፡ እየተጎነጨ ፡ ማን ፡ ማንን ፡ ቢሰማ ፡ መኳንንት ፡ ብቻ ፡ ሆኗል ፡ እነዚያም ፡ የመንግሥቱ ፡ ሥልጣን ፡ ይጠበቅ ፡

ያሉት ፡ መኳንንቶች ፡ ማገድና ፡ ጠቡን ፡ ማብረድ ፡ ስላልቻሉ ፡ በየውሽ ፡ በኩል ፡ ስልኩን ፡ እስካሉበት ፡ ድረስ ፡ እየበጠሱ ፡ ከንቲባን ፡ ይዘው ፡ ወደኋላ ፡ እንዳያፈገፍጉ ፡ ግድ ፡ ሆኖባቸው ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እየተላላኩ ፡ ጉዞ ፡ ቀጥለው ፡ ሳለ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ማስለቀቅ ፡ ብቻ ፡ ሳይበቃው ፡ ጦር ፡ ልክ ፡ የውሽ ፡ ላይ ፡ ተጋጠማቸው ፡ ሆኖም ፡ ተነከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ጋር ፡ የነበረውና ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ከተላኩ ፡ ከነነጋድራስ ፡ ወዳጆ ፡ ጋር ፡ የመጣው ፡ ጦር ፡ ጭምር ፡ አብሮ ፡ ያለውን ፡ ጦር ፡ ድል ፡ አድርጎ ፡ መለሳቸው ።

በዚያን ፡ ጊዜ ፡ በጦሩ ፡ ውስጥ ፡ ከነበሩት ፡ የፊታውራሪ ፡ ባለህ ፡ ልጅ ፡ ቀኛዝማች ፡ አክለው ፡ ባለህ ፡ (ዛሬ ፡ ፊታውራሪ) ፡ ከጦሩ ፡ ላይ ፡ ተማርኮ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ ተላከ ፡ እግርማዊነታቸው ፡ ፊት ፡ ቀርቦ ፡ ሲጠየቅ ፡ ባፍለኛነት ፡ ዘመኑ ፡ ላይ ፡ የነበረ ፡ በመሆኑ ፡ ጥፋት ፡ ያጠፋና ፡ በጥፋቱ ፡ ተይዞ ፡ እንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ላይ ፡ መቅረቡ ፡ አይስማወም ፡ ነበርና ፡ ያለ ፡ ምንም ፡ ሥጋት ፡ እኛ ፡ አላጠፋንም ፡ ያጠፉ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ናቸው ፡ እያለ ፡ የከንቲባ ፡ ማተቤን ፡ ወንጀል ፡ ይዘረዝር ፡ ጀመር ። እንደዚህ ፡ ሆኖ ፡ ሳለ ፡ በዚያኑ ፡ ጊዜ ፡ ለጎጃም ፡ ለመኳንንቱና ፡ ለፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ኃይሉ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መላክተኛ ፡ እንዲላክ ፡ ተመከረና ፡ ሊጋባ ፡ ወዳጇ ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ያየህይራድም ፡ ለጊዜው ፡ በጠቡ ፡ ላይ ፡ ሳይኖሩ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ስለ ፡ ተገኙ ፡ እሳቸው ፤ እኔም ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ በአውሮፕላን ፡ እንድንሄድ ፡ ተወሰነና ፡ ያንጊዜ ፡ የአውሮፕላኑ ፡ መነሻና ፡ ማረፊያ ፡ ጃንሜዳ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ወደ ፡ ጃንሜዳ ፡ ሄድን ።

ጃንሜዳ ፡ ስንደርስ ፡ አውሮፕላኑ ፡ አራታችንን ፡ ለመያዝ ፡ የማይችል ፡ ሆነና ፡ እኔና ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ቆይተን ፡ ሊጋባ ፡ ወዳጇና ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ሄዱ ። እነሱን ፡ አድርሶ ፡ ተመልሶ ፡ መጣና ፡ እኔንና ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስን ፡ ይዞን ፡ ሄደ ፤ አይሮፕላኑም ፡ ያረፈው ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወስታ ፡ እተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ነው ። አውሮፕላኑ ፡ እንዳረፈ ፡ ቀኛዝማች ፡ አድማሱ ፡ ተፈሪ ፡ የተባለ ፡ የፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ኃይሉ ፡ አሽከር ፡ አንድ ፡ መቶ ፡ ያህል ፡ ባለብረት ፡ ወታደሮች ፡ ሜዳውን ፡ አስከብበው ፡ ይጠብቅ ፡ ስለነበረ ፡ ካውሮፕላኑ ፡ እንደወረድን ፡ በጥበቃ ፡ መልክ ፡ ከቦና ፡ አሳጅቦ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ይዞን ፡ ሄደ ። እዚያም ፡ ስንደርስ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ኃይሉን ፡ ከብዙ ፡ መኳንንቶችና ፡ የመኳንንት ፡ ልጆች ፡ ጋራ ፡ አገኘነው ። እኛም ፡ እንደደረስን ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጇም ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማም ፡ እዚያው ፡ መኳንንቱ ፡ ባሉበት ፡ ተገናኘን ፡ ወዲያው ፡ የተላክንበትን ፡ ነገር ፡ ጀመርን ፡ በዚህም ፡ ነገር ፡ ላይ ፡ ከፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡



ጋራ ፡ የነበሩ ፡ መኳንንቶች ፡ ትዝ ፡ የሚሉኝ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደርሰህ ፡ ፊቃዱ ፤ ደጃዝማች ፡ ማዘንጊያ ፤ ደጃዝማች ፡ ካሣ ፤ ቀኛዝማች ፡ አደገህ ፡ በኋላ ፡ (ፊታውራሪ) ፤ ፊታውራሪ ፡ ዘውዴ ፡ እንግዳ ፤ ቀኛዝማች ፡ እንተነህ ፡ ንጉሤ ፤ ቀኛዝማች ፡ ሰውነቴ ፡ እልምነህ ፡ ከመኳንንቶችም ፡ ልጆች ፡ እነእጥናፉ ፡ ባለህን ፡ የመሰሉ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ። በምንነጋገርበት ፡ ጊዜ ፡ ማማሾቹ ፡ እዚሁ ፡ እንዳለ ፡ ምህረት ፡ ይደረግለትና ፡ ይቀመጥ ፡ ሲሉ ፡ ማማሾቹ ፡ ባለፈው ፡ ጥፋቱ ፡ በሕይወቱ ፡ እንዳይቀጣ ፡ ምህረት ፡ ከተደረገለት ፡ ይሂድ ፡ በማለት ፡ ሆኖ ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ከተደረገ ፡ በኋላ ፡ በሕይወቱ ፡ ቅጣት ፡ ከቀረለት ፡ ይሂድ ፡ ቢታሰር ፡ ምናለበት ፡ አባቱስ ፡ ብዙ ፡ ጊዜ ፡ ታስረው ፡ ተፈተው ፡ አይደለምወይ ፡ ጎጃምን ፡ የገዙት ። በማለት ፡ አብዛኛው ፡ ድምፅ ፡ ተስማማና ፡ በመጨረሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ሐሳቡን ፡ እንዲናገር ፡ ቢጠየቅ ፡ እኔ ፡ ምን ፡ አውቃለሁ ፡ ጎጃም ፡ ያውቃል ፡ ማለትን ፡ ብቻ ፡ ተናግሮ ፡ ንግግሩን ፡ አቆመ ።

በመደምደሚያው ፡ እዚያ ፡ ካሉት ፡ መኳንንቶች ፡ ሁሉ ፡ በዕድሜ ፡ የሚበልጡ ፡ የንጉሥ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ አሽከር ፡ በመተማ ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ብዙ ፡ ሞያ ፡ የሠሩ ፡ ፊታውራሪ ፡ ደርሰህ ፡ ፊቃዱ ፡ ስለነበሩ ፡ እሳቸው ፡ እንዲናገሩ ፡ ተባለና ፡ እኝህ ፡ ሽማግሌ ፡ ነገሩን ፡ የሚያበርድ ፡ ሐሳብ ፡ ይሰጣሉ ፡ ብለን ፡ ስንጠብቅ ፡ እኔን ፡ ተናገር ፡ ካላችሁኝ ፡ ሲሄድ ፡ አይታየኝም ፡ ዘር ፡ ሳይጠፉ ፡ ለምን ፡ እንደጠፉ ፡ ይሆናል ፡ ጌታው ፡ ራስ ፡ ኃይሉ ፡ በድለው ፡ እንደሆነ ፡ መልካም ፡ በጥፋታቸው ፡ ይታሰሩ ፡ አንዱ ፡ ሲያጠፋ ፡ አንዱን ፡ መተካት ፡ የተለመደ ፡ ነው ። ዘር ፡ ጠፉ ፡ አይባል ፡ እዚያው ፡ ባደባባያቸው ፡ የመየቱ ፡ ንግሥት ፡ ልጆች ፡ አሉ ፡ አንዱን ፡ አይልኩትም ፡ ኖሯል ፡ ወይ ፡ ለምን ፡ እንደዚህ ፡ ተደረገ ፡ እኔስ ፡ ያፈቀደው ፡ ይሁን ፡ የሆነውም ፡ ሆኗል ፡ ሲሄድ ፡ አይታየኝም ፡ ብለው ፡ ሲቃ ፡ በሚሰማበት ፡ አነጋገር ፡ ተናግረው ፡ ሲጨርሱ ፡ ልጅ ፡ እግር ፡ የሆነው ፡ የቆመው ፡ የተቀመጠውም ፡ የመኳንንቱ ፡ ልጅ ፡ ባንድ ፡ ድምፅ ፡ የጌታ ፡ የፊታውራሪ ፡ ደርሰህ ፡ ቃል ፡ ቃላችን ፡ ነው ፡ አለና ፡ ሲያወካ ፡ ጊዜ ፡ ድብልቅልቅ ፡ አለና ፡ መደማመጥ ፡ ጠፋ ።

በዚህም ፡ መሐከል ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ ሲባርቅ ፡ ጊዜ ፡ ወደ ፡ መሸበሩ ፡ አዘነበለ ። ይህ ፡ ሲሆን ፡ ፊ/አድማሱ ፡ በሽሽት ፡ መልክ ፡ የክፍሉን ፡ መዝጊያ ፡ ከፈተና ፡ ዘሎ ፡ ጥልቅ ፡ ሲል ፡ እጎኑ ፡ ተቀምጠው ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጇ ፡ በሱ ፡ ዓይነት ፡ ዘለው ፡ ገቡ ፡ ከሳቸውም ፡ ቀጥለው ፡

የሚገኙት ፡ ሊቄ ፡ ኅብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ስለ ፡ ነበሩ ፡ ተከትለው ፡ ለመግባት ፡ ቢሞክሩ ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጆ ፡ በሩን ፡ ዘጉባቸው ። በዚያች ፡ በትንሺ ፡ ሰዓት ፡ የነበረው ፡ ሁናቴ ፡ የሚያስተዛዝብ ፡ ነበር ።



ደጃዝማች ፡ ወዳጆ ፡ ውቤ ።

ሆኖም ፡ ከጥቂት ፡ ጊዜ ፡ በኋላ ፡ የሽብሩ ፡ ሰዓት ፡ አለፈና ፡ ንግግሩ ፡ ቀጥሎ ፡ በመጨረሻ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ እንዲሄድ ፡ ተወሰነ ። ነገሩን ፡ ያለቀበትን ፡ ሁናቴ ፡ ለማስረዳት ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ለመሄድ ፡ እኔ ፡ ልሂድ ፡ እኔ ፡ ልሂድ ፡ የሽሽት ፡ መልክ ፡ የሚያሳይ ፡ ጥያቄ ፡ ቀረበና ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ያየህ ፡ ይራድ ፡ እንዲሄዱ ፡ ተወስኖ ፡ ሄዱ ።

ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ከሄዱ ፡ በኋላ ፡ አውሮፕላኑ ፡ ሲሄድ ፡ አደጋ ፡ ይደርስበታል ፡ ሲዋሹ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱን ፡ አይሰዱ





ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ያየኸ ፡ ይራድ ።

ትንም ፡ የሚል ፡ የግል ፡ ሐሳብ ፡ ቀርቦ ፡ ኖሮ ፡ አውሮፕላኑ ፡ ከመምጣት ፡ ዘገየ ።

በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ስልኩ ፡ የሚገኘው ፡ የውሽ ፡ እተባለው ፡ አገር ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ ሄጄ ፡ እንድጠይቅ ፡ ሆነና ፡ ብጠይቅ ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ያሰጋል ፡ ስላሉን ፡ ነውና ፡ የቆየው ፡ እውነት ፡ ለመምጣት ፡ ፈቃደኛ ፡ ከሆነ ፡ ከቤተመንግሥቱ ፡ ይውጣና ፡ ላውሮፕላኑ ፡ ቅርብ ፡ እሆነው ፡ እፊታውራሪ ፡ ፍላቴ ፡ ቤት ፡ ይሂድና ፡ እዚያ ፡ መሄዱን ፡ እንዳስታወቃችሁን ፡ አውሮፕላኑ ፡ ይላካል ፡ ተባልኩና ፡ ተለመስኩ ፤ ይህንኑ ፡ ነገርኩና ፡ ፊ/አድማሱ ፡ ከቤተመንግሥቱ ፡ ወጥቶ ፡ ወደ ፡ ፊታውራሪ ፡ ፍላቴ ፡ ቤት ፡ ሄደ ፤ እዚያ ፡ እንደደረሰም ፡ ወደ ፡ ስልክ ፡ ቤት ፡ ሄጄ ፡ ጥያቄው ፡ መፈጸሙን ፡ ነገርኩና ፡ ተመልሼ ፡ ወደ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ መጥቼ ፡ ጥቂት ፡ እንደቆየሁ ፡ አንድ ፡ ያልሆነ ፡ ወሬ ፡ አስወሩ ፤ ወሬው ም ፡ ከማን ፡ እንደመጣ ፡ ባይታወቅም ፡ ቃሉ ፡ እንዲህ ፡ የሚል ፡ ነው ፤ የፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ኃይሉ ፡ የግል ፡ አሽከሮች ፡ ከቤተመንግሥቱ ፡ የዘረፉትን ፡ ብርና ፡ ወርቅ ፡ ዕቃም ፡ ወደ ፡ አገራቸው ፡ ወደ ፡ ዳሞት ፡ ሸኝተው ፡ ደረቅ ፡ ጦር ፡ ሆነው ፡ መጡ ፡ እሱን ፡ እንዳይሄድ ፡ ለማድረግ ፡ ነው ፡ የሚል ፡ ነበር ።

ጦሩ ፡ መጣ ፡ ወደ ፡ ተባለበት ፡ ቦታ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ አሰልለው ፡ እንዲያስታ ውቁኝ ፡ ለፊ/አድገህ ፡ ቢሰወር ፡ ነገርኳቸውና ፡ የመቃ ፡ አቦ ፡ እተባለ ፡ ደብር ፡ ድረስ ፡ ሰው ፡ ልከው ፡ ጦር ፡ ግን ፡ የለም ፡ ወሬው ፡ ይወራል ፡ የሚል ፡ መልስ ፡ ነገሩኝ ፤ እኔም ፡ በመጨረሻ ፡ ጦር ፡ የመጣ ፡

እንደ ፡ ሆነ ፡ ምን ፡ ማድረግ ፡ እንዳለብኝና ፡ የት ፡ ቦታ ፡ እንደምሆን ፡ ለሊቄ ፡ ገ/ክርስቶስ ፡ ብቻ ፡ ነገርኳቸ ውና ፡ ስንጠብቅ ፡ ጠዋ ፡ ሳይመጣ ፡ አወ ሮፕላኑ ፡ መጣና ፡ ፊ/አድማሱን ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄንና ፡ ሊቀ ፡ ገ/ክርስቶስን ፡ ይዘው ፡ እንዲሄዱ ፡ እኔ ፡ እንድቆይ ፡ ነበር ፡ የተማከርነው ፡ ነገር ፡ ግን ፡ ፊ/አድማሱ ፡ ተክንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ጋራ ፡ የተጣሉባት ፡ ሴት ፡ አብራኝ ፡ ካልሄደች ፡ ብሎ ፡ ስላስቸገረ ፡ ሊቄ ፡ ገ/ክርስቶስ ፡ እንዲቀሩና ፡ ሴቲቱ ፡ ከአንድ ፡ አሽከር ፡ ጋራ ፡ አብረው ፡ እንዲሄዱ ፡ ተደረገ ።

አውሮፕላኑን ፡ ከሸኘን ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ ቤተመንግሥቱ ፡ ስንሄድ ፡ የፊታውራሪ ፡ አድገህ ፡ ልጅ ፡ ጠመንጃዬን ፡ ልያዝልህ ፡ አለኝና ፡ ሰጠሁት ፡ አባትየው ፡ ጌታው ፡ ድሮ ፡ ተማመንን ፡ አሉኝ ፡ ጠቡ ፡ ሄደ ፡ ለምን፡ አንተማመን ፡ አልኳቸው ና ፡ በሳቅ ፡ ተለያየን ፤ ተማመን ፡ ወይ ፡ ብለው ፡ የጠየቁበትም ፡ ምክንያት ፡ መሣሪያቸውን ፡ ጠመንጃዬን ፡ እንያዝልህ ፡ ሲሉኝ ፡ ለመስጠት ፡ አልፈቅድም ፡ ነበርና ፡ በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ነው ።

ፊታውራሪ ፡ አድማሱን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ከሰደድን ፡ በኋላ ፡ እኔና ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ለማረፊያ ፡ ተሰጥቶን ፡ ወደ ፡ ነበረው ፡ ወደ ፡ ቀኛዝማች ፡ አድገህ ፡ ቢሰውር ፡ ቤት ፡ ሄድንና ፡ አድረን ፡ በማግሥቱ ፡ እነ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ ከየውሽ ፡ ወደ ፡ ደብረማርቆስ ፡ እንዲመጡ ፡ ላክንባቸውና ፡ መጥተው ፡ ዕቃውና ፡ ሀብቱ ፡ በሙሉ ፡ ተዘርፎ አል ፡ ያንኑ ፡ ወናውን ፡ ቤት ፡ አስረክብናቸው ።

የዕቃውን ፡ መዘረፍ ፡ ካነሣሁ ፡ ከዘረፋው ፡ ታሪክ ፡ ትንሽ ፡ ላውጋ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤን ፡ ለማጥቃት ፡ ተነስቶ ፡ አዲጋ ፡ ጥሎ ፡ ሲታኰስ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደጻፍኩት ፡ ግራዝማች ፡ ወልደየሱስና ፡ ከንቲባ ፡ ማተቤ ፡ እየተከላከሉ ፡ ራሳቸውን ፡ ለማዳን ፡ ብሩ ፤ ወርቁ ፤ ጨርቁ ፤ አረቄው ፡ በይያይነቱ ፡ በመላው ፡ ሙሉ ፡ የራስ ፡ ኃይሉ ፡ ተክለሃይማኖት ፡ ሀብት ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ ለቀው ፡ ወጡ ፤ የጥይት ፡ ድምፅ ፡ እያሰማ ፡ ወደ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የሚመጣው ፡ አዛውንት ፡ ሲደርስ ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አዲጋ ፡ ጥሎ ፡ የገባው ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ እነከንቲባ ፡ ቤተ ፡ መንግሥቱን ፡ ለቀውለት ፡ ሲወጡ ፡ ዕቃ ፡ ያለበትን ፡ ቤት ፡ ሰብሮ ፡ ገብቶ ፡ ያገኘውን ፡ ማንሳት ፡ ጀምሮ ፡ ነበርና ፡ አዲስ ፡ መጪው ፡ የሱን ፡ ዓላማ ፡ በመከተል ፡ ወደ ፡ ዕቃ ፡ ቤቱ ፡ እየገባ ፡ ያገኘውን ፡ እያነሳ ፡ መውጣት ፡ ሆነ ።

በዚህም ፡ ላይ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ አረቄ ፡ በየይነቱ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እያነሳ ፡ ከነጠርሙሱ ፡ መጐንጨት ፡ ሲሆን ፡ ስውነቱ ፡ እየጋለ ፡ አንዱ ፡ ሌላውን ፡ የማይሰማው ፡ ሆነና ፡ የዝርፊያ ፡ መልክ ፡ አጥቶ ፡ መጋደያ ፡ ሆነ ፤ አንድ ፡ ከረጢት ፡ ብር ፡ ወይም ፡ አንድ ፡ ስልቻ ፡ ብር ፡ አንዱ ፡ አንስቶ ፡ ሲሄድ ፡ አንዱ ፡ እሱን ፡ ይደገድልና ፡ ይዞ ፡ ሲሮጥ ፡ ደግሞ ፡



ሌላው ፡ ሁለተኛውን ፡ ይገድልና ፡ ገንዘቡን ፡ ሶስተኛው ፡ ይዞ ፡ ሲሄድ ፤ ሶስተኛውን ፡ ደግሞ ፡ እንደዚሁ ፡ አንዱን ፡ ይገድልና ፡ ይዞ ፡ ሲሄድ ፡ እየተጣጣለ ፡ በአንድ ፡ ከረጢት ፡ ወይም ፡ ስልቻ ፡ ብር ፡ እስከ ፡ ፲፫ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ የመጨረሻው ፡ የሚወስደው ፡ ይሆናል ፤ ይህ ፡ አድራጎት ፡ ባንድ ፡ ቦታ ፡ ሳይሆን ፡ ባራቱም ፡ ማዕዘን ፡ የሚደርስ ፡ በመሆኑ ፡ ከግቢው ፡ ይዞ ፡ ሲወጣ ፡ ተመልክቶ ፡ ይከተለውና ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከተማ ፡ በሰንሰል ፡ የከበረ ፡ ሜካ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ እዚያ ፡ እየተሽነጠ ፡ መታኰስና ፡ መጋደል ፡ በመጨረሻም ፡ ጊዜ ፡ ብሩም ፡ እሬሳውም ፡ እየሰንሰሉ ፡ ውስጥ ፡ ተገኝቷል ።



ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ።

በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንደገለጽኩት ፡ ከመኳንንቱ ፡ ጋራ ፡ ንግግር ፡ በምናደርግበት ፡ ጊዜ ፡ አንድ ፡ ጥይት ፡ በመባረቁ ፡ ምክንያት ፡ ወደ ፡ ማሽበሩ ፡ ታይቶ ፡ እንደነበረ ፡ ገልጨ ፡ ነበር ። ነገሩ ፡ በርዶ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱም ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተሄደ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ ማተቤ ፡ ካፈገፈጉበት ፡ እስቲመጡ ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስና ፡ እኔ ፡ ከሌሎች ፡ ከጐጃም ፡ መኳንንቶች ፡ ጋራ ፡ ሆነን ፡ በቤተ ፡ መንግሥቱ ፡ ግቢተን ፡ ስንጠባበቅ ፡ በዚያች ፡ በመጥፎዋ ፡ ሰዓት ፡ የነበረውን ፡ አንስተው ፡ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ የተናገሩትን ፡ ቃል ፡ የሚያስቅ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ጽፌዋለሁ ፤ የሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፡ ንግግር ፤

ያች ፡ ነገረኛ ፡ ጥይት ፡ ከመባረዷ ፡ በፊት ፡ እኔና ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ በመተሳሰብ ፡ ጐን ፡ ለጐን ፡ እየተመካከርን ፡ ተቀምጠን ፡ ነበር ፤ ጥይቷ ፡ ስትጮኽ ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ባቅራቢያው ፡ የሚገኘውን ፡ በር ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ ከፈተና ፡ ሲገባ ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ ዘለው ፡ ገቡና ፡ እኔ ፡ ልገባ ፡ ስል ፡ ዘጉና ፡ ከለከሉኝ ፡ መለስ ፡ ብዬ ፡ ባይ ፡ በመስኮት ፡ በኩል ፡ የቱን ፡ ልበለው ፡ እያለ ፡ ጠብመንጃውን ፡ በደረቱ ፡ ላይ ፡ ያነጣ ጠረ ፡ ሰው ፡ ተመለከትኩ ፡ በሩን ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ ዘጉብኝ ፡ ግን በውን ፡ ወደ ፡ ኋላዬ ፡ ብገፋው ፡ አልገፋ ፡ አለኝ ፤ ሰውዬው ፡ ለእኔ ፡ ነው ፡ ያነጣጠረው ፡ አልኩ ። ይህ ፡ ሰው ፡ ጠብ ፡ የለን ፡ እንተዋወቅ ፡ በምን ፡ ምክንያት ፡ ወደኔ ፡ አነጣጠረ ፡ ብዬ ፡ ሳስብ ፡ ልጅ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ ካጠ ገቢ ፡ ጠመንጃውን ፡ ወደ ፡ ሰውዬው ፡ ሲያዘግብ ፡ ቀኛዝማች ፡ አንተነህ ፡ ንጉሤ ፡ የሚባሉት ፡ ከወዲያ ፡ መጥተው ፡ አንተ ፡ አበድክ ፡ እኔን ፡ በለኝ ፡ ብለው ፡ በሰውዬውና ፡ በልጅ ፡ ከበደ ፡ ጠመንጃ ፡ መሃከል ፡ ሲገቡ ፡ ሰው ዬው ፡ ወደ ፡ ኋላው ፡ ተመለሰ ፡ ደጃዝማች ፡ ወዳጄ ፡ በሩን ፡ ዘግተው ፡ በድምጻቸው ፡ እየጮሁ ፡ ዋ ፡ አውሮፕላን ፡ ነጅውን ፡ ትገድሉና ፡ ጉድ ፡ ይፈላል ፡ እያሉ ፡ ሲናገሩ ፡ ይሰማሉ ። መልካቸው ፡ አይታይም ፡ ደግሞ ፡ ባላምባራስ ፡ ግርማ ፡ ተቀምጠንበት ፡ የነበረውን ፡ ወንበር ፡ መከታ ፡ አድርገው ፡ አይታዩም ፡ ነበር ፤ እኔም ፡ በኋላ ፡ አየኋቸውና ፡ ዋይ ፡ ንዴት ፡ ትድም ፡ አውቄ ፡ ብሆን ፡ ግንቡን ፡ ከምገፋ ፡ እንደሳቸው ፡ አንዱን ፡ ወን በር ፡ በላዬ ፡ ላይ ፡ አድርጌ ፡ ቁጭ ፡ ብል ፡ መልካም ፡ ነበር ፡ ብዬ ፡ ካለፈ ፡ በኋላ ፡ አሰብኩ ፡ ብለው ፡ እየተናገሩ ፡ አሳቁን ፤ ሚሽካም ፡ አንዱን ፡ ጥጋት ይዞ ፡ ቆሞ ፡ ነበር ፤ ደግሞ ፡ አንድ ፡ የሚገርም ፡ ነገር ፡ ሽብሩን ፡ ሰምቶ ፡ ይናጭ ፡ ከሚባለው ፡ አገር ፡ ፊታውራሪ ፡ እምቢአለ ፡ የሚባል ፡ የታወቀ ጀግና ፡ ነው ፡ የተባለ ፡ እኛ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ከደረስን ፡ በኋላ ፡ ከነወታ ደሮቹ ፡ ስለ ፡ መጣ ፡ አነጋገርነው ፡ እሱም ፡ ተሸብሯል ፡ ቢሉኝ ፡ ለዕር ዳታ ፡ መጣሁ ፡ አለን ፤ በል ፡ እንግዲህ ፡ ይህችን ፡ የተራረፈች ፡ ዕቃና ፡ ጥይት ፡ አስጠብቅ ፡ አንተም ፡ ለመንግሥቱ ፡ ባለውለታ ፡ ትሆናለህ ፡ ብለነው ፡ እሺ ፡ ብሎ ፡ ሲጠብቅ ፡ ውሎ ፡ አድሮ ፡ ነበር ፡ በመጨረሻው ፡ ግን ፡ ፊታውራሪ ፡ አድማሱ ፡ ከሄደ ፡ በኋላ ፡ እኛ ፡ እምነታችንን ፡ በሱ ፡ ላይ ፡ ጥለን ፡ ቀድሞ ፡ ወደ ፡ ተመራንበት ፡ ለአዳር ፡ እፊታውራሪ ፡ አድ ገህ ፡ ቢሰውር ፡ ቤት ፡ ሄደን ፡ አደርን ፡ ጧት ፡ ብንመጣ ፡ ያ ፡ ፊታውራሪ ፡ ያችን ፡ ጠብቅ ፡ የተባለውን ፡ ከዘረፉ ፡ አምልጣ ፡ ቀርታ ፡ የነበረች ፡ ጥይ ትና ፡ ዕቃ ፡ ሌሊት ፡ ጥርግ ፡ አድርጎ ፡ ከነሰዎቹ ፡ ጥበቃውን ፡ ትቶ ፡ አገሩ ፡ ሄዶ ፡ አገኘነው ፤ ወደረፋዱ ፡ ላይ ፡ ከንቲባ ፡ ማተቢያ ፡ መጡ ፤ እኛም ፡ ያንኑ ፡ ወና ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ አስረከብንና ፡ አውሮፕላን ፡ ስለ ፡ መጣልን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ተመለስን ።

ሐ/ አሁን ፡ ወደተነሣሁበት ፡ ተመልሼ ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ጊዜ ፡ ስለ ፡ ተደረገው ፡ ሁኔታ ፡ እቀጥላለሁ ።



በትግሬም ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ጉግሣ ፡ እመጀመሪያው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ነው ፡ ተብሎ ፡ እምነት ፡ ተጥሎበት ፡ ሳለ ፤ የትግሬ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ በሙሉ ፡ አልተሰጠኝም ፡ በማለት ፡ ተቀያሚ ፡ ሆኖ ፡ ይሁን ፡ ወይም ፡ በሌላ ፡ ምክንያት ፡ ይሁን ፡ አይታወቅም ፡ ከጦሩ ፡ ግምባር ፡ ላይ ፡ ከነወታደሮቹ ፡ ከድቶ ፡ ለጠላት ፡ አመነና ፡ በሩን ፡ ከፍቶ ፡ አድርጎ ፡ ጠላትን ፡ አስገባው ። ሌሎችም ፡ እንደዚሁ ፡ የጠላትን ፡ የተንኰል ፡ መርዝ ፡ የቀመሱ ፡ ከሩን ፡ የሚሉ ፡ ሁሉ ፡ በግልጥ ፡ ባይከዱ ፡ አብዛኞዎቹ ፡ በጦር ነቱ ፡ ጊዜ ፡ አገሬ ፡ ቤቴ ፡ ብለው ፡ ስለ ፡ ነፃነታቸው ፡ ያልተዋጉ ፡ መሆ ናቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ።

ከዚህ ፡ በላይ ፡ የጻፍኩት ፡ የከዱትንና ፡ የበደሉትን ፡ ሲሆን ፡ አሁን ፡ ደግሞ ፡ የምቀጥል ፡ አዝማች ፡ በነበሩት ፡ ላይ ፡ ተደረገ ፡ የተባለውንና ፡ ኃይል ፡ የቀነሰውን ፡ ስህተት ፡ ነው ።

መ/ በሐረር ፡ በኩል ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ ሆነው ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝ ማች ፡ ነሲቡ ፡ ዘአማኑኤል ፡ በቤተ ፡ መንግሥት ፡ በማደግና ፡ ወይም ፡




ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዘአማኑኤል ።

የጦር ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ በአዝማችነት ፡ ሞያ ፡ የታወቁ ፡ ካለመሆናቸው ፡ የተነሣ ፡ በወ ስጣቸው ፡ እንዲታዘዙና ፡ እንዲሰለፉ ፡ የተደረጉትና ፡ የተ መደቡት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ እላይ ፡ በገለጽሁት ፡ ምክንያት ፡ በመናናቃ ቸው ፡ ትእዛዙ ፡ በደንብ ፡ የተከበረ ፡ አልነበረም ፡ ይባላል ።

በዚህ ፡ ባለመግባባትና ፡ ባለመከባበር ፡ ምክንያት ፡ በአዛዥም ፡ ሆነ ፡ በታዛዦቹ ፡ ብዙ ፡ ጊዜና ፡ ሰዓት ፡ ያለ ፡ ሥራ ፡ በከንቱ ፡ ይጠፋ ፡ ነበር ፤

ይህንንም ፡ ብዬ ፡ ልጽፍ ፡ የቻልኩት ፡ ከላይ ፡ በተጠቀሰው ፡ የጦር ፡ ግም ባር ፡ ክፍል ፡ የባሎና ፡ የጐፋ ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ዳምጠው ፡ በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ የነበረውን ፡ የሥራ ፡ ጉድለት ፡ በመ ዘርዘር ፡ እየተናገሩ ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ መንግሥቱ ፡ መፍረሱ ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ በደኅና ፡ ተመልሰን ፡ ቢሆን ፡ እንዲያውም ፡ ፍርድ ፡ እጠይቃለሁ ፡ ብዬ ፡ ነበር ፡ በዚያ ፡ በሐረር ፡ በኩል ፡ ሥራ ፡ ሳይሠራ ፡ ለተበተነው ፡ ጦር ፡ አላፊ ፡ ሆኖ ፡ መጠየቅና ፡ መወቀስ ፡ የነበረበት ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዘአማኑኤል ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ የጦርነቱን ፡ በደንብ ፡ አለመከናወንና ፡ የጦር ፡ አዛዥነታቸውን ፡ በመንቀፍ ፡ ሲናገሩ ፡ በሰማሁት ፡ መሠረት ፡ ነው ፡ የጻፍሁት ። በሐረር ፡ ውጋዴን ፡ በኩል ፡ በደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ የበላይ ፡ ጦር ፡ አዛዥነት ፡ ሥር ፡ ተመድበው ፡ የነበሩ ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ ጦሩ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከቱት ፡ ናቸው ።



ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ።

፩/ የሐረርጌ ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ አዝማች ፡ ደጃዝማች ፡ ነሲቡ ፡ ዘአ ማኑኤል ፤

፪/ የኢሉባቦር ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ አዝማች ፡ ደጃዝማች ፡ መኰንን ፡ እንዳልካቸው ፤





ደጃዝማች ፡ ሀብተ ፡ ሚካኤል ፡ ይናዱ ።



ደጃዝማች ፡ አምደ ፡ ሚካኤል ፡ ሀብቴ ፡ ሥላሴ ።

፫/ ጠመንጃ ፡ ያዥ ፡ የሚባለው ፡ የኩሎ ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ አዝማች ፡ ደጃዝማች ፡ ሃብቱ ፡ ሚካኤል ፡ ይናዱ ፤

፬/ መሐል ፡ ሰፋሪ ፡ የሚባለው ፡ የአሩሲ ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ አዝማች ፡ ደጃዝማች ፡ አምዴ ፡ ሚካኤል ፡ ሃብቱ ፡ ሥላሴ ፤



ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ።

፭/ የጐፋና ፡ የባኮ ፡ ጦር ፡ በሙሉ ፡ አዝማች ፡ ደጃዝማች ፡ አበበ ፡ ዳምጠው ፤

እነዚህ ፡ ከዚህ ፡ በላይ ፡ ስማቸው ፡ በዝርዝር ፡ የተጠራው ፡ አዛገሮች ፡ ጦሩም ፡ የታወቀና ፡ ስምቹም ፡ ሁሉ ፡ የቤተ ፡ መንግሥት ፡ አደጎች ፡ በመ ሆናቸው ፡ እላይ ፡ እንደገለጽሁት ፡ በአዛዥና ፡ በታዛገሮች ፡ መካከል ፡ በነበረው ፡ መናናቅ ፡ ምክንያት ፡ ትእዛዙ ፡ በደንብ ፡ ባለመከበሩና ፡ ባለ



መጠበቁ ፡ የጦሩ ፡ ኃይል ፡ ደካማ ፡ ሆነና ፡ ይሠራል ፡ የተባለውን ፡ ያህል ፡ ሳይሠራ ፡ ቀረ ።

ሰ/ በባሌ ፡ በኩል ፡ አዝማች ፡ የነበሩት ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መር ዕድ ፡ ናቸው ፡ በዚሁ ፡ በባሌ ፡ በኩል ፡ በደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርዕድ ፡ የበላይ ፡ ጦር ፡ አዛዥነት ፡ ሥር ፡ ተመድበው ፡ የነበሩ ፡ የጦር ፡ አለቆችና ፡ ጦሩ ፡ ቀጥሎ ፡ የተመለከተው ፡ ነው ።




ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርዕድ ።

፩/ የባሌ ፡ ጦር ፡ በደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርዕድ ፡ መሪነት ፤

፪/ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ በኰሎኔል ፡ አሁን ፡ (ብ/ጄኔራል)አስፋው፡ወልደ፡ ጊዮርጊስ ፡ መሪነት ፤

፫/ የጉማይ ፡ ጦር ፡ በፊታውራሪ ፡ አጥናፍ፡፡ ሰገድ ፡ ወልደ፡ጊዮርጊስ አዝማችነት ፡ የሄደውን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ በጠረፉ ፡ ላይ ፡ ተሰልፈው ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ አልፎ ፡ አልፎ ፡ በመዋጋት ፡ ላይ ፡ እንደቆዩ ፡ በተጨ ማሪ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ በጅሮንድ ፡ ፍቅረ ፡ ሥላሴ ፡ ከደሴ ፡ ተመልሰው ፡ በዚሁ ፡ በባሌ ፡ ውጋዴን ፡ ጦር ፡ ግምባር ፡ እንዲዋጉ ፡ ስለ ፡ ተደረገ ፤

የገንዘብ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጦር ፤ ከአራዳ ፡ ዘበኛ ፡ ጀንደር ፡ መሪ ፡ በተባለ ፡ ስም ፡ ተሰይሞ ፡ የሁለት ፡ ሻለቃ ፡ ጦር ፡ ወታደር ፡ ከተመለሰና ፡ ከሠለጠነ ፡-



ፊታውራሪ ፡ ኃይሌ ፡ አባ ፡ መርሳ ።

በኋላ ፡ ከጠላት ፡ ጦር ፡ ግምባር ፡ ከድተው ፡ ከነወታደሮቻቸው ፡ ከመጡት ፡ የኤርትራ ፡ ተወላጆችና ፡ ስመ ፡ ጥሩ ፡ ጀግኖች ፡ በነቀኛዝማች ፡ ሰለባና ፡ ቀኛዝማች ፡ አሰፋ ፡ ባሕታ ፡ መሪነት ፡ እንዲዘምቱ ፡ ተደረገ ። እነሱም ፡ ይኸን ፡ ጦር ፡ ይዘው ፡ ሄደው ፡ ከደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርዕድ ፡ ጋራ ፡ ተደ ባልቀው ፡ በሚገባ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ከተዋጉ ፡ በኋላ ፡ ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ መርዕድና ፡ ቀኛዝማች ፡ ሰለባ ፡ ቀኛዝማች ፡ አሰፋ ፡ ባሕታ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞቱ ። ከዚህ ፡ ውጊያ ፡ በኋላ ፡ በጅሮንዱ ፡ መዋጋታችን ፡ ቀርቶ ፡ ለጠላት ፡ እጃችንን ፡ እንስጥ ፡ የማለት ፡ መንፈስ ፡ በመግለጻቸው ፡ በላ ቸው ፡ የበላይ ፡ አዛዥነት ፡ የዘመተው ፡ የመንግሥቱ ፡ ጦርና ፡ እሩሲ ፡ ላይ ፡ የተገናኙዋቸው ፡ ስመ ፡ ጥሩው ፡ ጀግና ፡ ቀኛዝማች ፡ ኃይሌ ፡ አባ ፡ መርሳ ፡ ጭምር ፡ ሐሳቡን ፡ በመቃወም ፡ በኛ ፡ በኩል ፡ ለነፃነታችን ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ የምንዋጋ ፡ ስለ ፡ ሆንን ፡ እንሂድ ፡ ካሉ ፡ በርስዎ ፡ አሽከሮች ፡ እጅ ፡ ያለውን ፡ የጦር ፡ መሣሪያ ፡ ለኛ ፡ ማስረከብ ፡ አለብ ዎት ፡ አሏቸው ።



እሳቸውም ፡ መሣሪያውን ፡ ለማስረከብ ፡ እና ፡ ከነሱም ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ለመዋጋት ፡ ፈቃደኛ ፡ አለመሆናቸውን ፡ በመግለጽ ፡ ከጠላት ፡ ለመ ስማማት ፡ ጉዞ ፡ በመቀጠላቸው ፡ ከላይ ፡ ከጠቀስናቸው ፡ ተቀዋሚዎ ቻቸው ፡ ጋራ ፡ ተዋግተው ፡ ከሁለቱም ፡ በኩል ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ከሞተ ፡ በኋላ ፡ ድል ፡ ሆነው ፡ ከነአሽከሮቻቸው ፡ ተማርከው ፡ መሣሪያቸውን ፡ ተገፈው ፡ ታሠሩ ።



ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ በላንቃ ።

ከዚያም ፡ በኋላ ፡ በሌላው ፡ ቀን ፡ ማራኪዎቹ ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ጦርነት ፡ ገጥመው ፡ ሲዋጉ ፡ ከእሥር ፡ ቤት ፡ አምልጠው ፡ ከጠላት ፡ ጦር ፡ ጋር ፡ ተደባልቀዋል ፤ ቀኛዝማች ፡ ኃይሌ ፡ አባመርሳ ፡ ግን ፡ ከጠላት ፡ ጋራ ፡ ሲዋጉ ፡ በጦርነቱ ፡ ላይ ፡ ሞተዋል ፤ ፊታውራሪ ፡ አጥናፍ ፡ ሰገድ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስም ፡ በጠላት ፡ እጅ ፡ ተይዘው ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ላይ ፡ ተገድለዋል ።

ረ/ በሲዳሞ ፡ በኩል ፡ የነበሩት ፡ የጦር ፡ አዝማች ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ ናቸው ። እሳቸውም ፡ በታክቲክ ፡ ለመዋጋት ፡ አስበው ፡ በመ ደራጀት ፡ ላይ ፡ ሳሉ ፡ እግንባር ፡ ቀድሞ ፡ እንዲዋጋ ፡ የታዘዘው ፡ ጦር ፡

አለቃ ፡ ፊታውራሪ ፡ ታደመ ፡ አንበሴ ፡ የተባለ ፡ አሽከራቸው ፡ በጠላት ፡ ተሰብኰ ፡ ለጠላት ፡ ስለገባ ፡ በመጀመሪያው ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ የሚያሳዝን ፡ ነገር ፡ አጋጥሟቸው ፡ ነበር ።



ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ በላንቃ ።

በዚህ ፡ ምክንያት ፡ ከንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ሊዘምቱ ፡ ጉዞ ፡ የጀመሩት ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ከደሴ ፡ ተመልሰው ፡ በሲዳሞ፡ በኩል ፡ ለራስ ፡ ደስታ ፡ ረዳት ፡ እንዲሆኑ ፡ ተደረገ ፤ የሲዳሞም ፡ ጦር ፡ የሚበዛው ፡ የደጃዝማች ፡ ባልቻ ፡ አባ ፡ ነፍሶ ፡ ወታደር ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በጌታው ፡ የለመደውን ፡ ሰፌ ፡ ግብርና ፡ ሽልማት ፡ ካጣ ፡ ብዙ ፡ ጊዜው ፡



ስለሆነና ፡ አዲስም ፡ የተሾሙት ፡ የሲዳሞ ፡ አገረ ፡ ገዢዎች ፡ የየራሳቸውን ፡ አዲስ ፡ አሽከሮች ፡ በማደላደል ፡ ጥንት ፡ የደረጀውንና ፡ የጦር ፡ ልምድ ፡ ያለውን ፡ ፊት ፡ በመንሳት ፡ ስለ ፡ አደኸዩት ፡ በእንደዚህ ፡ ያለ ፡ ጊዜ ፡ ቢጠሩት ፡ ቅር ፡ እያለው ፡ ትእዛዝ ፡ ለመፈጸም ፡ ብቻ ፡ ቢዘምትም ፡ እንደቀድሞው ፡ አገሬንና ፡ ጌታዬን ፡ በማለት ፡ ተባብሮ ፡ በጦሩ ፡ ግንባር ፡ ሊጋፈጥና ፡ ሊዋጋ ፡ አልፈቀደም ፡ ነበር ፡ ይባላል ። አዲሱም ፡ ሎሌ ፡ የጦር ፡ ልምድ ፡ አልነበረውምና ፡ ምንም ፡ እንኳ ፡ ሰልፍና ፡ ድርጅቱን ፡ ቢያሳምር ፡ በጦር ፡ ግንባር ፡ ከልቡ ፡ ሊዋጋና ፡ ሊመክት ፡ አልፈቀደም ። ስለዚህ ፡ ለመጀመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ጥቂት ፡ ቅር ፡ ማሰኘቱ ፡ አልቀረም ፡ ነበር ፤ ግን ፡ ከደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ ጋር ፡ ከተገናኙ ፡ በኋላ ፡ እስከ ፡ መጨረሻው ፡ ድረስ ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ ተዋግተው ፡ ጠላትንም ፡ በየሥፍራው ፡ አጥቅተው ፡ ደጃዝማች ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ በጦሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ሲሞቱ ፡ ራስ ፡ ደስታ ፡ ዳምጠው ፡ እጃቸው ፡ በጠላት ፡ ከተያዘ ፡ በኋላ ፡ በግፍ ፡ ተገደሉ ።

ሰ/ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ ከነበሩት ፡ የጦር ፡ አዝማቾች ፡ መሐከል ፡ አብረው ፡ ካዘመቷቸው ፡ ሰዎች ፡ እንደተሰማው ፡ በቤጌምድርና ፡ በሰሜን ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ግንባር ፡ በሰሜን ፡ በኩል ፡ የዘመቱት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አፄኸ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ መልካም ፡ ያዝማችነት ፡ ስም ፡ እንዳላቸው ፡ ተነግሯል ። ምክንያቱም ፡ ከዚህ ፡ ቀጥዬ ፡ በገጽ ፡ ፻፴፮ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ የጐጃም ፡ ጦር ፡ የሚበልጠው ፡ በደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ በለው ፡ አሳዳሚነትና ፡ መሪነት ፡ ዳባት ፡ ከተባለው ፡ አገር ፡ ላይ ፡ ከድቶ ፡ የተመለሰው ፡ ብዙ ፡ ቢሆንም ፡ ከሸዋ ፡ አብሮ ፡ ሄዶ ፡ ከነበረውና ፡ ከጐጃሞችም ፡ ታማኞች ፡ ሆነው ፡ የቀሩትን ፡ ወታደሮች ፡ እንደነፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ ጌታሁን ፡ ያሉትንና ፡ ሌሎቹንም ፡ ይዘው ፡ ጠላትን ፡ ደኅና ፡ አድርገው ፡ እንደወጉት ፡ ተነግሯል ።

ሸ/ ከራስ ፡ እምሩ ፡ ጋራ ፡ አብረዋቸው ፡ ከነበሩት ፡ ዘማቾች ፡ ከጐጃም ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ በለው ፡ ብዙውን ፡ ጦር ፡ አስከድቶ ፡ ሲመለስ ፡ እንደዚሁ ፡ የሰሜኑ ፡ ገዢ ፡ ደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፡ በጠላት ፡ ተደልለውና ፡ ተሰብከው ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ በግልጥ ፡ እንደ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ባይከዱም ፡ አልተዋጉም ። ሃይማኖታቸውና ፡ ሞራላቸው ፡ ያዘዛቸው ፡ እነ ፊታውራሪ ፡ ነጋሽና ፡ እነፊታውራሪ ፡ ተሻገር ፡ ጥሩ ፡ ሞያ ፡ እንደሠሩ ፡ በዘማቹ ፡ አንደበት ፡ ይተረካል ፤ የነዚህም ፡ ጀግኖች ፡ መልካም ፡ ሥራ ፡ ሲነገር ፡ የደጃዝማች ፡ አያሌው ፡ ብሩ ፡ መለገምና ፡ መክዳት ፡ አንድነት ፡

ጣልቃ ፡ እየገባና ፡ እየተደባለቀ ፡ በጐጃምች ፡ እንደበት ፡ ይወጋል ፡ ይተ ረካል ። የራስ ፡ እምሩን ፡ መልካም ፡ አዝማች ፡ ናቸው ፡ ተብሎ ፡ ካስመ ሰገናቸው ፡ አንዱ ፡ እነዚህ ፡ ሰዎች ፡ እንደ ፡ ከዱ ፡ ሲያውቁ ፡ ጠላትን ፡ ወደፊት ፡ አስቀምጦ ፡ አንዱን ፡ ከድቷል ፡ አንዱንም ፡ ሊከዳ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ ከወገን ፡ ጋራ ፡ ከመዋጋት ፡ እንዳላወቀና ፡ እንዳልሰማ ፡ ሆኖ ፡ ጠላትን ፡ በተገኘው ፡ ኃይል ፡ ማጥቃት ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ ብሀትና ፡ ማነሱን ፡



ልዑል ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።

ሳይመለከቱ ፡ በተገኘው ፡ ጦር ፡ ጠላትን ፡ መውጋታቸውና ፡ ሲመለሱም ፡ ያንኑ ፡ በመጠኑ ፡ የተገኘውን ፡ ሰው ፡ ሥርዐቱን ፡ አክብሮ ፡ የአዛዥና ፡ የታዛዥም ፡ መግባባት ፡ እንዳለ ፡ ጐጃም ፡ ደርሰው ፡ ከጐጃም ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ ክብራቸው ፡ እንደተጠበቀ ፡ መሻገራቸው ፡ ነው ።

በዚህም ፡ ጊዜ ፡ ጐጃሞችን ፡ ከዱ ፡ ብለን ፡ ብንጽፍም ፡ ከመካከላ ቸው ፡ ታማኝ ፡ አልጠፉም ፡ ነበር ፤ ታማኞችም ፡ የምንላቸው ፡ በሬ ትም ፡ እነ ፡ ደጃዝማች ፡ ገሠሠ ፡ ከዳባት ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ከድተው ፡ ቢመጡ ፡ አገር ፡ አናስገባም ፡ ብለው ፡ የተዋጉና ፡ መድረሻ ፡ ካሳጡቸ ውና ፡ ከድል ፡ በኋላም ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ ደብረ ፡ ማርቆስ ፡ ሲደርሱ ፡ ክብራ





ደጃዝማች ፡ አላምረው ።



ፊታውራሪ ፡ ደስታ ፡ ጌታሁን ።



ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ እምሩ ።

ቸውን ፡ ጠብቀው ፡ በግንደበረት ፡ ወደ ፡ ሸዋ ፡ ሲሻገሩ ፡ እስከ ፡ ሜጫ ፡ ቤታቸው ፡ ድረስ ፡ ራስ ፡ እምሩን ፡ ያደረሱ ፡ እነደጃዝማች ፡ አላምረ

ውና ፡ እንደነፊታ ውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ እምሩ ፡ ያሉት ፡ ናቸው ። ምንም ፡ እንኳ ፡ የደጃዝማች ፡ አላምረውና ፡ የፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ እምሩ ፡ ስም ፡ በመሪነታቸው ፡ ቢጠራ ፡ አብረዋቸው ፡ የነበሩት ፡ ባለውለታዎች ፡ ብዙ ፡ መሆናቸው ፡ የሚዘነጋ ፡ አይደለም ። እስከዚህ ፡ ድረስ ፡ ያለውን ፡ ስለ ፡ ራስ ፡ እምሩ ፡ አዝማችነት ፡ ስጽፍ ፡ ከጐጃም ፡ መኳንንቶችና ፡ ከሕዝ ቡም ፡ ከያንዳንዱም ፡ ተራ ፡ ወታደር ፡ በሰማሁት ፡ ሲሆን ፡ ወደ ፡ ጐሬ ፡ ከተዛወሩ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ መንግሥትን ፡ ለማቋቋም ፡ ሞክረው ፡ እንደ ፡ ነበረ ፡ ብሰማም ፡ በመጨረሻ ፡ እንደ ፡ እነደጃዝማች ፡ ታዬ ፡ ጉልላቴ ፡ ያሉትና ፡ ሌሎችም ፡ ጭምር ፡ እንደ ፡ አታለሏቸው ፡ ይነገራል ። የዚህ ንም ፡ ዝርዝር ፡ አጥርቼ ፡ ባለማወቄ ፡ ሰፋ ፡ አድርጌ ፡ ለመጻፍ ፡ ስለአል ቻልኩ ፡ አልፌ ፡ ወደ ፡ ተነሳሁበት ፡ ሥረ ፡ ነገር ፡ እመለሳለሁ ።

ቀ/ በውስጥ ፡ የነበረው ፡ ፖለቲካ ፡ እርስ ፡ በርሱ ፡ ባለመስማማት ፡ በጠላት ፡ ተንኰል ፡ የተመረዘ ፡ ስለሆነ ፡ በአስተዳደሩ ፡ በኩል ፡ ለመ ሪው ፡ ችግር ፡ ሳይፈጥር ፡ አልቀረም ። ነበሩ ፡ ከሚባሉትም ፡ አዋቂዎ ችና ፡ ጀግኖች ፡ ብዙዎቹ ፡ በሞት ፡ የታጡ ፡ ሲሆን ፡ ያሉትንም ፡ የጠ ላት ፡ ሰብከት ፡ እያታለላቸው ፡ በሥራት ፡ ጥፋት ፡ በመጋዝና ፡ በመሻር ፡ ኃይላቸው ፡ የደከመ ፡ ነበር ። ጠላታችንም ፡ ቅድሙንም ፡ እርስ ፡ በርሳ ችን ፡ የማንስማማበትን ፡ ተንኰል ፡ ባልታወቀ ፡ መንገድ ፡ መስበኩ ፡ እዚህ ፡ ለመድረስ ፡ ስለሆነ ፡ ያጠመደው ፡ ወጥመድ ፡ እንደያዘለት ፡ ሲረ ዳና ፡ አዲሱም ፡ የሥልጣኔ ፡ ድርጅት ፡ እንደ ፡ አልደረሰ ፡ ሲያውቅ ፡ ማጥቃት ፡ የሚቻለው ፡ ዛሬ ፡ ነው ፡ ብሎ ፡ የግፍ ፡ ወረራውን ፡ ቀጠለ ። ይህ ፡ ሁናቴ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ለዋናው ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ቀዳሚ ፡ ሆነው ፡ በታዘዙት ፡ የጦር ፡ አለቆችም ፡ በኩል ፡ አንዳንድ ፡ የተሳሳቱ ፡ ነገሮች ፡ እንደነበሩም ፡ ከጦሩ ፡ ግንባር ፡ በሽሽት ፡ ተመላሽ ፡ ከነበሩት ፡ ዘማቾች ፡ ላይ ፡ ይሰማ ፡ ነበር ።

ይህም ፡ የሚሰማው ፡ ቃል ፡ የሚያስረዳው ፡ እንደጠቀስኩት ፡ መተ ባበርና ፡ መግባባት ፡ አለመኖሩን ፡ ነው ። በኢትዮጵያ ፡ ሰሜን ፡ ግንባር ፡ በትግሬ ፡ ክፍል ፡ አዝማች ፡ የነበሩት ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉና ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ነበሩ ። በዚህ ፡ ማስታወሻ ፡ ጽሑፍ ፡ ውስጥ ፡ የምገልጠው ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃትም ፡ ሆነ ፡ አቅድ ፡ ለማሻሻል ፡ ካንደኛው ፡ አዝማች ፡ ለሌላው ፡ አዝማች ፡ ቃል ፡ የደረሳቸው ፡ እንደሆነ ፡ እንደ ፡ አስፈላጊነቱ ፡ አመ ዛዘኛ ፡ መሥራት ፡ ወይም ፡ ለመሥራት ፡ የሚያስቸግር ፡ ነገር ፡ እንዳለ ፡ ለማስረዳት ፡ መልስ ፡ በመስጠት ፡ ፋንታ ፤ እንደገና ፡ ወደ ፡ ንጉሠ ፡ ነገ ሥቱ ፡ ጥያቄ ፡ ያስተላልፉ ፡ ነበር ፡ በማለት ፡ አብሮ ፡ ዘምቶ ፡ በነበረው ፡





ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ።

ከሞት ፡ ተርፎ ፡ በተመለሰው ፡ ዘማች ፡ አንደበት ፡ ይነገር ፡ ነበር ። እንዲ ያውም ፡ በጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ በቀጥታ ፡ አዛዥነት ፡ ዘምተው ፡ ከነበሩት ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ለማጥቃት ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ እያገኙ ፡



ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ።



ራስ ፡ ሙሉጌታ ።



አዝማቹን ፡ እንዲፈቅዱ ፡ ሲጠይቋቸው ፡ ንጉሡ ፡ ንጉሥ ፡ ነገሥቱን ፡ ሳልጠይቅ ፡ አይሆንም ፡ እያሉ ፡ ስለ ፡ ከለከሏቸው ፡ ጠላትን ፡ ለማጥቃት ፡ በሚችሉበት ፡ ጊዜ ፡ መጠቃት ፡ የደረሰባቸው ፡ ዘማቾች ፡ ብዙ ፡ እንደነበሩ ፡ ታውቋል ።



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ማርያም ።

አንዳንዶቹም ፡ የጦር ፡ አለቆቹ ፡ አዝማቹ ፡ ባይፈቅዱም ፡ ከምን ጠቃ ፡ በማለት ፡ ጠላትን ፡ እያጠቁ ፡ በጦሩ ፡ ግንባር ፡ ሕይወታቸውን ፡ እስከ ፡ ማሳለፍ ፡ ድረስ ፡ እየሠሩ ፡ ወድቀው ፡ ላገርና ፡ ለወገን ፡ ኩራት ፡ የሚሆነውን ፡ የጀግንነት ፡ ሞያ ፡ በመፈጸም ፡ ታሪክ ፡ አትርፈዋል ፡ አንዳንዶቹም ፡ ጠላትን ፡ አጥቅተው ፡ ሲመለሱ ፡ ያለፈቃድ ፡ ሄዳችሁ ፡ ለምን ተዋጋችሁ ፡ በመባል ፡ በጦር ፡ ሚኒስትሩ ፡ ተወቅሰው ፡ ዋስ ፡ የጠሩ ፡

መሆናቸውን ፡ ከሞት ፡ ተርፈው ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ ከተመለሱት ፡ አንደ ኛው ፡ ፩ ደጃዝማች ፡ ወልደማርያም ፡ የተባሉት ፡ ነግረውኛል ።

በጦሩም ፡ ግንባር ፡ ላይ ፡ የጀግንነት ፡ ሞያቸውን ፡ እየፈጸሙ ፡ የወ ደቁትና ፡ ለተከታዩ ፡ ትውልድ ፡ የሚያኰሩ ፡ ታሪክ ፡ የተውለት ፡ እንደ



ቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ።

---

ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ማርያም፤ በአድዋ ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ ከቀኛዝማች ፡ ታፈሰ ፡ አባይ ነህ ፡ ጋራ ፡ የነበሩ ፡ ቀኛዝማች ፡ ታፈሰ ፡ አባይነህ ፡ አድዋ ፡ በጦሩ ፡ ላይ ፡ ስለሞቱ ፡ ደጃዝ ማች ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ትእዛዝ ፡ በራስ ፡ አባተ ፡ ቧ ፡ ያለው ፡ ባልደረብነት ፡ እንዲተዳደሩ ፡ ሆነው ፡ በከንባታ ፡ ደንበኛ ፡ ጦር ፡ ውስጥ ፡ የኖሩ ፡ በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ አጋፋሪነት ፡ በኋላም ፡ ደጃዝማች ፡ አባውቃው ፡ ከታሠሩ ፡ በኋላ ፡ የጌልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ ለሚባለው ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ ተሾመው ፡ የነበሩ ፡ በማይጨው ፡ ዘመቻ ፡ ጊዜ ፡ በጦር ፡ ሚኒስቴሩ ፡ በላይነት ፡ ለሚተዳደረው ፡ በጎሙ ፡ ግዛት ፡ ለሚኖረው ፡ ጦር ፡ አለቃ ፡ ሆነው ፡ የተሾሙ ፡ የጎሙ ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ናቸው ። የትውልድ ፡ አገራቸው ፡ በደብረ ፡ ብርሃን ፡ አውራጃ ፡ ሞዮ ፡ ቀበሌ ፡ ነው ።





ደጃዝማች ፡ በየነ ፡ ወንድማገኘሁ ፡ (ሊጋባ ፡ የነበሩት) ።

ነቢትወደድ ፡ መኰንን ፡ ደምሰው ፡ እንደነደጃዝማች ፡ በየነ ፡ አባስብስብ ፡ ያሉትና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ናቸው ፤ እንደዚሁም ፡ ካንዱ ፡ አዝማች ፡ ወደ ፡ ሌላው ፡ ቃል ፡ የተላለፈ ፡ እንደሆነ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ሳይሰ ሙትና ፡ ሳይፈቅዱ ፡ እየተባለ ፡ አይሠራበትም ፡ ነበርና ፡ እርስ ፡ በርስ ፡ ከወዲያ ፡ ወዲህ ፡ በመጠያየቅ ፡ የሚያልፈው ፡ ጊዜ ፡ ለጠላት ፡ መዘጋ ጃና ፡ መጠንቀቂያ ፡ ምቹ ፡ ጊዜ ፡ ሆነውና ፡ በዚያን ፡ ግንባር ፡ የነበረው ፡ ጦር ፡ ከላይ ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ወኔያቸው ፡ እያበዛቸው ፡ የጀግንነት ፡ ሥራ ፡ ከሠሩት ፡ በስተቀር ፡ የጦር ፡ አዝማቾቹ ፡ ፕላን ፡ አዘጋጅተው ፡ ለጦሩ ፡ አቅድ ፡ ሰጥቶ ፡ በመምራት ፡ እንዳልተሠራ ፡ ይነገር ፡ ነበር ።

አዝማቾቹ ፡ ባለመግባባታቸው ፡ ምክንያት ፡ ጦር ፡ እንደውሀ ፡ ጠምቶት ፡ ያገሩ ፡ ነፃነትና ፡ የንጉሡ ፡ ነገሥቱ ፡ ፍቅር ፡ አስገድዶት ፡

የጠላትን ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ለግንባር ፡ ገጥሞ ፡ ለመውጋት ፡ የጐመጀው ፡ ወታደር ፡ በከንቱ ፡ እንዲዋዥቅ ፡ ሆነ ። እንደ ፡ ታሰበውም ፡ ሳይሆን ፡ ቀረና ፡ ጦሩ ፡ ወደ ፡ መመለሱ ፡ ደረሰ ። የራያና ፡ ያዘቦ ፡ ተወላጅም ፡ ከድቶ ፡ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ከነጦራቸው ፡ ከጦር ፡ ግንባር ፡ መመለሳቸውን ፡ በተመለከቱ ፡ ጊዜ ፡ በየሚካውና ፡ በየቁጥቋጦው ፡ ውስጥ ፡ እየተደበቀ ፡ በተመላሹ ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ባደጋውም ፡ ውስጥ ፡ ፩ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ የተገደሉ ፡ መሆናቸውን ፡ ይህን ፡ የመሰለ ፡ የሚያሳዝን ፡ ወሬ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ወልድያ ፡ ሲደርሱ ፡ ሰሙ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ በግሥጋሴ ፡ መንገዝ ፡ ጀመሩና ፡ አላማጣ ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣና ፡ የልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ ጦር ፡ ድል ፡ ሆኖ ፡ እንደተመለሰ ፡ ተሰማ ። ቢሆንም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጉዞዋቸውን ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ ቀጠሉና ፡ ኰረም ፡ ላይ ፡ ሲደርሱ ፡ ከራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ጦር ፡ ተባራሪ ፡ እየሆነ ፡ ደረሰ ። ኰረም ፡ ላይ ፡ ጥቂት ፡ ጊዜ ፡ ተቆየና ፡ የነልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ የመጨረሻ ፡ ሁኔታቸው ፡ ስላልታወቀ ፡ እሉ ፡ ወደተባለበት ፡ ቦታ ፡ መልክተኛ ፡ ተላከና ፡ ሲጠበቅ ፡ ጥቂት ፡ ራሳቸውን ፡ ሆነው ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣና ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መጡ ። የተላከውም ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡ ነበር ።

ለራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ እርዳታ ፡ ተልከው ፡ የነበሩት ፡ ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻም ፡ እንደዚሁ ፡ ከጥቂት ፡ ወታደሮች ፡ ጋራ ፡ ሆነው ፡ ኰረም ፡ ላይ ፡ ደረሱ ።

---

፩ ራስ ፡ ሙሉጌታ ፡ በአጼ ፡ ምኒልክ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከር ፡ ሆነው ፡ ያደጉ ፡ ናቸው ። የትውልድ ፡ አገራቸውም ፡ በሸዋ ፡ ጠቅላይ ፡ ግዛት ፡ እንሳሮ ፡ ወረዳ ፡ ነው ። በቤተ ፡ መንግሥት ፡ እንደማደጋቸው ፡ መጠን ፡ በኢትዮጵያ ፡ በመጀመሪያ ፡ ሚኒስቴር ፡ በተሾመ ፡ ጊዜ ፡ በጅሮንድ ፡ ሙሉጌታ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ። በኋላም ፡ በልጅ ፡ ኢያሱ ፡ ዘመን ፡ መንግሥት ፡ ደጃዝማች ፡ ተብለው ፡ የግሚራ ፡ አውራጃ ፡ ገዥ ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ። በንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ዘመነ ፡ መንግሥት ፡ በድጋሚ ፡ የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ። ልዑል ፡ አልጋ ፡ ወራሽ ፡ ራስ ፡ ተፈሪ ፡ ሲባሉ ፡ ወደ ፡ አውሮፓ ፡ በሄዱበት ፡ ጊዜ ፡ ተከታይ ፡ ሆነው ፡ ከሄዱት ፡ መኳንንቶች ፡ አንዱ ፡ ናቸው ። የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ የነበሩት ፡ ፊታውራሪ ፡ ሀብተጊዮርጊስ ፡ ስለሞቱ ፡ ደጃዝማች ፡ ሙሉጌታ ፡ ፊታውራሪ ፡ ሙሉጌታ ፡ ተብለው ፡ የጦር ፡ ሚኒስትርነትን ፡ ተሾመዋል ። በዚሁ ፡ ሥራቸው ፡ ላይ ፡ እንዳሉ ፡ ራስ ፡ ጉግሣ ፡ ወሌ ፡ ከመንግሥት ፡ ፈቃድ ፡ ውጭ ፡ በሆኑበት ፡ ጊዜ ፡ በቢጌምድር ፡ ቋና ፡ አንችም ፡ ከተባለ ፡ ቀበሌ ፡ ተዋግተው ፡ ድል ፡ አድርገዋል ።

ግርማዊት ፡ ንግሥተ ፡ ነገሥታት ፡ ዘውዲቱ ፡ ካረፉ ፡ በኋላ ፡ በግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ራስ ፡ ተብለው ፡ የኢሉባቦር ፡ ጠቅላይ ፡ ገዥ ፡ ሆነው ፡ ተሾመዋል ። ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ለሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ የጦር ፡ ሚኒስትር ፡ ተብለው ፡ ተሾመው ፡ ለማይጨው ፡ ዘመቻ ፡ ለመጀመሪያው ፡ ግንባር ፡ ቀደም ፡ ጦር ፡ አዝማች ፡ ሆነው ፡ የቀደሙ ፡ ናቸው ።



ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ከየጦሩ ፡ ግንባር ፡ የተመለሰውንም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ደጀን ፡ ሆኖ ፡ ይጓዝ ፡ የነበረውንም ፡ ጦር ፡ ባንድነት ፡ አድርገው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ተጉዞ ፡ የጠላትን ፡ ጦር ፡ ለመውጋት ፡ በምክር ፡ ተወሰነና ፡ ጉዞው ፡ ወደ ፡ ፊት ፡ ቀጠለ ፤

ከኰረም ፡ ወደ ፡ ማይጨው ፡ በሚደረገው ፡ ጉዞ ፡ አሸንጌን ፡ አልፎ ፡ በማይጨው ፡ አውራጃ ፡ ግዛት ፡ አህዮ ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ሲደረስ ፡ በወገኑ ፡ ተገድሎ ፡ የወደቀው ፡ የወገናችን ፡ እሬሳ ፡ በጣም ፡ አሳዛኝና ፡ አስቃቂ ፡ ነበር ። ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ የሚጓዘውም ፡ ወታደር ፡ ለመግደል ፡ ወይም ፡ ለመሞት ፡ መሆኑን ፡ አውቆ ፡ ቢጓዝም ፡ ቅሉ ፡ በወገኑ ፡ የተገደለውን ፡ ሬሳ ፡ በየመንገዱ ፡ ላይ ፡ ግራና ፡ ቀኝም ፡ እየተመሳቀለ ፡ ወድቆ ፡ በማየቱ ፡ ከፍ ፡ ያለ ፡ ሐዘን ፡ ሳይሰማው ፡ አልቀረም ። የሆነ ፡ ሆኖ ፡ ሐዘኑን ፡ በሆዱ ፡ አድርጎ ፡ ጠላት ፡ ወደ ፡ ተሰለፈበት ፡ ጉዞውን ፡ አመራ ። ከዚህ ፡ በኋላ ፡ ነገሩ ፡ እየተበላሸ ፡ እንደሄደ ፡ ተገነዘቡና ፤ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ራሳቸው ፡ ላለው ፡ ጦር ፡ ጠቅላይ ፡ የጦር ፡ አዛዥና ፡ መሪ ፡ ሆነው ፡ መዋጋት ፡ ግድ ፡ ሆነባቸው ። ያንኑ ፡ የተገኘውን ፡ ምንም ፡ ከየደንቡ ፡ የተጠራቀመና ፡ ያልተዋወቀም ፡ ቢሆን ፡ መልክ ፡ ሰጥቶ ፡ ማሰለፍ ፡ ስለ ፡ አስፈለገ ፡ በመሐል ፡ ግንባር ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፤ በግራ ፡ ግንባር ፡ ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፤ በቀኝ ፡ ግንባር ፡ ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፤ ተመደቡ ። እነዚህም ፡ የጦር ፡ መሪ ፡ እንዲሆኑ ፡ የታዘዙት ፡ እላይ ፡ እንዳመለከትኩት ፡ ያንኑ ፡ ከየደንቡ ፡ የተጠራቀመውን ፡ ጦር ፡ ተከፋፍለው ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ የካቲት ፡ ፳፩ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ሰኞ ፡ እንዲሰማሩ ፡ ተወስኖ ፡ ሌሊቱን ፡ ተጉዞ ፡ በጠላት ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ጉዞውን ፡ ቀጠለ ።

## የሰልፉም ፡ አመራር ፡ ከዚህ ፡ ቀጥሎ ፡ በተጻፈው ፡ ዓይነት ፡ ነው ።
## ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ጋራ ፤

፩/ ከግንባር ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፡ በቀኛዝማች ፡ መኩሪያ ፡ ባንትይርጉና ፡ በግራዝማች ፡ ክፍሌ ፡ እርገቱ ፡ አዛዥነት ። የባለሚል ፡ ደንብ ፡ ጦር ፡ የእልፍኝ ፡ አስከልካይ ፡ በቀኛዝማች ፡ በልዩ ፡ ደገፉ ፡ አዛዥነት ።

፪ በግራ ፡ ግራዝማች ፡ አበራ ፡ ግዛው ፡ የሚመራው ፡ የክብር ፡ ዘበኛ ፤

፫/ በጀርባ ፡ የእልፍኝ ፡ ዘበኛ ፡ በደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፤

## በመሐል ፡ ግንባር ።

፩/ በልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ፡ የበላይ ፡ መሪነት ፤

ሀ/ በፊታውራሪ ፡ አሸናፊ፡ ኃይሉ፡ አበጋዝነት ፤ የግቢ ፡ ሚኒስቴር ፡ ጦር፤



ፊታውራሪ ፡ አሸናፊ ።

አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፤

ቀኛዝማች ፡ የሺነህ ፤
ቀኛዝማች ፡ ግፋ ፡ ወሰን ፤
አዛዥ ፡ ዘውዴ ፡ ዘመድ ፡ አገኘሁ ፤
ግራዝማች ፡ ኃይሌ ፡ ብሩ ፡
ግራዝማች ፡ ካሣዬ ፡ አልታዬ ፤
ፊታውራሪ ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፤
ፊታውራሪ ፡ ባንትይርጉ ፤

ሙሉ ፡ ቤት ፡ አዛዥርና
የግቢ ፡ ሚኒስቴር ፡
ዋና ፡ ዲሬክተር ፤
የአስታማቢዎች፡ሻለቃ
የዙፋን፡ ቤት፡ ሻለቃ ፡
ምክትል ፡ አዛዥ ፡
የሥጋ፡ ቤት ፡ ሻለቃ ፡
የቀጅዎች ፡ አለቃ ፡
የፋና ፡ወጊዎች፡ ሻለቃ
ገነት፡ሆሎታ፡ምስለኔ፡



ቀኛዝማች ፡ ዘረፋ ፡
ልጅ ፡ ደገፋ ፡ አየለ ፤

አድአ ፡ ምስለኔ ፡
የእንጀራ ፡ አሳላፊዎች
ምክትል ፡ ሹም ፡



ሊጋባ ፡ ጣሰው ፡ ዋለሉ ።

ለ/ ደጃዝማች ፡ ግዛው ፡ ጅማ ፤ የጐላ ፡ ጦር ፤
ግራዝማች ፡ ወልደ ፡ ሚካኤል ፡ አቦዬ ፡

መ/ በደጅ ፤ አጋፋሪዎች ፡ የሊጋባ ፡ ጦር ፡
ሊጋባ ፡ ጣሰው ፡ ዋለሉ ፡ አዝማች ፡
የራስ ፡ ከበደ ፡ አሽከሮች ፡
የርሻ ፡ ሚኒስትር ፡ ባልደረቦች ፡
በአዛዥ ፡ ቦጋለ ፡ የእቴጌ ፡ ጦር ፡
ነጋድራስ ፡ ወዳጆ ፡ ዓሊ ፡

ሠይፈ ፡ ጃግሬዎች ፡
ፊታውራሪ ፡ አርአያ ፡
የሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ባልደረቦች ፡
ለጦሩ ፡ ቦታ ፡ ለማሳየት ፡ መሪ ፡ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ቶድላ ፡



ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ቶድላ ።

## በቀኝ ፡ ግንባር ፤

2. ልዑል ፡ ራስ ፡ ሥዩም ፡ መንገሻ ፡ አበጋዝነት ፤
የሲናደር ፡ ያዢ ፡ ጦር ፡
የወለጋ ፡ ጦር ፡
የሊቀ ፡ መኳስ ፡ ኃይለማርያም ፡ ወልዴ ፡ ገብርኤል ፡ ጦር ፡
የቀኛዝማች ፡ ወልደዮሐንስ ፡ ወልደአብ ፡ የመድፈኛ ፡ ጦር ፡
መሪ ፡ ፊታውራሪ ፡ ተፈሪ ፡ ቶድላ ፡

## በግራ ፡ ግንባር ፤

3. በራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡ አበጋዝነት ፤
የከንባታ ፡ ጦር ፡



የዕቃ ፡ ቤት ፡ ጦር ፡
የገንዘብ ፡ ሚኒስትር ፡ ጦር ፡
በቀኛዝማች ፡ ተክሌ ፡ ማርቆስ ፡ የፖ. ቴ. ቴ. ሚኒስቴር ፡
በቀኛዝማች ፡ አበበ ፡ ረዶ ፡ የማለፊያ ፡ ጠመንጃ ፡ ያዢ ፡
በቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ በላይነህ ፡ የባልደራስ ፡ ጦር ፡



ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ።

ደጃዝማች ፡ አስፋው ፡ ደምሰው ፡
ለጦሩ ፡ ቦታ ፡ ለማሳየት ፡ መሪ ፡ ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ከበደ ፡

## በመጀመሪያ ፤

በጦርነቱ ፡ ጊዜ ፡ ለወገን ፡ መታወቂያ ፡ የተሰጠ ፡ ምልክት ፡
የማነህ ፡ የአባ ፡ ጠቅል ፡
ጠቅል ፡ ምን ፡ አለ ?
በጦሬ ፡ አልታመንም ፡ ኃይል ፡ የእግዚአብሔር ፡ ነው ፡ አለ ።
ከድል ፡ በኋላ ፡
ለመታወቂያ ፡ የተሰጠ ፡ ምልክት ፡

አምላካችን ፡ ከእኛ ፡ ጋራ ፡ አልወጣም ።
ጦሩ ፡ ባታዋየ ፡ ከተባለው ፡ ዋሻ ፡ ተነስቶ ፡ ቁልቁለቱን ፡ ወርዶ ፡ መሐን ፡ ከተባለው ፡ ቦታ ፡ ሲደርስ ፡ እንደገና ፡ ምክር ፡ ተለወጠና ፡ በዚያ ፡ ቦታ ፡ ላይ ፡ ውሎ ፡ ሆኖ ፡ የጦሩ ፡ ግጥሚያ ፡ በማግሥቱ ፡ የካቲት ፡ ፳፪ ፡ ቀን ፡ ማክሰኞ ፡ እንዲሆን ፡ ተደረገ ፡


ደጃዝማች ፡ ኃይሉ ፡ ከበደ ።

በዚህም ፡ በተባለው ፡ ቀን ፡ ውሎ ፡ እንዲሆን ፡ የታሰበበት ፡ ቦታ ፡ ለጠላት ፡ ጦር ፡ በጣም ፡ የቀረበ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ምናልባት ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ ከምሽጉ ፡ ወጥቶ ፡ ይመጣና ፡ በጠራ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ እንገናኝ ፡ ይሆናል ፡ በማለት ፡ ታስቦ ፡ ነበር ፤ የጠላት ፡ ጦር ፡ ቢጠበቅም ፡ ምሽጉን ፡ ለቆ ፡ ሊወጣና ፡ ሊገጥም ፡ አልቻለም ።

ነገር ፡ ግን ፡ ባለበት ፡ ቦታ ፡ እንዳለ ፡ የራቀውን ፡ በመድፍ ፡ የቀረበውንም ፡ በመትረየስ ፡ እንደዚሁም ፡ አይሮፕላኑ ፡ ተራ ፡ በተራ ፡ እየተመላለሰ ፡ ሲከላከል ፡ ዋለ ። በንጉሡ ፡ ነገሥቱም ፡ የሚታዘዘው ፡ ጦር ፡ ውሎ ፡ የተደረገበትና ፡ የቀድሞው ፡ ሠፈሩ ፡ ቅርብ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ስንቅ ፡ ለማምጣትና ፡ ግማሹም ፡ ሠፈር ፡ አድረን ፡ እንመለሳለን ፡ በማለት ፡ ሄዶ ፡ ኖሮ ፡ ጠላት ፡ ከምሽግ ፡ ወጥቶ ፡ የማይገጥም ፡ ከሆነ ፡ እንደፊተኛው ፡ ሐሳብ ፡ ማታውኑ ፡ ተጉዞ ፡ ሌሊት ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ለመዋጋት ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ አዛዥ ፡ ከግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ በየክፍሉ ፡ ለተመደቡት ፡ የጦር ፡ መሪዎች ፡ ትእዛዝ ፡ ተሰጠ ።



የጦር ፡ መሪ ፡ የሆኑትም ፡ ከየደንቡ ፡ የተጠራቀመው ፡ ጦር ፡ በብዙም ፡ ያልተላመደና ፡ ያልተዋወቀ ፡ ጦር ፡ ከመሆኑም ፡ በላይ ፡ በላይኛው ፡ መስመር ፡ እንዳስረዳሁት ፡ ገሚሱ ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ሄዶ ፡ ገና ፡ አልተመለሰም ፡ ነበርና ፡ ሁሉም ፡ ሊገኝ ፡ አልቻለም ፤ ሆኖም ፡ ያንኑ ፡ የተገኘውን ፡ ወታደር ፡ ይዞ ፡ ትእዛዝ ፡ መፈጸም ፡ ግድ ፡ ሆነና ፡ ሁሉም ፡ በየግንባሩ ፡ ተጓዘና ፡ አደጋ ፡ እንዲጣል ፡ እተወሰነው ፡ ጊዜና ፡ ቦታ ፡ ለመድረስ ፡ ግማሽ ፡ ሰዓት ፡ ያህል ፡ ሲቀረው ፡ ቀደም ፡ አለው ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ ከጠላት ፡ ወገን ፡ ያለው ፡ ቃፊር ፡ ጠባቂ ፡ በሮምታ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ብቻ ፡ ተኩሰና ፡ ዝም ፡ አለ ።

ከዚህ ፡ ተኩስ ፡ በኋላ ፡ ከኛ ፡ በኩል ፡ ያለው ፡ የእኛው ፡ ጦር ፡ በሞላ ፡ የተኩሱን ፡ ድምፅ ፡ በመስማት ፡ ብቻ ፡ ጠላት ፡ ወዴት ፡ እንዳለ ፡ ሳይለመለከት ፡ ከኋላም ፡ ከፊትም ፡ ያለው ፡ በሙሉ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ተኩሰና ፡ ተደባለቀ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ በቀኝ ፡ ግንባር ፡ የታዘዘውም ፡ ሆነ ፡ በግራ፡ ግንባር ፡ እንደዚሁም ፡ በመሐል ፡ ግንባር ፡ የታዘዘው ፡ ሁሉም ፡ አንድነት ፡ ባንድ ፡ ግንባር ፡ ተጋፈጡ ። የጠላትም ፡ ጦር ፡ ለጊዜው ፡ ጥቂት ፡ እንደተታኮሰ ፡ ቆየት ፡ አለና ፡ የሽሽት ፡ መልክ ፡ አሳየ ። መሬት ፡ ይዞ ፡ ይታኩስ ፡ የነበረውም ፡ የእኛ ፡ ጦር ፡ አባራሪ ፡ ሆኖ ፡ እንዲከተለው ፡ ሲሆንና ፡ ለመታኮሻ ፡ የያዘውን ፡ ቦታ ፡ ሲለቅ ፡ ባንድ ፡ በኩል ፡ ባዘጋጀው ፡ ጦር ፡ ባልጠበቀውና ፡ ባልተመለከተው ፡ ሥፍራ ፡ የግባት ፡ ተኩስ፡ አደጋ ፡ ጣለበት ። አመለጠን ፡ በማለት ፡ ለጀብዱ ፡ ሥራ ፡ ጓጉቶ ፡ በማባረር ፡ በሚከታተለው ፡ ወታደር ፡ ላይ ፡ የተተኮሰው ፡ የጠላት ፡ ጥይት ፡ ከመሬት ፡ ላይ ፡ ሊያርፍ ፡ አልቻለም ። ምክንያቱም ፡ ወታደሩ ፡ የተከታተለው ፡ በብዛት ፡ ስለሆነ ፡ ሳያነጣጥርም ፡ የውርጭፍንም ፡ ቢተኩስ ፡ ሊስት ፡ አይችልም ፡ ነበርና ፡ በዚያች ፡ በትንሽ ፡ ሰዓት ፡ ውስጥ ፡ ጠላት ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ ጐዳብን ።

የጠላትም፡ ጦር ፡ የእኛን ፡ ወታደር ፡ አደናፈሩን ፡ ከተመለከተ ፡ በኋላ ፡ በምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ ከመተኮስ ፡ በስተቀር ፡ ከምሽጉ ፡ ወጥቶ ፡ ሊገጥመን ፡ አልደፈረም ፡ ከኋላ ፡ የሚመጣውንም ፡ የእኛን ፡ ወታደር ፡ በአውሮፕላንና ፡ በመድፍ ፡ ኃይል ፡ ብዛት ፡ አቋርጦብን ፡ ነበር ። ንጉሡ ፡ ነገሥቱም ፡ ከጥቂት ፡ የክብር ፡ ዘበኞቻቸው ፡ ጋራ ፡ በጦሩ ፡ መሐል ፡ ገብተው ፡ ካራቸውን ፡ መዘው ፡ በማበረታታትና ፡ በማደፋፈር ፡ መንፈስ ፡ ወታደሩን ፡ ወደ ፡ ግንባር ፡ እንዲገፋ ፡ ያዝዙ ፡ ነበር ፤ ትእዛዝ ፡ ተቀባዩም ፡ ወታደር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ትእዛዝ ፡ አክብሮ ፡ ወደ ፡ ፊቱ ፡ ጠላት ፡ ከምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ ሳይወጣ ፡ በአይሮፕላንና ፡ በመድፍ ፡ የቀረበውንም ፡ ከምሽጉ ፡ ውስጥ ፡ እንዳለ ፡ ሆኖ ፡ በመትረየስና ፡ በእጅ ፡ ቦንብ ፡ ይከላከል ፡ ነበር ።



ግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ።



የእኛ ፡ ወታደር ፡ ጠላትን ፡ ከምሽግ ፡ ወጥቶ ፡ የግባኝር ፡ ለግንባር ፡ ግጥሚያ ፡ እናገኛለን ፡ ብሎ ፡ ተመኝቶት ፡ የነበረውን ፡ ጠላት ፡ እንደ ፡ አይጥ ፡ እኩብ ፡ ውስጥ ፡ ገብቶ ፡ ስለቀረ ፡ አላገኘውም ። ንጉሠ ፡ ነገሥቱም ፡ ተስፋ ፡ በመቁረጥ ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውጊያ ፡ ውስጥ ፡ ወደፊት ፡ ለመሄድና ፡ እስከ ፡ መጨረሻ ፡ ሕይወታቸው ፡ ሊገፉበት ፡ ቆርጠው ፡ ሲሄዱ ፡ በዚያን ፡ ጊዜ ፡ እጨጌ ፡ በነበሩት ፡ በእጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አሁን ፡ አቡነ ፡ ባስልዮስ) ፡ ትግልና ፡ ውግዘት ፡ የታገዱና ፡ የተመለሱ ፡ መሆናቸው ፡ እርግጥ ፡ ነው ። ከጦሩም ፡ ግንባር ፡ በእንደዚህ ፡ ያለው ፡ ውዝግብና ፡ ትግል ፡ እንደተመለሱ ፡ መጋቢት ፡ ፳፫ ቀን ፡ መሐን ፡ በተባለው ፡ ቦታ ፡ ውሎ ፡ ሆነ ። የተበታተነው ፡ ጦርና ፡ ቁስለኛም ፡ ከተሰበሰበ ፡ በኋላ ፡ በ፪ኛው ፡ ቀን ፡ መጋቢት ፡ ፳፭ ፡ ቀን ፡ ባታዋየ ፡ በተባለው ፡ በመጀመሪያ ፡ ወደ ፡ ጦሩ ፡ ግንባር ፡ ሲኬድ ፡ ሠፈር ፡ ከነበረው ፡ ዋሻ ፡ ደርሰው ፡ ውሎ ፡ ሆነ ። በመጨረሻም ፡ ሊደረግ ፡ የሚገባው ፡ ተመክሮ ፡ ሲወሰን ፡ ማታውኑ ፡ ጉዞው ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ አመራ ። በምክሩም ፡ ላይ ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ ጦሩ ፡ በሁለት ፡ ግንባር ፡ ተከፍሎ ፡ ለመከላከል ፡ ነበር ። ይህም ፡ በሁለት ፡ ግንባር ፡ ይከፈል ፡ የተባለው ፡ አቅድ ፡ አንደኛው ፡ ባላማጣ ፡ በር ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ ሁለተኛው ፡ ሚካኤል ፡ ዋሻ ፡ በተባለው ፡ ወደ ፡ ሰቆጣ ፡ በሚያመራው ፡ በር ፡ በኩል ፡ ነበር ። በእነዚህ ፡ በተጠቀሱት ፡ በር ፡ ይሆናሉ ፡ በተባሉት ፡ ቦታዎች ፡ ቀድመው ፡ ጦሩን ፡ እንዲያዘጋጁ ፡ የታዘዙት ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብረኤል ፡ (በኋላ ፡ ራስ) ፡ በሰቆጣ ፡ አቅጣጫ ፡ ሚካኤል ፡ ዋሻ ፡ በተባለው ፡ በር ፡ ላይ ፡ ሲሆን ፡ ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡ ደግሞ ፡ ወደ ፡ የጁ ፡ በሚያመራው ፡ በአላማጣ ፡ በር ፡ በኩል ፡ ነበር ።

## በማይጨው ፡ በዋናው ፡ ጦር ፡ ግምባር ፡ የሞቱ ፡ ታላላቅ ፡ የጦር ፡ አለቆች ።

ደጃዝማች ፡ መሸሻ ፡ ወልዴ ፡ (በተንቤን ፡ ጦር ፡ ግንባር) ፡
ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ይራድ ፡ የመራቤቴ ፡ ገዢ ፡
ፊታውራሪ ፡ አሸናፊ ፡ የግቢ ፡ ሚኒስትር ፡
ደጃዝማች ፡ መንገሻ ፡ ይልማ ፡ የጦር ፡ ሚኒስቴር ፡ ዋና ፡ ዲሬክተር ፡
ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ተድላ ፡ የማይጨው ፡ ገዢ ፡
ፊታውራሪ ፡ በየነ ፡ ሠራዊቱ ፡ (በአላጌ ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ የሞቱ) ፡
ፊታውራሪ ፡ ኃይሉ ፡ ማርያም ፡ ጎሹ ፡
ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ በላይነህ ፡ የባልደራስ ፡ ሻለቃ ፡
ቀኛዝማች ፡ አበበ ፡ ረዴ ፡ የጋሻ ፡ ጃግሬ ፡ አለቃ ፡
ፊታውራሪ ፡ ነጋሽ ፡ ተስፋዬ ፡



ደጃዝማች ፡ ወንዲራድ



ፊታውራሪ ፡ በየነ ፡ ሡራዊቱ ፡





ቀኛዝማች ፡ በየነ ፡ በላይነህ ፡



ቀኛዝማች ፡ አበበ ፡ ረዴ ፡

ግራዝማች ፡ ካሣዬ ፡ አሊታዬ ፡ የጠጅ ፡ አሳላፊዎች ፡ ሻለቃ ፡
ሻለቃ ፡ ዳኜ ፡ ወዳጆ ፡
ግራዝማች፣ እሸቱ፡ ሸዋ ፡ ርካብህ፡ የባልደራስ፡ ሻለቃ ፡ ምክትል ፡
ሻለቃ ፡ ሽበሽ ፡ ደያስ ፡ ክብር ፡ ዘበኛ ፡
ግራዝማች ፡ ተናኘ ፡ ዳርጌ ፡
ሻምበል ፡ ለገሠ ፡ አያኔ ፡
ሻምበል ፡ ተሰማ ፡ አያኔ ፡
ባላምባራስ ፡ ፋንታዬ ፡ በግቢ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሻምበል ፡
ሻምበል ፡ መብራቴ ፡ ኰላሴ ፡ በክብር ፡ ዘበኛ ፡
ባላምባራስ ፡ በቀለ ፡ ጎሹ ፡ በሥራ ፡ ሚኒስቴር ፡ ሻምበል ፡
ሻለቃ ፡ በረሄ ፡ ገብሩ ፡
የሙቶ ፡ አለቃ ፡ ሥዩም ፡ ዘለቀ ፡
ባላምባራስ ፡ ደምሰው ፡
ባሻ ፡ ግዛው ፡ የቀጂ ፡ ሻምበል ፡ በግቢ ፡ ሚኒስቴር ፡

## ከማይጨው ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ መመለስ ፤

ከዚህም ፡ በኋላ ፡ ያው ፡ የተገኘው ፡ ጦር ፡ የባታዋዮን ፡ ዋሻ ፡ ለቆ ፡ መመለስ ፡ ግድ ፡ ሆነበትና ፡ ፊቱን ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ አምርቶ ፡ ሌሊቱን ፡ ጉዞ ፡ ተጀመረ ፤ ጠላትም ፡ በሰላዮች ፡ ይህን ፡ ተመክሮ ፡ የተወሰነውን ፡ ድርጅት ፡ ደርሶበትና ፡ አውቆት ፡ ኖሮ ፡ በበኩሉ ፡ ሌሊቱን ፡ ሲገሰግስ ፡ አድሮ ፡ አሸንጌ ፡ ከተባለው ፡ ሥፍራ ፡ ላይ ፡ ሲደርስ ፡ የደፈጣ ፡ አደጋ ፡ ጥሎ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ ሌሊቱን ፡ ቀደም ፡ ብሎ ፡ አሸንጌን ፡ ያለፈው ፡ ብቻ ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ ተላለፈ ።

ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ የነበረው ፡ ክፍል ፡ ግን ፡ በደፈጣ ፡ የተጣለውን ፡ አደጋ ፡ ተከላክሎ ፡ ለማለፍ ፡ ሲታሰብ ፡ ወዲያው ፡ ንጋቶ ፡ ነበርና ፡ የጠላት ፡ አይሮፕላን ፡ ደረሰና ፡ በመርዝና ፡ በቦንብ ፡ ጠሩን ፡ በአሸንጌ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ፈጀው ። የተረፈው ም ፡ ጥቂት ፡ ጦር ፡ አሸንጌን ፡ ባሕሩን ፡ ወደ ፡ ግራ ፡ ትቶ ፡ ወደ ፡ ኰረም ፡ የሚወስደውን ፡ ጐዳና ፡ ለቆ ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ ሆኖ ፡ ወደ ፡ ሰቆጣ ፡ መንገድ ፡ አመራና ፡ ተጓዘ ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ ትልቅ ፡ ችግር ፡ ተፈጠረና ፡ የተመከረበት ፡ ድርጅትና ፡ ፕላን ፡ ሁሉ ፡ ፈርሶ ፡ በየበሩ ፡ ላይ ፡ የመከላከል ፡ ጦር ፡ ግጥሚያ ፡ ይደረጋል ፡ የተባለው ም ፡ ቀረና ፡ ባላማጣ ፡ በኩል ፡ በየጁ ፡ አቅጣጫ ፡ በሚካኤል ፡ ዋሻ ፡ በሰቆጣ ፡ አቅጣጫ ፡ የተባለው ም ፡ የሁለቱም ፡ ወገን ፡ ትእዛዙን ፡ መፈጸም ፡ ሳይችል ፡ ቀረና ፡ ጉዞውን ፡ ሁሉም ፡ ባንድ ፡ ጐዳና ፡ አደረገና ፡ በሰቆጣ ፡ አቅጣጫ ፡ ይጓዝ ፡ ጀመር ። በር ፡ ሆኖ ፡ የመከላከል ፡ ጦርነት ፡ ይደረግበታል ፡ የተባለውንም ፡ የሚካኤል ፡ ዋሻ ፡ የተባለውን ፡ አልፎ ፡



ተጓዘ ። አሸንጌን ፡ ቀኙን ፡ ይዘው ፡ የተጓዙትን ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወዴት ፡ እንዳሉ ፡ ለማወቅ ፡ አልተቻለም ፡ ነበር ።

አንዳንዳችንም ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ለማግኘት ፡ ብንጥርም ፡ እርግጠኛ ፡ ያሉበትን ፡ ቦታ ፡ የሚነግር ፡ አልተገኘም ። ወደ ፡ መጣበት ፡ አገሩ ፡ ፊቱን ፡ የመለሰው ፡ ጦር ፡ ጃንሆይ ፡ ወዴት ፡ እንዳሉ ፡ ሳናውቅ ፡ እንዴት ፡ እንሄዳለን ፡ የሚል ፡ ጥያቄ ፡ ሲደርሰው ፡ ያላየውንና ፡ ያልሰማውን ፡ ወደፊት ፡ ሄደዋል ፡ እያለ ፡ ብቻ ፡ ጉዞውን ፡ ከመቀጠል ፡ በስተቀር ፡ ቆም ፡ ብሎ ፡ ተነጋግሮ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ያሉበትን ፡ ቦታ ፡ ለመፈለግ ፡ ፈቃደኛ ፡ የሆነ ፡ ብዙ ፡ ሰው ፡ አልተገኘም ፡ ነበር ።

ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ግን ፡ ሁል ፡ ጊዜ ፡ በሚሠሩት ፡ ሥራ ፡ ሁሉ ፡ ሳይለቁ ፡ የሚያመልኩበትን ፡ ፈሪሀ ፡ እግዚአብሔርንና ፡ የመንፈሳዊ ፡ ሥራ ፡ በዚያንም ፡ ጊዜ ፡ ያልተውት ፡ ስለሆነ ፡ ወደ ፡ ቅዱስ ፡ ላሊበላ ፡ ሄደው ፡ መንፈሳዊ ፡ ጸሎታቸውን ፡ አድርሰው ፡ ሲመጡ ፡ የሚበዛው ፡ ጦር ፡ ቀድሞ ፡ የተጓዘም ፡ ቢሆን ፡ ጥቂቱ ፡ ጦር ፡ የንጉሠ ፡ ነገሥቱን ፡ ወሬ ፡ እየጠየቀ ፡ በመጠበቅ ፡ ሙጃ ፡ ላይ ፡ ቆይቶ ፡ ስለ ፡ ነበረ ፡ አገኛቸውና ፡ ከዚያ ፡ በኋላ ፡ ጉዞውን ፡ አብሮ ፡ ቀጠለ ፤ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ጉዞ ፡ ዋድላና ፡ ደላንታን ፡ አቋርጦ ፡ ወደ ፡ ወሎ ፡ መሬት ፡ መሻገር ፡ ነበረበትና ፡ በሽሎን ፡ ተሻግሮ ፡ ወደ ፡ መቅደላ ፡ ጉዞውን ፡ ሲያቀና ፡ ቀድሞ ፡ ተጉዞ ፡ የነበረው ፡ ጦር ፡ በወረሂመኖች ፡ እየተገደለ ፡ የሚገኘው ፡ሬሳ ፡ ቁጥሩ ፡ ከመጠን ፡ ያለፈ ፡ ነበር ። እንደዚሁም ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ጋራ ፡ በሚመጣው ፡ ጦር ፡ ላይ ፡ አደጋ ፡ ለመጣል ፡ ወረሂመኖች ፡ አላቋረጡም ፡ ነበር ። ወታደሩንም ፡ በጥይት ፡ በካራና ፡ በጦር ፡ እየገደሉ ፡ መሣሪያና ፡ ልብሱን ፡ ከመግፈፍ ፡ በመርዝ ፡ አድክሞ ፡ መግፈፍ ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ ብለው ፡ መክረው ፡ ኖሮ ፡ በብዙ ፡ ረኃብና ፡ ችግር ፡ የተንገላታውንና ፡ የቦንብ ፡ መርዝ ፡ ያጠቃውን ፡ ወታደር ፡ በሽሎ ፡ ከተባለው ፡ ወንዝ ፡ ላይ ፡ በብዙው ፡ የእንክርዳድ ፡ ቂጣ ፡ እየያዙ ፡ ከወንዙ ፡ ዳርቻ ፡ ከወዲያና ፡ ከወዲህ ፡ ማዶ ፡ ጠብቀው ፡ ሊሸጡለት ፡ ቀረቡ ።

የተራበው ም ፡ ወታደር ፡ ቂጣ ፡ ማግኘቱን ፡ እንጂ ፡ ከምን ፡ የተጋገረ ፡ መሆኑን ፡ የወረሂመኑ ፡ ሕዝብ ፡ በጠላትነት ፡ ያቀረበለት ፡ መሆኑን ፡ ሳያስብ ፡ ረኃቡ ፡ ጊዜ ፡ አልሰጠው ምና ፡ በኪሱ ፡ ባገኘው ፡ ገንዘብና ፡ ከወገቡ ፡ በሚያገኘው ፡ ጥይት ፡ እየገዛ ፡ መብላት ፡ ጀመረ ። ከምግቡ ፡ በኋላ ፡ በረሃብና ፡ በበረሃው ፡ሙቀት ፡ የተሰቃየው ፡ ወታደር ፡ የእንክርዳዱን ፡ ቂጣ ፡ በልቶና ፡ ወኃውን ፡ ጠጥቶ ፡ ሊራመድ ፡ ስለአልቻለ ፡ በወንዙ ፡ ዳር ፡ ባሉት ፡ የዛፍ ፡ ቁጥቋጦ ፡ ቅጠሎችና ፡ በየታላላቅ ፡ ዛፎች ፡ ሥር ፡ እየሄደ ፡ ለማረፍ ፡ ቢሞክር ፡ በዚያው ፡ እየተኛ ፡ ቀረ ፡ እንጂ ፡ ተነስቶ ፡ ጉዞውን ፡ ሊቀጥል ፡ አልቻለም ፡ ነበር ፤ የእንክርዳዱን ፡ አደጋ ፡ ያለፈውን ፡ የወረሂመኑን ፡ ባላገር ፡ የመቅደላን ፡ በር ፡ ይዞ ፡ አላሳልፍም ፡

በማለት ፡ ይታኮስ ፡ ጀመር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የግርማዊ ፡ ቀዳማዊ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የእልፍኝ ፡ አሽከሮች ፡ ልጅ ፡ ገሥሥ ፡ ጅማና ፡ ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ግዛው ፡ ከባላገር ፡ በተተኰሰው ፡ ጥይት ፡ ሞተዋል ። ከብዙ ፡ መከላከል ፡ በኋላ ፡ የመቅደላ ፡ በር ፡ ታለፈና ፡ ተንታ ፡ ላይ ፡ አዳር ፡ ሆነ ።

የመቅደላ ፡ በር ፡ ታልፎ ፡ አፋፍ ፡ ላይ ፡ ማለት ፡ ተንታ ፡ ከተደረሰ ፡ በኋላ ፡ ግን ፡ ሥጋቱ ፡ ባይቀርም ፡ ብዙ ፡ አስቸጋሪ ፡ ነገር ፡ አልገጠመም ፡ በመጀመሪያ ፡ ከማይጨው ፡ መልስ ፡ በተደረገበት ፡ ጊዜ ፡ ተመክሮና ፡ ተወስኖ ፡ የነበረው ፡ በመጀመሪያ ፡ አላማጣ ፡ ላይ ፡ መዋጋት ፡ ከዚያም ፡ ሲያቅትና ፡ ሲያስቸግር ፡ ወደ ፡ ኋላ ፡ አፈግፍጐ ፡ ወልድያ ፡ ከዚያም ፡ እንደዚሁ ፡ አፈግፍጐ ፡ ቦሩ ፡ ሜዳ ፡ ላይ ፡ ለመግጠምና ፡ በዚህ ፡ ዓይነት ፡ ታክቲክ ፡ እየተሠራ ፡ እስከ ፡ ክረምቱ ፡ ወራት ፡ ድረስ ፡ ውጊያውን ፡ ለማ ቆየትና ፡ የመንግሥቱን ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ አዲስ ፡ አበባን ፡ ለቆ ፡ ወደ ፡ ጐሬ ፡ ለማዛወርና ፡ ጊዜም ፡ እንዲገኝ ፡ ታስቦ ፡ ነበር ።



ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡

ነገር ፡ ግን ፡ እነዚህ ፡ ለመከላከያና ፡ ለጊዜ ፡ ማስረዘሚያ ፡ ይሆናሉ ፡ የተባሉትን ፡ ቦታዎች ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ እየቀደመ ፡ ስለ ፡ ያዛቸው ፡ እንደ ታሰበው ፡ ሊፈጸም ፡ ስለአልተቻለ ፡ ሐሳብና ፡ መንገዱ ፡ ተለውጦ ፡ በሌላ ፤ በኩል ፡ ሆነ ፡ እንደገና ፡ በታሰበውና ፡ በተለወጠው ፡ መንገድና ፡ አቅድ ፡



ተጉዞን ፡ ወደ ፡ ወረኢሉ ፡ ለመግባትና ፡ ወደ ፡ ሸዋም ፡ ለመላላክ ፡ ወደ ፡ ወሎም ፡ እየተሳለሉ ፡ ለመላላክ ፡ ታቅበና ፡ ሊጋምቦ ፡ ከተባለው ፡ አገር ፡ ሲደርስ ፡ ወደ ፡ ወረኢሉ ፡ ለማደራጀት ፡ መላክተኞች ፡ ቀደም ፡ ብለው ፡ ተልከው ፡ ነበር ፡ መልክተኞችም ፡ ከመድረሳቸው ፡ በፊት ፡ በአራት ፡ ሰዓት ፡ ቅድሚያ ፡ ወረኢሉን ፡ የጠላት ፡ ጦር ፡ መያዙን ፡ የተላኩት ፡ መላክተኞች ፡ አስረዱ ። መልክተኞቹም ፡ ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ወልደ ፡ ጊዮር ጊስና ፡ ደጃዝማች ፡ ሽበሺ ፡ በያን ፡ ነበሩ ። አሁንም ፡ መንገድ ፡ መለወጥ ፡ ግድ ፡ ሆነና ፡ ወደ ፡ ለገሂዳ ፡ ጉዞው ፡ እንዲያመራ ፡ ተደረገ ።

ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወረኢሉ ፡ መያዙን ፡ ካረጋገጠ ፡ በኋላ ፡ ወደ ፡ አህያ ፡ ፈጅ ፡ አፋፍ ፡ ዘልቆ ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ ጋር ፡ የሚ ያገናኘው ፡ ስልክ ፡ ሳይቆረጥ ፡ ስለአገኘ ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ደውሎ ፡



ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ ሐዋስ ።

ከማይጨው ፡ ጃማ ፡ እስቲደርስ ፡ ጃንሆይ ፡ ያሉበት ፡ ሳይታወቅ ፡ ቆይቶ ፡ የነበረውን ፡ ግርማዊት ፡ እቴጌና ፡ ለአገር ፡ ጥበቃ ፡ የቀሩትም ፡ እንዲሰሙት ፡ ስለ ፡ አደረገ ፡ ዠማ ፡ ወንዝ ፡ ድረስ ፡ አባ ፡ ሐና ፡ ስንቅ ፡ ይዘው ፡ ደርሰዋል ።

ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባም ፡ ለመሄድ ፡ ይቀርብ ፡ የነበረው ፡ መንገድ ፡ በወረኢሉ ፡ አድርጐ ፡ ባህያ ፡ ፈጅ ፡ በኩል ፡ ሲሆን ፡ ይህ ፡ ቀረና ፡ ከለገ

ሂዳ ፡ ወደ ፡ ጅማ ፡ ታልፎ ፡ ሚዳና ፡ መርሐ ፡ ቤቴን ፡ አቋርጦ ፡ መንዝና ፡ ወደ ፡ ሰላሌ ፡ መሻገር ፡ የተሻለ ፡ ነው ፡ በማለት ፡ ተመከረና ፡ ጉዞው ፡ በዚህ ፡ ዐይነት ፡ ቀጥሎ ፡ ሰላሌ ፡ ፍቼ ፡ ከተማ ፡ ደረሰን ። በልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ቤት ፡ መልካም ፡ የራት ፡ ግብዣ ፡ ተደረገና ፡ ከራት ፡ ግብዣ ፡ በኋላ ፡ ማታውኑ ፡ በውድቅት ፡ ሌሊት ፡ ከአዲስ ፡ አበባ ፡ መኪና ፡ መጥቶ ፡ ሌሊቱን ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ ጉዞ ፡ ሆነ ።

ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ከንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሳይለዩ ፡ በጥሩ ፡ ሁኔታ ፡ ግዳጃቸውን ፡ የፈጸሙ ፡ ሲሆኑ ፡ በመልስም ፡ ጊዜ ፡ በብዙው ፡ ሰው ፡ ላይ ፡ የሞራል ፡ ውድቀት ፡ ደርሶበት ፡ ሥራውን ፡ በዘነጋበት ፡ ጊዜ ፡ በጐደለው ፡ ቦታ ፡ ሁሉ ፡ ሙሉ ፡ ሆኖ ፡ በመገኘት ፡ ጉዞውን ፡ ይመሩ ፡ ከነበሩት ፡ መኳንንቶች ፡ ውስጥ ፡ አንደኛነት ፡ ይዘው ፡ ይገኙ ፡ የነበሩ ፡ ሰው ፡ ናቸው ፤ ታሪክ ፡ ጸሐፊው ፡ ይህን ፡ ምስክርነት ፡ የጻፈው ፡ አብሮ ፡ በነበረበት ፡ ጊዜ ፡ ከማይጨው ፡ እስከጅቡቲ ፡ ድረስ ፡ የነበረውን ፡ ነው ።

## የግርማዊ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ወደ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ መመለስ ።

በማይጨው ፡ ጦርነት ፡ ላይ ፡ ውለው ፡ ግርማዊነታቸው ፡ ከማይጨው ፡ ሲመለሱ ፡ እስከ ፡ አዲስ ፡ አበባ ፡ አብረው ፡ የነበሩ ፡ መሳፍንት ፤ ታላላቅ ፡ መኳንንቶችና ፡ የክፍል ፡ ሹማምንቶች ፤ የቤተ ፡ ክህነትም ፡ ሰዎች ፡ ትዝያሉኝ ፡ ከዚህ ፡ በታች ፡ በማስታወሻው ፡ ተዘርዝረዋል ።

፩/ ልዑል ፡ ራስ ፡ ካሣ ፡ ኃይሉ ፡
፪/ ክቡር ፡ ራስ ፡ ከበደ ፡ መንገሻ ፡ ፍቼ ፡ ሲደርሱ ፡ ታዘው ፡ ቀሩ ፣
፫/ ክቡር ፡ ፊታውራሪ ፡ ብሩ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (ራስ)
፬/ ራስ ፡ ጌታቸው ፡ አባተ ፡
፭/ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡
፮/ ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ይናዱ ፡ (ራስ)
፯/ ደጃዝማች ፡ ወንድ ፡ ወሰን ፡ ካሣ ፡ (ፍቼ ፡ ሲደርሱ ፡ ታዘው ፡ ቀሩ)
፰/ ደጃዝማች ፡ አበራ ፡ ካሣ ፡ (በፈቃድ ፡ ቀሩ)
፱/ ደጃዝማች ፡ ወዳጆ ፡ (ፍቼ ፡ ሲደርሱ ፡ ታዘው ፡ ቀሩ ፡)
፲/ ደጃዝማች ፡ ደበበ ፡ አንዳርጋቸው ፡
፲፩/ ደጃዝማች ፡ ግዛው ፡ ጅማ ፡
፲፪/ ደጃዝማች ፡ ወልደ ፡ ማርያም ፡




፲፫/ ፊታውራሪ ፡ አሥራተ ፡ ወልደ ፡ ገብርኤል ፡ (መርሃ ፡ ቤቴ ፡ ሲደርሱ ፡ እመንገድ ፡ ታመው ፡ ሞተዋል ።
፲፬/ በጅሮንድ ፡ ለጥ ፡ ይበሉ ፡ ገብሬ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፲፭/ አጋፋሪ ፡ ያረጋል ፡ ረታ ፡ (ደጃዝማች) ፡



ደጃዝማች ፡ አደፍርሰው ፡ ይናዱ ፡ (ራስ) ፡

፲፮/ አቶ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡ (ጸሐፌ ፡ ትእዛዝ) ፤
፲፯/ ቀኛዝማች ፡ መኩሪያ ፡ ባንትይርጉ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፲፰/ ግራዝማች ፡ ክፍሌ ፡ እርገቱ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፲፱/ ቀኛዝማች ፡ በልሁ ፡ ደገፉ ፡
፳/ አዛዥ ፡ ከበደ ፡ ተሰማ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፳፩/ ዶክተር ፡ መልአኩ ፡ በያን ፡
፳፪/ ሻለቃ ፡ መስፍን ፡ ስለሺ ፡ (ራስ) ፡

፷፫/ ግራዝማች ፡ አበራ ፡ ግዛው ፡
፷፬/ ልጅ ፡ አርአያ ፡ አበበ ፡
፷፭/ ልጅ ፡ ታደሰ ፡ ወልደ ፡ ጊዮርጊስ ፡
፷፮/ ልጅ ፡ ግህሌ ፡ ድልነሳሁ ፡ (ፊታውራሪ) ፡
፷፯/ ልጅ ፡ ደገፋ ፡ አየለ ፡ (ቀኛዝማች) ፡
፷፰/ ልጅ ፡ አድማሱ ፡ ገበየሁ ፡ (ሻቃ) ፡
፷፱/ ሊጋባ ፡ ባሰው ፡ ዋለሉ ፡ (ቆስሎ ፡ በቃሬዛ ፡ እስከ ፡ ሰላሌ ፡ መጥቶ ፡ ደብረ ፡ ሊባኖስ ፡ ቀረ ።



ግራዝማች ፡ ክፍሌ ፡ እርገቱ ፡ (ደጃዝማች) ፡

፸/ ግራዝማች ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ ማንያዝዋል ፡
፸፩/ ግራዝማች ፡ እንደሻው ፡ ቁንጮ ፡
፸፪/ አዛዥ ፡ ቦጋለ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ፡
፸፫/ አቶ ፡ ገብረ ፡ ወልድ ፡ እንግዳ ፡ ወርቅ ፡
፸፬/ አቶ ፡ መኰንን ፡ ወልደ ፡ ዮሐንስ ፡



፸፭/ አዛዥ ፡ ጥላዬ ፡ ተሰማ ፡
፸፮/ ልጅ ፡ ሉል ፡ ሰገድ ፡ በየነ ፡
፸፯/ ቀኛዝማች ፡ ዘረፉ ፡
፸፰/ ልጅ ፡ ስለሺ ፡ ዘረፉ ፡ (ቀኛዝማች) ፡
፸፱/ ልጅ ፡ ገሠሠ ፡ ጅማ ፡ (መቅደላ ፡ ላይ ፡ ሞተ) ።
፹/ መሸሻ ፡ ይዘሽዋል ፡
፹፩/ ልጅ ፡ መሸሻ ፡ ደስታ ፡ (ፎቶግራፍ ፡ አንሺ) ፡
፹፪/ የሙቶ ፡ አለቃ ፡ ተሾመ ፡ ገብረ ፡ ማርያም ፡ (አዛዥ) ፡
፹፫/ ግራዝማች ፡ ኃይለ ፡ ማርያም ፡ ገሠሠ ፡ (ደጃዝማች) ፡
፹፬/ ፊታውራሪ ፡ ዘውዱ ፡ አባኩራን ፡ (ደጃዝማች) ፡
፹፭/ ቀኛዝማች ፡ የሺነህ ፡
፹፮/ ቀኛዝማች ፡ ግፋ ፡ ወሰንና ፡ ሌሎችም ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ።

## ከቤተ ፡ ክህነት ፤

፩/ እጨጌ ፡ ገብረ ፡ ጊዮርጊስ ፡ (አቡነ ፡ ባስልዮስ) ፡
፪/ አቡነ ፡ ጴጥሮስ ፡
፫/ ሊቄ ፡ ገብረ ፡ ክርስቶስ ፤
፬/ ሊቀ ፡ ሊቃውንት ፡ ገብረ ፡ አብ ፡ (አቡነ ፡ ፊልጶስ) ፡
፭/ አጋፋሪ ፡ ግህሌ ፡ የበ ት ፡ ክህነት ፡ ሊቀ ፡ ካህናት ፡ ክፍል ፡
፮/ ሌሎችም ፡ ቀሳውስቶች ፡ ከጊዮርጊስ ፡ ጽላት ፡ ጋር ፡ በስዕል ፡ ቤት ፡ ድንኳን ፡ የሚአገለግሉ ፡ ብዙዎች ፡ ነበሩ ።

ማሳሰቢያ ፤ በቅንፍ ፡ ተከቦ ፡ የሚገኘው ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ሁሉ ፡ በኋላ ፡ የደረሱበት ፡ የማዕረግ ፡ ስም ፡ ነው ።

## አዲስ ፡ አበባ ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ ምክር ፡ ስለመደረጉ ፤

አዲስ ፡ አበባም ፡ ስንደርስ ፡ ግርማዊ ፡ ጃንሆይ ፡ ስለአውሮፕላኑ ፡ አደጋ ፡ እንጦጦ ፡ ጥግ ፡ መንበረ ፡ መኰንን ፡ ወደተባለው ፡ ቦታ ፡ ሲገቡ ፡ የተከተለው ፡ ሰው ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ከታችኛው ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እን ዲገኝ ፡ እየተነገረው ፡ ወደ ፡ ሰፈሩ ፡ ሄደ ።

እንደተቀጠረው ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ በታላቁ ፡ ቤተ ፡ መንግሥት ፡ እልፍኝ ፡ አዳራሽ ፡ በተባለው ፡ ቤት ፡ ውስጥ ፡ ስብሰባ ፡ ተደረገ ። በዚህም ፡ ስብሰባ ፡ ውስጥ ፡ ከዘመቻ ፡ የተመለሱት ፡ አዲስ ፡ አበባም ፡ የቆዩት ፡ መኳንንትና ፡ የጦር ፡ አለቆች ፡ አንድነት ፡ ነበሩ ። በምክሩም ፡ ጊዜ ፡ ብዙ ፡ ክርክር ፡ ተደረገና ፡ ሳይወሰን ፡ በማግሥቱ ፡ በ፲፩ ፡ ሰዓት ፡ ሁለተኛ ፡ ጊዜ ፡ ስብሰባ ፡ እንዲደረግ ፡ ተቀጥሮ ፡ ስብሰባው ፡ ተመለሰ ። የክርክሩም ፡ ዓይነት ፡ ሁለት ፡ መንገድ ፡ የያዘ ፡ ነበር ።

አንደኛው ፡ ክፍል ፡ የተገኘው ፡ ጦር ፡ ተዘጋጅቶ ፡ በሁለት ፡ እንዲከፈል ፡ ሆኖ ፡ አንደኛው ፡ ክፍል ፡ በበረሀና ፡ በጣርማ ፡ በር ፡ በኩል ፤ ሁለተኛው ፡ ክፍል ፡ በአህያ ፡ ፈጅ ፡ በጅሁር ፡ አፋፍ ፡ በኩል ፡ ተመድቦ ፡ እንዲከላከል ፡ የመንግሥቱ ፡ መሥሪያ ፡ ቤት ፡ ወደ ፡ ምዕራብ ፡ ኢትዮጵያ ፡ እንዲዛወር ፡ በማለት ፡ ነበር ። ሲስማማ ፡ ጦሩ ፡ አንድነት ፡ ሆኖ ፡ በሁለት ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ይዋጋ ፡ የሚለውን ፡ ሐሳብ ፡ ተቃውሞ ፡ ጦሩ ፡ ጥቂት ፡ በጥቂት ፡ እየተከፈለ ፡ በሁለቱም ፡ ግንባር ፡ የሽፍታ ፡ ጦርነት ፡ እያደረጉ ፡ ግራ ፡ ማግባት ፡ ነው ፡ እንጂ ፡ ባንድ ፡ ጊዜ ፡ ግጥሚያ ፡ ለማድረግ ፡ ድርጅቱ ፡ የማይበቃ ፡ ይሆንና ፡ የጦርነቱን ፡ ዕድሜ ፡ ያሳጥረዋል ፡ የሚል ፡ ሐሳብ ፡ ነበር ።

የዚህም ፡ ማስታወሻ ፡ ደራሲ ፡ የሆንኩት ፡ የእኔም ፡ ሐሳብ ፡ የሽፍትነቱን ፡ ውጊያና ፡ የመከላከል ፡ ዘዴ ፡ የሚደግፍ ፡ ነበር ።

ነገር ፡ ግን ፡ የክርክሩ ፡ ውጤት ፡ እሁለት ፡ በመከፈሉ ፡ ነገሩን ፡ አጥንቶ ፡ ለመወሰን ፡ በማግሥቱ ፡ ተገናኝተን ፡ ይወሰናል ፡ ተብሎ ፡ ተቀጥሮ ፡ በነበረው ፡ መሠረት ፡ ሲጠበቅ ፡ የትላንቱ ፡ ሐሳብ ፡ ተለውጦ ፡ ወደ ፡ ዓለም ፡ መንግሥታት ፡ ማኅበር ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥቱ ፡ ሄደው ፡ እንዲያመለክቱ ፤ እዚያ ፡ ድረስ ፡ ጦሩ ፡ በየሀገሩ ፡ ተሰማርቶ ፡ በሽፍትነት ፡ እየተከላከለ ፡ ከሰውም ፡ ሆነ ፡ ከእግዚአብሔር ፡ የሚገኘውን ፡ ፍርድ ፡ እንዲጠብቅ ፡ ተመክሮ ፡ ተወሰነና ፡ ኤውሮፓ ፡ ለመሄድ ፡ በሚያዝያ ፡ ፳፱ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፳፰ ፡ ዓ ፡ ም ፡ ቀዳሚ ፡ ወደ ፡ ጅቡቲ ፡ በባቡር ፡ ጉዞ ፡ ሆነ ።

## ጅቡቲ ፡ ከደረሰብኝ ፡ ችግር ።

የልጅ ፡ ወርቅነህ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤልን ፡ ውለታ ፡ ለማስታወስ ፡ በዚህ ፡ ታሪክ ፡ ማስታወሻ ፡ ላይ ፡ ሥዕሉ ፡ እንዲገኝ ፡ ተደርጓል ። ውለታው ፡ ታሪክ ፡ ጸሐፊው ፡ ከዋናው ፡ ጦር ፡ ግንባር ፡ ከማይጨው ፡ እንደ ፡ ተመለሰ ፡ ቅሌን ፡ ጨርቄን ፡ ሳይል ፡ ሲታዘዝ ፡ ብድግ ፡ ብሎ ፡ እስረኛ ፡ ይዞ ፡ የወጣ ፡ ስለነበረ ፡ ልብስ ፡ የሚይዝበት ፡ ሻንጣ ፡ የሚገዛበት ፤ ገንዘብ ፡ የሌለው ፡ ነበር ። በዚህ ፡ ጊዜ ፡ የልጅነት ፡ አእምሮው ፡ ሳያግደው ፡ የእሱን ፡ ዕቃ ፡ አውጥቶ ፡ ሻንጣውን ፡ ለችግረኛው ፡ ስደተኛ ፡ በመስጠት ፡ ውለታ ፡ የጣለብኝ ፡ ስለሆንኩ ፡ ሳስታውሰው ፡ ነው ፡ የኖርኩት ። አሁን ፡ ግን ፡ እዚህ ፡ ላይ ፡ ያኖርኩት ፡ እኔ ፡ ስሄድ ፡ እንዳይረሳ ፡ ነው ።





ልጅ ፡ ወርቅነህ ፡ ወልደ ፡ አማኑኤል ፡ (ደጃዝማች) ።